በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማሳያ የሚሆን ሥርዓተ ትምህርት

አዘጋጅ የሰንት ትምህርት ቤቶች ጎብረት

2008ዓ.ም

ምስጋናAcknowledgment

ምንተኑ አዐስዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኩሉ ዘገብረ ሊተ መዝ115፤3

ከሁሉ በማስቀደም በጎ ነገር ማድረግ ልማዱ የሆነ እግዚአብሔር አምላካችንን ስላደረልን በጎ ነገር ሁሉ እናመሰግነዋለን፤ ልመናችንን ሁሉ በየጊዜው ሰምታ ግዳጃችንን ምትፈጽምልኝ ለአብ መርአቱ ለወልድ ወላዲቱ ለመንፈስ ቅዱስ ጽርሐ ቤቱ የሆነች ድንግል ማርያምን እናመሰግናለን።በረድኤተ እግዚአብሔር ይህንን ማሳያ ሥርዓተ ትምህርት ስናዘጋጅ በማንኛውም መንገድ ሲረዱን የነበሩትን ሁሉ አምላከ ቅዱሳን በምድር በሰማይ በጎ ዋጋቸውን ይስጥልን።

አጠቃሎAbstract

ይህ ማሳያ የሚሆን ሥርዓተ ትምህርት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሰንበት ትምህርት ቤቶች በአስሩም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ በአራቱም ማዕዘናት ማለት በምስራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ በሚገኙ ከ100 በላይ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት ላይ የተዘጋጀ የዳሰሳ ጥናት መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት ማሳያ ሲሆን በሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ በምልከታ በመጠይቅ እና በመጠየቂያ ጥያቄዎች በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ የጋራ የሚባል የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ክፍተት በመታየቱ ይህንን ምክንያት በማድረግ ወጥ የሆነ እና የተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ማሳያ እንዲሆን ሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶችን አንድ የሚያደርግ ሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሠጡ በሁሉም ግቢ ጉባኤያት እና መንፈሳዊ ኮሌጆቻችን በዲፕሎማ ደረጃ ከሚሰጡ ኮርሶች ከእንግሊዘኛ በቀር ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ የትምህርት ዓይነቶች ከነዓላማ ይዘት ማስተማሪያ ዘዴ መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ ምዘና እና ግምገማ እንዲሁም የጊዜ ሰሌዳን የያዘ ማሳያ የሚሆን ሥርዓተ ትምህርትም እንዲዘጋጅ ሆኖዋል።

አበርክቶት

ይህ ማሳያ ሥርዓተ ትምህርት መታሰቢያነቱ ከልጅነት እስከ እውቀት በመንፈሳዊ ትምህርት እግዚአብሔርን በመፍራት ኮትኩተው ላሳደጉን ለሚያሳድጉን ፍቅረ ቤተክርስቲያንን ፈሪሐ እግዚአብሔርን ሀገር መውደድን ሰውን ማክበር ማፍቀርን

ላስተማሩን እና ለሚያስተምሩን እያስተማሩን ላሉት እና ወደ ፊትም ለሚያስተምሩን ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን እና በሰንበት ትምህርት ቤት በበጎ ፈቃድ በመንፈሳዊ ቅናት እና በጎነት ተነሳስተው ላስተማሩን እያስተማሩን ላሉት እና ወደ ፊትም ለሚያስተምሩን መምህራን ይሁን።።።

ምንተኑ አአስዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኩሉ ዘገብረ ሊተ መዝ65፣

መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሶስቱም ህግጋት ማለትም በህገ ልቡና በህገ ኦሪት እና በህገ ወንጌል ፈጣሪን በማምለክ የኖረች እና ዘመናትን የተሻገረች ስትሆን ቤተክርስቲያናችን ከጥንት እስከ ዛሬ ለሀገሪቱ እድገት፣ ልማት፣ እውቀት፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ፍልስፍና፣ ህክምና፣ ምህንድስና፣ መንፈሳዊም ስጋዊም ብልጽግና፣ ምንጭ፣መገኛ እና መሰረት የነበረች በተጨማሪም አሁንም ያንኑ

ባለማቋረጥ እየሰጠች ያለች ሲሆን ግብረገብ የሆነ ሀገሩን የሚወድ አምራች ቤተሰቡን እና ራሱን የሚረዳ ዜጋ በመፍጠር ለሀገር እድገት እያበረከተች ያለችው አስተዋጽኦ በቃላት የማይገልጹትነው። ከዚህ በዘለለ ለህዝብ እርስ በእርስ ተከባብሮ እና ተረዳድቶ በሰላም እና በፍቅር እንዲኖር የሀገር አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር መተኪያ የማይገኝለት አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች።የቤተክርስቲያናችን አንድ አካል የሆኑት ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ደግሞ ይህንኑ ከቤተክርስቲያናችን ያገኘነውን አባቶቻችን እና እናቶቻችን በቃል ፤ በህይወት ፤ ያወረሱንን እና ያሳዩንን በጎ ትምህርት እና ህይወት ለተተኪው ትውልድ ሳይበረዝ እና ሳይከለስ የሚያስተላልፉ የህይወት ምንጮች እና ህያዋን ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ ከተመሰረቱበት ወቅት ጀምሮ በሚችሉት አቅም ሁሉ ትምህርተ ቤተክርስቲያንን ማለት መሰረተ እምነትዋን ሥርዓትዋን እና ትውፊትዋን ለምእመናን በሙሉ በመዝሙራት በትምህርት እና በህይወት ሲገልጹ ኖረዋል። ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ለግማሽ ምዕት ዓመታት የጠለቀ የነገረ እግዚአብሔር ትምህርት በተደራጀ እና በተጠናከረ መልኩ እንዳይሰጡ እንቅፋት ከሆኑባቸው ነገሮች አንዱ ወጥ የሆነ የተደራጀ እና በባለሙያ የተጠና ሥርዓተ ትምህርት አለመኖሩን ብዙዎች የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮች በአንድ ድምጽ የሚመሰክሩት እውነታ ነው ይህ የተደራጀ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት አለመኖር የሰንበት ትምህርት ቤቶችን የአንድነት መንፈስ የፈታ እና ሁሉም ለየግሉ የመሰለውን እንዲያስተምር እና እንዲማር ያደረገና እድገት እንዳናመጣ ሁልጊዜ ባለንበት እንድንሆን ያደረገ በተለይ በውጤት ላይ ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ሲመዘኑ የእውቀት ክፍተት ያለባቸው ግማሹ ዘፋኝ መናፍቅ ፕሮቴስታንት ሰንበት ተማሪ ነበርኩ የሚል ትውልድ ለማፍራት የቻልነው የተጠናከረ ሥርዓተ ትምህርትን መሰረት ያደረገ ትምህርት በሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን መስጠት ባለመቻላችን እና ከመዝሙር ቤትነት ወደ ትምህርት ቤትነት መቀየር ባለመቻላችን ነው ፤ በመሆኑም የተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን ትምህርት ቤት ከማድረጉም በዘለለ ለሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ዘላቂ ጎብረት እና የእውቀት ሙላት እንዲሁም በጎ ኦርቶዶክሳዊ ህይወት መተኪያ የማይገኝለት መፍትሄ በመሆኑ ሁሉን ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድ የሚያደርግ ሥርዓተ ትምህርት ሊሆን ይችላል ብለን ያመንበትን ለምክረ ሀሳብ እና ለውይይት እንዲህ ባለ መልክ አቅርበነዋል።ይህ ሥርዓተ ትምህርት ለሰንበት ትምህርት ቤቶች የሥርዓተ ትምህርት ማሳያ ይሆናል ተብሎ ለውይይት የቀረበ እና የተዘጋጀ እንጂ በሚመለከተው አካል ባለድርሻ አካላት ሳይስማሙበት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት ከዛሬ ጀምሮ ይህ ነው ለማለት የቀረበ እንዳልሆነ ሁሉም ሰው እንዲያውቅልን እንፈልጋለን ።

ሰላመ እግዚአብሔር አይለየን።

ማውጫ

ተ.ቁ	ክፍል	የትምህርቱ ዓይነት	ገጽ	ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ	ኮርስኮድ	ምርመራ
1		መግቢያ	3			
2		አጠቃላይ ስለ ሥርዓተ ትህርት	7			

		የሰ/ት/ቤ/ን ገጽታ ራዕይ ግብ	7			
3		ተልእኮ ዓላማ	7			
4		የትኩረት አቅጣጫዎች	8			
5		የፍላት እና አቅርቦት ሁኔታ	8			
6		ጠንካራ እና ደካማ ጎኖቻችን	9			
7		መልካም አጋጣሚዎች	10			
8		ስጋቶች ተጠቃሚዎች	10			
9		የእቅድ ትግባራ	11-12			
10		ቴክኒካዊ ጥናት	12			
11		የገንዘብ ትንተና የገቢ ምንጭ እና	13			
12		ቁጥጥር እና ግምገማ	13			
13		ቀጣይ እቅድ	14			
14		ሰንበት ትምህርት ቤት ምንድነው	14-15			
15		ሥርዓተ ትምህርት ምንድነው	15			
16		የሥርዓተ ትምህርት ሂደት	15			
17		የሥርዓተ ትምህርት ዓይነቶች	16			
18		የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ	16			
19		የሥርዓተ ትምህርት ዕቅድ ዝግጅት	16			
20		የሥርዓተ ትምህርት ሥርጭት	17			
21		ምዘና እና ግምገማ ዘዴ የምዘና መስፈርቶች	17			
		ትምህርቶችበክፍለ ትምህርት(በዲፓርትሜንት)				
22		ማስተማሪያ ዘዴ	18			
23		የመማር ማስተማር መርኖች	19			
24		የሰንበት ትምህርት ቤቶች ትምህርት ከአብነት ትምህርቶች አንጻር	20			

25		የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የትምህርት ዓይነቶች	21			
	1ኛክፍል	የህፃናት አንድ ትምህርት	22			
26		ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር	22-26	12ሰዓት	ህ/ክ/ሥ/ም1	
27		ግእዝ (ንባብ እና ቃል ጥናት)	27-30	16ሰዓት	ህ/ግ/ቋ/1	
28		ዜማ(አጫጭር የግእዝ መዝሙራት)	31-34	12ሰዓት	ህ/ዜ/1	
29		የቤተክርስቲያን ታሪክ (የቤ/ን ዓላት)	35-39	16ሰዓት	ህ/ቤ/ታ/1	
	2ኛክፍል	ህጻናት ሁለት	40			
30		ትምህርተ ሃይማኖት(አእማደምስጢርንበጥያቄ	40-43	16ሰዓት	ህ/ት/ሃ/1	
31		ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር	44-46	12ሰዓት	ህ/ክ/ሥ/ም/2	
32		ግእዝ(የቃል ጥናት)	47-50	16ሰዓት	ህ/ግ/ቋ/2	
33		ዜማ(አጫጭር የግእዝ መዝሙራት)	51-54	16ሰዓት	ህ/ዜ/2	
34		የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት(የብሉይ ኪዳን ታሪክ)	55-58	16ሰዓት	ህ/መ/ቅ/ጥ/1	
35		የቤተክርስቲያን ታሪክ	59-63	16ሰዓት	ህ/ቤ/ታ/2	
	3ኛክፍል	ሶስተኛ ክፍል የህፃናት ሶስት ትምህርት	64			
36		ትምህርተ ሃይማኖት ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በጥያቄና መልስ	64-66	16ሰዓት	ህ/ሃ/ት/2	
37		ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር	67-68	12ሰዓት	ህ/ክ/ሥ/ም/3	
38		ዜማ(መዝሙር)	69-71	16ሰዓት	ህ/ዜ/3	
39		የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሀዲስ ኪዳን ጥናት	72-74	16ሰዓት	ህ/መ/ቅ/ጥ/2	
40		የቤተክርስቲያን ታሪክ	75-77	16ሰዓት	ህ/ቤ/ክ/3	
41		ግእዝ(የቃልጥናት)	78-80	16ሰዓት	ህ/ግ/ቋ/3	
	4ኛክፍል	የአዳጊ አንድ ትምህርት	81			

42		ዜማ(መዝሙር)	81-83	16ሰዓት	ህ/ዜ/4	
43		ግእዝ(የቃልጥናት)	84-86	16ሰዓት	ህ/ግ/ቋ/4	
44		ትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ	87-89	10ሰዓት	ህ/ት/ሃ/3	
45		የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያ	90-92	10ሰዓት	ህ/መ/ቅ/ጥ/3	
46		ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር	93-95	16ሰዓት	ህ/ክሥ/ም/4	
47		የቤተክርስቲያን ታሪክ	96-98	12ሰዓት	ህ/ቤ/ታ/4	
	5ኛክፍል	የአዳጊ ሁለት ትምህርት	99			
48		ትምህርተ ሃይማኖት ነገረ ማርያም	99-102	12ሰዓት	ህ/ት/ሃ/4	
49		የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አዋልድ መጻሕፍ	103-105	8ሰዓት	ህ/መ/ቅ/ጥ/4	
50		ግእዝ መልክዐ ማርያም	106-108	16ሰዓት	ህ/ግ/ቋ/5	
51		የቤተክርስቲያን ታሪክ መግቢያውን	109-111	12ሰዓት	ህ/ቤ/ክ/5	
52		ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር	112-114	22ሰዓት	ህ/ክ/ሥ/ም5	
53		ዜማ ውዳሴ ማርያም	115-117	16ሰዓት	ህ/ዜ/5	
	6ኛክፍል	የማዕከላውያን ትምህርት	118			
54		ግእዝ መልክዓ ኢየሱስ	118-120	12ሰዓት		
55		ዜማ ውዳሴማርያም	121-122	16ሰዓት		
56		ቤተክርስቲያንህን እወቅ(ሥርዓተ ቤ/ክ)	123-124	16ሰዓት		
57		ትምህርተ ሃይማኖት ነገረ ቅዱሳን	125-126	12ሰዓት		
58		ኦርቶዶክሳዊ የጾታ ትምህርት	127-128	12ሰዓት		
59		ሥርዓተ ቅዳሴ የሕዝብ ተሰጥኦ	129-130	16ሰዓት		
	7ኛክፍል	የቀዳማይ ክፍል ትምህርት	131			
60		ትምህርተ ሃይማኖት	131-134	38ሰዓት	ወ/ት/ሃ/1	

61		የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት	135-139	38ሰዓት	ወ/መ/ቅ/ጥ/1	
62		ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር	140-143	28ሰዓት	ወ/ክ/ሥ/ም/1	
63		የቤተክርስቲያንታሪክበዓለም መድረክመግቢያ	144-148	28ሰዓት	ወ/ቤ/ክ/ታ/1	
64		ግእዝ መግቢያ	149-152	28ሰዓት	ወ/ግ/ቋ/1	
	8ኛክፍል	የካልዓይ ክፍል ትምህርት	153			
65		የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ	153-157	38ሰዓት	ወ/ቤ/ክ/ታ/2	
66		የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታሪክ	158-161	38ሰዓት	ወ/ቤ/ክ/ታ/3	
67		የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ	162-165	38ሰዓት	ወ/ማ/ት/1	
68		ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን	166-169	28ሰዓት	ወ/ት/ሃ/ም/2	
69		የግእዝ ቋንቋ2	170-173	28ሰዓት	ወ/ግ/ቋ/2	
	9ኛክፍል	የሣልሳይ ክፍል ትምህርት	174			
70		ግእዝ3	174-177	28ሰዓት	ወ/ግቋ/3	
71		ትምህርተ አበው	178-181	28ሰዓት	ወ/ዜ/አ/1	
72		የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ1	182-185	38ሰዓት	ወ/ዮ/ት/	
73		ክርስቲያናዊ ህይወት	186-189	28ሰዓት	ወ/ክ/ሥ/ም/2	
74		ኦርቶዶክሳዊመዝሙርእና ምስጢራዊ ሥርዓቱ	190-193	16ሰዓት	ወ/ዜ/1	
75		ፍልስፍና መግቢያ	194-195	16ሰዓት	ወ/ፍ/1	
	10ኛክፍል	የራብዓይ ክፍል ትምህርት	196			
76		የቤተክርስቲያን አስተዳደር	196-199	28ሰዓት	ወ/ቤ/ክ/አ/1	
77		የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ	200-203	28ሰዓት	ወ/ዮ/ት/2	

78		ሥርዓተ ቤተክርስቲያን	204-207	28ሰዓት	ወ/ሥ/ቤ/2	
79		የግእዝ ቋንቋ4	208-211	28ሰዓት	ወ/ግ/ቋ/4	
80		የጥናት እና ምርምር ዘዴ	212-215	28ሰዓት	ወ/ጥ/ም/ዘ/1	
81		ክርስትና እና መገናኛ ብዙኃን	216-218	12ሰዓት	ወ/ክ/ሥ/ም3	
	11ኛክፍል	የኃምሳይ ክፍልትምህርት	219			
82		ሐዋርያዊ ተልእኮ	219-223	16ሰዓት	ወ/ሐ/ተ/1	
83		የዕብራውያን መልእክት ትርጓሜ	224-227	38ሰዓት	ወ/ዕ/ት/1	
84		ኦርቶዶክሳዊ የጾታ ትምህርት እና የልጆች አስተዳደግ	228-231	18ሰዓት	ወ/ክ/ሥ/ም4	
85		አንጻራዊ ትምህርተ መለኮት	232-235	28ሰዓት	ወ/ት/ሃ/2	
86		ሰዓታት1	236-238	38ሰዓት	ወ/ዜ/2	
87		ሥነ ልቡና መግቢያ	239-241	16ሰዓት	ወ/ሥ/ል1	
	12ኛክፍል	የሳድሳይ ክፍል ትምህርት	242			
88		ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ	242-245	20ሰዓት	ወ/ኦ/ስ/ዘ1	
89		ሥርዓተ ቅዳሴ	246-249	32ሰዓት	ወ/ሥ/ቤ/ክ2	
90		የዮሐንስ ራዕይትርጓሜ	250-253	38ሰዓት	ወ/ዮ/ራ/ት/1	
91		ሰዓታት2	254-257	38ሰዓት	ወ/ዜ/3	
92		የግእዝ ቋንቋ አገባብ እና ቅኔ	258-261	38ሰዓት	ወ/ግ/ቋ/5	
93		ባህረ ሀሳብ	262-264	16ሰዓት	ወ/ባ/ሃ/1	
	ልዩ ክፍል	የልህቅት ማእከላት አብነት ትምህርት	265			
94		ንባብ ቤት		2ዓመት	አ/ን/ቤ	
95		ዜማ ቤት		3ዓመት	አ/ዜ/ቤ	

96		ቅዳሴ ቤት		3ዓመት	አ/ቅ/ቤ	
97		ቅኔ ቤት		2ዓመት	አ/ቅ/ቤ	
98		አቋቋም ቤት		3ዓመት	አ/አ/ቤ	
99		ብሉያት ትርጓሜ ቤት		5ዓመት	አ/ብ/ት/ቤ	
100		ሐዲሳት ትርጓሜ ቤት		4ዓመት	አ/ሐ/ት/ቤ	
101		ሊቃውንት ትርጓሜ ቤት		5ዓመት	አ/ሊ/ት/ቤ	
102		መነኮሳት ትርጓሜ ቤት		4ዓመት	አ/መ/ት/ቤ	
103		ቁምጽህፈት እና ሥነ ሥዕል		2ዓመት	አ/ሥ/ሥ/ቤ	
104		የመዝሙር መገልገያ ንዋያት ጥናት		2ዓመት	አ/መ/መ/ቤ	
105		መዝሙር ጥናት		3ዓመት	አ/መ/ጥ/ቤ	

<u>አጠቃላይ ስለ ሥርዓተ ትምህርቱ</u>

ሥርዓተ ትምህርቱ ሁኔታዊ ሥርዓተ ትምህርት (Setuational curriculm) ዓይነት ሲሆን ሙሉ ለሙሉ ሁሉንም ክፍላት ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉ ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉ ሲሆን ተግባዊ ለማድረግ

1. የሰንበት ትምህርት ቤቱ መዋቅር
2. የመምህራን ብዛት እና እውቀት ውሱንነት
3. የመማሪያ ቦታና ማስተማሪያና ማመሳከሪያ መርጃ መሳሪያ ዝግጅት ጉድለት
4. የተማሪ ማነስና መብዛት
5. የቦታ ቅርበት እና ርቀት ምቹነት
6. ትምህሮቹ የተማሪዎችን እድሜ ባማከለ የተዋቀሩ በመሆናቸው በተቻለ መጠን ከእድሜያቸውእና ትምህርቱን

ከመቀበል አቅማቸው ጋር ጋር በሚሄድ መልኩ አገናዝበን መስጠት ብንችል ጥሩ ነው

7. ሌሎች ባህላዊ፣ አካባቢያዊ፣ ፖለቲካዊ፣መልክዓምድራዊ ሁኔታዎች ተግባራዊ ለማድረግ የማይፈቅዱላቸው ሰንበት ትምህርት ቤቶች ከተቀመጡት ክፍሎች እና የትምህርት ዓይነቶች የሚችሉትን ብቻ የሚያስተምሩ ይሆናል ሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች በስልታዊ እቅዱ ላይ የተቀመጠውን ራዕይ፣ ግብ፣ዓላማ፣ተልእኮ፣በመተግበር አንድነታቸውን ያሳያሉ ሁሉም በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በተቀመጠው ዓላማ አንድ ይሆናሉ።

   የሚለኩትም በዓላማው ይሆናል።ይዘት እና ትምህርቶቹን እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ ሁኔታ እየለዋወጡ የሚሰጡ ይሆናል።

   ትምህርቶቹበተቻለ መጠን በመደበኛ የቅዳሜና እሑድ ቀናት የሚሰጡ ከሆነ ወይም ባዘቦት ከሰኞ እስከ ዐርብ ማታ ማታ በተቻለ መጠን የመጀመሪያ ትምህርቶች ማለት ቅዳሜ ስነምግባር እና ታሪክ ነክ እሁድ ሃይማኖት (ዶግማዊ) ትምህርቶች እንዲሰጡ ማድረግ

<u>የሥርዓተ ትምህርቱ አካባቢያው ገጽታ</u>

ሥርዓተ ትምህርቱ በዋነኛነት በጥናት ተደግፎ የጥናት አካባቢውን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ አስሩም ክፍለ ከተሞች ላይ በሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች መሰረት ያደረገ ሲሆን ከእነሱ ለጥናት የተወሰነ ናሙና በመውሰድ ሲሆን አብዛኛው ሰንበት ትምህርት ቤት ከህጻናት ክፍል ጀምሮ የተደራጀ የሥርዓተ ትምህርት ግብዓቶችን ያካተተ ሥርዓተ ትምህርት እንደሌላቸው በጥናት ያረጋገጥን ሲሆን በዚህም ምክንያት የሰንበት ተማሪው ህይወት ላይ በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ።

ያንን ችግር ለመቅረፍ እና ሌሎቹንም ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማለት በሀገራችን በክልሎች የሚገኙትንም ከሀገር ውጭ ያሉትንም አንድ የሚያደርግ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግ የተሞከረ ሲሆን በሀገራችን በክልሎች የሚገኙት ሁሉም በክልል ቋንቋቸው ሥርዓተ ትምህርቱን ተርጉመው

የሚጠቀሙበት ይሆናል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሥርዓተ ትምህርቱን በተለያዩ የሀገራችን እና ዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ተርጉሞ በመረጃ መረብ ላይ የሚለቀቅ ይሆናል።

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ራዕይ</u>

ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የቤተክርስቲያናችንን መሰረተ እምነት በሚገባ ጠብቀው ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ጠብቀው እና አስጠብቀው በቤተክርስቲያናችንን ትውፊት በበጎ ክርስቲያናዊ ህይወት ሲኖሩ እና ከአባቶቻችን ጋር በእውቀት ተካክለው የእነሱን ትምህርት ሲያስተምሩ የቤተክርስቲያናችንን ዝማሬ ሲዘምሩ ቅኔ ሲቀኙ ትርጓሜ ሲያብራሩ ዝማሜ ሲዘምሙ ማየት ነው።

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ግብ</u>

ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን በሁሉም ነገር በጎ አርዓያ መልካም አብነት መሆን እና ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን የነገረ እግዚአብሔር እና የአብነት ትምህርት የልህቀት ማዕከል (center of excellence) ማድረግ ነው።በአዲስ አበባ እና በክልሎች በተመረጡ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ትምህርትን ወደ ከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በኮሌጅ ደረጃ የነገረ መለኮትን እና የአብነት ትምህርቶችን መስጠት ነው።

ለመንፈሳዊ ኮሌጆቻችን ተማሪዎችን የሚመግቡ መምህራኑንም የሚያወጡ ሆኖ መገኘት ነው

ተልእኮ

የቤተክርስቲያናችንን መሰረተ እምነት ሥርዓት እና ቅዱስ ትውፊት በማስተማር በሰንበት ተማሪዎች ላይ የሚታየውን የእውቀት እና የሥነ ምግባር ችግሮች ደረጃ በደረጃ መቅረፍ እና ስብከተ ወንጌልን በመላው ዓለም ማስፋፋት ነው።

የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ዓላማዎች

1.ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የሚመጡ ምዕመናንን መሰረተ እምነት (ዶግማ) ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን (ቀኖና) የቤተክርስቲያንን ቅዱስ ትውፊት (ባህል) እና ሥነ ምግባርን ማስተማር

2.የአብነት ትምህርቶችን በሰንበት ትምህርት ቤት በተጠናከረ ሁኔታ መስጠት

3.ማንኛውም የቤተክርስቲያናችን አባል ሃይማኖቱን እና የሃይማኖቱን ሥርዓት እንዲያውቅ ማድረግ

4.መንፈሳዊያን ህፃናት በሰንበት ትምህርት ቤት ተደራጅተው እየተማሩ የሀገርንም ሆነ የቤተክርስቲያንን ታሪክ በሚገባ አውቀው በነገረ መለኮት ሃይማኖታዊ ትምህርት ብስለት እንዲያገኙ እና የነገዋን ቤተክርስቲያን በኃላፊነት ለመረከብ የሚችሉ እና ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ

5.በበጎ ሥነ ምግባር የታነጹ ምዕመናን ለሀገር እና ለወገን የሚበጁ ትውልድ እንዲፈሩ ማድረግ

6.በቅዱሳት መጻህፍት እውቀት የበረቱ እንዲሆኑ ማስቻል ነው

የትኩረት አቅጣጫዎች

1.የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የትኩረት አቅጣጫዎች በዋነኛነት ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት መስጠት ሲሆን

2.የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን ትምህርት በደረጃ ተከፋፍሎ ወጥነት እና ተከታታይነት ኖሮት እንዲሰጥ ማድረግ

3.በሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የሚሰጠውን ትምህርት አንድ ዓይነት ማድረግ

4.የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን ሥርዓተ ትምህርት በየጊዜው መከለስ

5.የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን ሥርዓተ ትምህርት የሚያዘጋጅ የሚገመግም ክፍል ማቋቋም

6.ሁሉን አቀፍ የሆነ የትምህርት ማእከላት መቋቋም

7.ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን በትምህርት በቁሳቁስ በቴክኒክ የሚረዳዱበትን መንገድ ማመቻቸት

8.በአዲስ አበባ በአራቱም አቅጣጫ መ/ገ/ጽ/ቅ/ጊዮርጊስን ጨምሮ 5 የልህቀት ማዕከላትን መፍጠር እነዚህ ማእከላት ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ምስክር ቤቶች እንዲሆኑ ማድረግ

9.የተመረጡት 5 ሰንበት ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን በማሳደግ በዲፕሎማ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ

10. በሀገራችን በተለያዩ ክልሎችም እንዲሁ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ምስክር ቤቶች (የልህቀት ማእከላትን) መፍጠር ነው።

የትምህርት ፍላጎት እና አቅርቦት ሁኔታ

በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ካለው ህዝብ ብዛት እና ከኦርቶዶክሳዊው ምዕመን አንጻር ህጻናቱ እና ወጣቱ ብዙውን የሚይዝ ሲሆን እነዚህን የሚያስተምሩ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እና መምህራኑ ግን በጣም ጥቂት መሆናቸውን በአዲስ አበባ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ለመረዳት ተችሎዋል በመሆኑም የምዕመኑን መንፈሳዊ ትምህርት ፍላጎት ለማርካት መንፈሳዊውን ትምህርት በሚገባ ተምረው የሚያስተምሩ መምህራን እና ምዕመኑን ከእድሜው ከዕውቀት ደረጃው ጋር ተመጣኝ እና በደረጃ የተከፋፈለ ምዕመኑ ያለበትን ችግር የሚፈታ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ያስፈልጋሉ።

ከዚህም በዘለለ የቤተክርስቲያናችንን የአብነት ትምህርት ለመማር የሚፈልጉ ብዙ ሰንበት ተማሪዎች እንዳሉ ለማስተማር የሚችሉ ብዙ መምህራነ ቤተክርስቲያንም በቤተክርስቲያናችን አሉ በመሆኑም ሁለቱን ተፈላላጊዎች ማቀራረብ እና በአባቶች እግር የሚተካ እነሱን መስሎ እና አህሎ ቤተክርስቲያንን የሚያገለግል ሰንበት ተማሪን ማውጣት እና ማፍራት ያለባቸው ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ናቸው በዚህ ረገድ ከጥቂት ሰንበት ትምህርት ቤቶች በቀር ሁሉም ሥርዓተ ትምህርት ቀርጸው መምህር እና ቦታ መድበው ደረጃ ሰጥተው የሚያስመሰክሩ የሚመርቁ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ከብዛታቸው አንጻር ጥቂት በመሆናቸው በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አብነት ትምህርት የሰንበት ትምህርት ቤቱ አንዱ የትምህርት አካል እንዲሆን እና ሁሉም ምዕመን የቤተክርስቲያንን ትምህርት እንዲያገኝ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርታቸውን በዚህ ረገድ መልሰው ሊያስተካክሉት ይገባል።

ጠንካራ ደካማ ጎን መልካም አጋጣሚ እና ስጋቶች

የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ጠንካራ ጎን

1.የተደራጀ ሳይንሳዊ የሆነ ሥርዓተ ትምህረት ለመቅረጽ እና ለመተግበር የሚችል አቅም መኖሩ

2.ሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማለት ይቻላል ቢያንስ ሁለት እና ከዛ በላይ የመምህርነት ኮርስ ሥነ ትምህርት የወሰዱ መምህራን መኖራቸው

3.በሰንበት ትምህርት ቤት የቤተክርስቲያንን የአብነት ትምህርት የተማሩ ሰንበት ተማሪዎች መኖራቸው

4.በቤተክርስቲያናችን የአብነቱን ትምህርት በመምህርነት አስመስክረው ማስተማር የሚፈልጉ መኖራቸው

5.የቤተክርስቲያንን የአብነቱንም የነገረ መለኮትንም ትምህርት ለመማር የሚፈልጉ ብዙ ምዕመናን መኖራቸው

6.የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን እድገት ሁሉም የቤተክርስቲያናችን አባቶች ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ የሚፈልጉት እና የሚመኙት መሆኑ

7.ስለ ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ምዕመናንም ሆኑ አገልጋይ ካህናት ቀና ነገር መኖሩ

8.ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ዕቅድ አቅደው ፕሮጀክት ነድፈው ለመተግበር የእውቀት የቦታ የገንዘብ አቅም ማዳበራቸው

9.በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ የአብነት ትምህርቱንም የነገረ መለኮት ትምህርቱንም በጉባኤው ቤት ውለው ያስመሰከሩ አባላት መኖራቸው

10.አንዳንድ ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የራሳቸው የሆነ መማሪያ እና ማስተማሪያ ቦታ ፣ቤተ መጻህት ያላቸው መሆኑ

የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ደካማ ጎን

1. አንዳንድ ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የመማሪያ እና ማስተማሪያ ቦታ በበቂ ሁኔታ አለመኖር

2.ራቅ ባሉ እና ከተማ ውስጥ ባሉ አብዛኛው ሰንበት ትምህርት ቤቶች የተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት አለመኖር

3.በተለያዩ ማኅበራዊ ፖለቲካዊ መንፈሳዊ ሥነልቡናዊ ችግሮች አባላት ከሰንበት ትምህርት ቤቶች መራቅ

4.የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ዓላማ ጥቅም እና አቅም ያልተረዱ የቤተክርስቲያናችን አካላት በተለያየ ወቅት ችግር መፍጠራቸው

5. የመናፍቃኑ ቅሰጣ እና የሐሰት ትምህርት በአንዳንድ ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ላይ የሚፈጥሩት ጫና

6.በትምህርት ለውጥ ማጣት በሚገባ አለመማር

7.በቤተክርስቲያን ጉዳይ ቀጥተኛ ተሳታፊ አለመሆን

8.የጋራ የሆነ ስልታዊ እቅድ አለመኖር

9.የበጀት እጥረት ጊዜ ማነስ

10.የመንፈሳዊ ህይወት ዝለት በሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ላይ መታየት

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን መልካም አጋጣሚዎች</u>

1.በራሳቸው በጀት የሚንቀሳቀሱ ለቤተክርስቲያን ሁሉን ነገራቸውን የሚሰጡ አባላት መኖራቸው

2.ለመማር ለማስተማር የሚከለክል ምንም ነገር አለመኖሩ

3.አገልግሎቱን እና የትምህርት ሥርዓቱን በየጊዜው እያሳደጉ ለመምጣት መቻሉ

4.ሰንበት ትምህርት ቤትን እና አገልግሎቱን ፈላጊው ብዙ መሆኑ

5.በከተማ የሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች በማንኛውም ወቅት እና ሰዓት ትምህርት ለመማር እና ለማስተማር በቃለ አዋዲው ላይ በቅዱስ ሲኖዶስ ስልጣን መሰጠቱ

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ስጋቶች</u>

1.ቢጽሐሳውያን (ፕሮቴስታንታዊ ተሀድሶዎች፤ መናፍቃን፤ ፕሮቴስታንቶች፤አክራሪ ሙስሊሞች እና ሉላዊነት ዓለምአቀፍ ጸረሃይማኖት ተቋማት እና መሰሎቻቸው)

2.የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ዓላማ እና ጥቅም እንዲሁም አቅም ያልገባቸው የቤተክርስቲያን አገልጋዮች

3.በስሜት ብቻ የሚመላለሱ ዓላማቸውን የሳቱ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አባላት

4.የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የገንዘብ አቅም ውሱንነት

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቱ ትምህርት ተጠቃሚዎች</u>

1. በእያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያን የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ምዕመናን ያለ ምንም ልዩነት
2. በአጥቢያው የሚገኙ ማኅበረ ካህናት የአብነቱንም የነገረ መለኮትንም ትምህርት በመማር በማስተማር

3. ሰንበት ተማሪዎች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት በመማር በማስተማር
4. የሰንበት ተማሪዎች ወላጆች ልጆቻቸው በፈሪሀ እግዚአብሔር በአክብሮ ሰብእ ያድጋሉና
5. በጎ ቅን እና በሥነ ምግባር የተኮተኮተ ምዕመን እና ዜጋ በማግኘት ሀገሪቱ
6. ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያው የሰንበት ተማሪዎችን ሙሉ ነገር መጠቀም በመቻል
7. ሌሎች በሰላም በፍቅር በትህትና የሚኖር ማኅበረሰብእ ያገኛሉ

<u>የትግበራ እቅድ</u>

ይህንን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት ለመተግበር የጥናቱ ውጤት ቅዱስ ፓትርያርኩ ከተቻላቸው እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የበላይ ኃላፊ የከንባታ ሀድያና ስልጤ አህጉረ ስብከት ሊቀጳጳስ እና የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ እንዲሁም የቅዱስ ሲኖዶስ አባል የሆኑት ብጹዕ አቡነ ቀሌምንጦንስ ብጹአን ሊቃነ ጳጳሳት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ እና መምሪያ ኃላፊ የሆኑት መምህር እንቁ ባህርይ ተከስተ እንዲሁም ከሊቃውንት ጉባኤ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያ ኃላፊዎች የሰንበት ትምህርት ቤቶች ጎብረት ተወካዮች እና በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤት ስራ አስፈጻሚዎች እና አባላት በተገኙበት የጥናት ውጤቱ ይቀርብ እና ማሳያ የሚሆነው ሥርዓተ ትምህርት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያው ስራውን በኃላፊነት ወስዶ እዛው ከተገኙት ተሰብሳቢዎች መካከል በሙያ የሚያግዙት አባላት ተመርጠው ከሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች አሁን እየተጠቀሙባቸው የሚገኘውን ሥርዓተ ትምህርት ለማሳያነት ከቀረበው ጋር በማመሳከር የመጨረሻ የእርማት እና የማደራጀት ስራ ከተሰራ በኋላ ስብሰባ ጠርቶ የደረሰበትን ውጤት ለሰንበት ትምህርት ቤት ተወካዮች ይቀርብ እና በሁሉም ተሳታፊዎች ይሁንታ ሲያገኝ ወደ ሊቃውንት ጉባኤ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በኩል ይቀርብ እና አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ አስተያየቱን ተቀብሎ የሚስተካከለውን ካስተካከለ በኋላ ለቅዱስ ሲኖዶስ አቅርቦ ያጸድቃል። እንደጸደቀ ማስመስከሪያ የሚሆኑ የልህቀት ማዕከላት ሰንበት ትምህርት ቤቶችን በምስራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ በአራቱም አቅጣጫ ለይቶ ለትራንስፖርት ያላቸውን ምቹነት ለማስተማር ከመማሪያ ቦታ ምቾት ከመምህራን ብዛት እና የትምህርት ዝግጅት ብቃት አንጻር ታይቶ ይመረጣሉ እና ከ1ኛ ክፍል እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ሁሉም ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድ ዓይነት እና ለማሳያ በተሰራው ሥርዓተ ትምህርት ላይ እንደተቀመጠው ሁለቱን ትምህርቶች እና የልህቀት ትምህርቶችን(የአብነት ትምህርት ምስክሮችን) የልህቀት ማእከላቱን መ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ሰንበት ትምህርት ቤት ከማስተማር ልምድ፤ ከቦታው ለትራንስፖርት ምቹነት፤ ከመምህራን ብቃት ከቤተ መጻህፍት መደራጀት አንጻር አምስተኛ ማስመስከሪያ ሰንበት ትምህርት ቤት ይሆንና ቃሊቲአካባቢ ያሉት ወደጊዮርጊስ ፒያሳ ሳይመጡ እዛው አካባቢ ባለ የልህቀት ማዕከል ሰንበት ትምህርት ቤት እስከ 12ኛ ክፍል ተምረው ይጨርሱና 12ኛ ክፍል ላይ ከመጀመሪያው ዓመት ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ያሉትን ትምህርት እንደመውጫ ፈተና(exit exam) ተዘጋጅቶ በመለኪያ (እስታንዳርዱ) ላይ የተቀመጠውን የማለፊያ ነጥብ ካመጣ የልህቀት ማእከል የሆነው ሰንበት ትምህርት ቤት በቅዱስ ሲኖዶስ በተሰጠው ስልጣን ለእከሌ ከነሙሉ ጥቅሙ እና ግዴታው ጋር ይህንን ዲፕሎማ ሰጥቶታል የሚል ዲፕሎማ ይሰጠዋል ።ከዚያ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ይቀጥላል በነዚሁ የልህቀት ማእከላት እነዚህ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚባሉትም የቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርቶች ሲሆኑ እነዚህን በሚሰራላቸው ሥርዓተ ትምህርት እና በሚወስዱት የትምህርት ዘመን ልክ ለእያንዳንዱ ትምህርት ከሰርተፊኬት እስከ ዲፕሎማ ይሰጣሉ እነዚህም

1ኛ. ንባብ

2ኛ. ዜማ

3ኛ.ቅዳሴ

4ኛ.ቅኔ

5ኛ.አቋቋም

6ኛ.ብሉያት ትርጓሜ

7ኛ. ሐዲሳት ትርጓሜ

8ኛ. ሊቃውንት ትርጓሜ

9ኛ. መነኮሳት

10ኛ.የመዝሙር መገልገያ ንዋያተ ቅድሳት

11ኛ. መዝሙር

12ኛ.ቁምጽህፈት እናሥነ ሥዕል

ይሆናሉ የእነዚህ ዝርዝር ዓላማ ይዘት ማስተማሪያዘዴ ምዘና እና ግምገማ ዘዴ መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ የጊዜ ሰሌዳ አፈጻጸማቸውም የሚሰራ ይሆናል።

ቴክኒካዊ ጥናቱ

ቴክኒካዊ ጥናቱ በዝርዝር የሚሰራ ሲሆን እንደማሳያ ግን የሰው ኃይልን በተመለከተ

ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርት ለማስተማር

1ኛ. ቤተክርስቲያናችን ካሉዋት የአብነት ትምህርት ቤቶች በመምህርነት ያስመሰከረ(በጉባኤ የዋለ)ተፈትኖ

2ኛ.ቤተክርስቲያናችን ካሉዋት መንፈሳዊ ኮሌጆች ተመርቆ የወጣ ተፈትኖ

3ኛ ቤተክርስቲያናችን ካሉዋት የካህናት ማሰልጠኛ ተመርቆ የወጣ

4ኛ.በሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን የሚሰጠውን ተከታታይ ትምህርት ያለጉድለት በብቃት የጨረሰ ተፈትኖ

5ኛ.የቤተክርስቲያናችን አገልጋይ ካህን የሆነ

6ኛ.ከ5ዓመት በላይ በሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን በማስተማር ላይ ያለ ተፈትኖ

7ኛ.የግቢ ጉባኤያትን ትምህርት በሚገባ ተምሮ የጨረሰ ለዛም ምስክር ወረቀት የሚያመጣ ተፈትኖ የሚያስተምሩ ይሆናል

የገንዘብ ትንተና እና የገንዘብ ምንጭ

ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን እንደ ትምህርት ቤትነታቸው የሰንበት ትምህርት ቤቱን ትልቁን በጀት ለትምህርት መመደብ ይገባቸዋል

1.ከሌላ ደብር ለሚመጡ መምህራን ትራንስፖርት

2.ለአብነት መምህራኑ ደሞዝ ሳይበዛ

3.ቅዱሳት መጻህፍትን ለመግዛት

4.የትምህርት ማእከላትን እና ቤተ መጻህፍቶችን ለማደራጀት ገንዘብ ማውጣት ይገባቸዋል

5. ማስተማሪያ ቅዱሳት ሥዕላትን ለማሰራት

6. መጻህፍትእና ሽቶችን ለማዘጋጀት

<u>ሥርዓተ ትምህርቱ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረጉ ነገሮች እንደ ምንጭም ያገለገሉ</u>

1. መጽሐፍ ቅዱስ
2. አዋልድ መጻህፍት
3. የአብነት ትምህርት ቤቶቻችን የትምህርት ሥርዓት እና ትምህርት
4. ቤተክርስቲያናችን ያሉዋት የካህናት ማሰልጠኛዎች ሥርዓተ ትምህርት
5. ቤተክርስቲያናችን ያሉዋት መንፈሳዊ ኮሌጆች ሥርዓተ ትምህርት
6. የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ሥርዓተ ትምህርት መጻህፍት እና ሽቶች
7. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መሰረተ እምነት(ዶግማ) ቀኖና እና ትውፊት
8. ማኅበረ ቅዱሳን ለግቢ ጉባኤያት ያዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት
9. ማኅበረ ቅዱሳን ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ያዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት
10. የእድገት ሥነልቡና
11. ሥነ ትምህርት
12. ማኅበራዊ ሥነ ልቡና
13. ሥነ ማኅበረሰብ
14. የትምህርት ፍልስፍና
15. የትምህርት ሥነ ልቡና
16. የሀገሪቱ የአስኳላ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት
17. የምዕራባውያን የትምህርት ሥርዓት
18. የአኀት አብያተ ክርስቲያናት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት

19. በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት
20. በአዲስ አበባ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የመምህራን ልምድ
21. በአዲስ አበባ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶች
22. በሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ሥርዓተ ትምህርት እና አጠቃላይ ትምህርት ላይ የተጠኑ ጥናቶች እና የጥናት ውጤቶች እና መሰል ግብዓቶችን ተጠቅመናል

የገንዘብ ምንጩ

1ኛ.ሰንበት ተማሪው የሚያዋጣው ወርኃዊ አስተዋጽኦ

2ኛ. ገቢ መሰባሰቢያ መድረክ

3ኛ. ውጭ የሚኖሩ ሰንበት ተማሪዎች

4ኛ. ሰራተኛ የሆኑ ሰንበት ተማሪዎች የሚሰጡት መዋጮ

5ኛ በጎ አድራጊ ምዕመናን

6ኛ. ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት

7ኛ.ሰንበት ትምህርት ቤቶች እያንዳንዳቸው በአዲስ አበባ ብቻ የሚገኙት1000ብር በሰንበት ትምህርት ቤታቸው ቢያወጡ 168000ይመጣል ይህ ክፍለ ሀገር ላሉት ሰንበት ትምህርት ቤቶችም የሚበቃ መጻህፍት ማለት ሥርዓተ ትምህርቱን በመጽሐፍ መልክ ለማሳተም ያስችላል።

8ኛ. ሌሎች

ቁጥጥር እና ግምገማ

ቁጥጥር እና ግምገማን በተመለከተ በዋነኛነት የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት እና ትግበራውን የሚከታተለው የሚቆጣጠረው የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያው ሲሆን መምሪያው በሚያዋቅረው የቁጥጥር እና ክትትል ኮሚቴ አማካይነት በየሶስት ወይም በየስድስት ወሩ የሥርዓተ ትምህርት ትግበራ እና ቁጥጥር ኮሚቴው በየሰንበት ትምህርት ቤቶች እየተዘዋወረ የሚሰጡት ትምህርቶች በሥርዓተ ትምህርቱ መሰረት እየተሰጡ መሆኑን እና የመምህራኑን የማስተማር ብቃት የተማሪውን የእውቀት እና የህይወት ለውጥ በመከታተል የማስተካከያ እርምጃ ይሰጣል።

የእያንዳንዱ ሰንበት ትምህርት ቤት ሰበካ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ሥርዓተ ትምህርቱ ተሰጥቶት በቃለ አዋዲው መሰረት በአጥቢያው የሚሰጠውን ትምህርት የሚከታተል ይሆናል

ቀጣይ እቅድን በተመለከተ

የሥርዓተ ትምህርቱ ዕቅድ ማደራጀት ማሰራጨት በመጽሐፍ መልክ ማዘጋጀት እና ትግበራ እንዲሁም ግምገማ እና ቁጥጥርን በተመለከተ የሚዋቀረው ኮሚቴ እቅድ አዘጋጅቶ በእቅዱ መሰረት የሚተገብረው ይሆናል ቀድመን እንደገለጽነው ማሳያ የሚሆነው የአብነት ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት እና የፕሮጀክቱ ረቂቅም አብሮ የሚዘጋጅ ይሆናል።

ሰንበት ትምህርት ቤት ምንድነው

ሰንበት ትምህርት ቤት ህጻናት እና ወጣቶች ያለጾታ ልዩነት በሰንበት ቀናት እና አመቺ በሚሆንበት ቀናት ሁሉ ምዕመናን በቤተክርስቲያን ተገኝተው የቤተክርስቲያናችንን መሰረተ እምነት ሥርዓት እና ትውፊት እንዲሁም በጎ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን የሚማሩበት ክፍል እንደሆነ በ1986 ጸድቆ የወጣው ቃለ አዋዲ አንቀጽ21 ላይ ይገልጻል በዝርዝር ሲቀመጥም እንዲህ ይላል

ስለ ሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችበቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ደንብ እና መመሪያ እየተከታተለ የሰበካው ሰንበት ትምህርት ቤት ክፍልተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል።

1. የሰንበት ትምህርት ቤትን በሰበካው ቤተክርስቲያን ያቋቁማል ያደራጃል በሰበካው ከአራት እስከ ሰላሳ የእድሜ ክልል የሚገኙትን ወጣቶች ሰንበት ትምህርት ቤት አባላት እንዲሆኑ እና ዲያቆናት በመማር ቀሳውስት እና መምህራን በማስተማር በሰንበት ትምህርት ቤቱ እንዲሳተፉ ያደርጋል

2. ለህፃናት እና ለወጣቶች እንደ እድሜያቸው ክልል በመከፋፈል በማዕከል ደረጃ መሚወጣው ሥርዓተ ትምህርት መሰረት ትምህርት መሰጠቱን ይከታተላል

3. በሰንበት እና በሌሎችም ዓበይት በዓላት እና አመቺ ቀናት የዕለት እና የዓመት መርሐ ግብር በማውጣት የቤተክርስቲያን ህግ እና ሥርዓትን የጠበቀ ትምህርት የቅዳሴ ተሰጥኦ እና የቅዱሳት መጻህፍት ጥናት እንዲሰጥ ያደርጋል

4. ህጻናት እና ወጣቶች ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንዳይወጡ የቤተክርስቲያንን ህግ እና ሥርዓት እንዲያውቁ እና እንዲያከብሩ ግብረ ገብ እንዲሆኑ ከአስተዳደሩ ጋር በመተባበር በቅርብ እየተከታተለ ያስተባብራል ይመክራል ይቆጣጠራል

5. ለምዕመናን ትምህርትን የሚሰጡ መንፈሳዊ መዝሙራትን ---የዘወትር መርሐ ግብር ያዘጋጃል

6. ወጣቶች መንፈሳዊ እውቀታቸው እንዲዳብር ልዩልዩ መማሪያ መሳሪያዎች የሚገኙበት ቤተ መጻህፍት ያቁማል

7. ከሰንበት ተማሪዎች በበዓላትም ሆነ በአጋጣሚ ,--የሚያቀርቡትን መንፈሳዊ ዝግጅት በቅድሚያ ለሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አቅርበው ከተመረመረ እና ከተጠና በኋላ ሲፈቀድ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል አፈጻጸሙንም ይከታተላል

8. የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትያትርም ሆነ በማናቸውም ሁኔታ የሚሰበስቡት ገንዘብ ለአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ገንዘብ ቤት ገቢ ይሆናል ለሚያስፈልጋቸው ወጪ ጥናቱ ለአስተዳደር ጉባኤው ቀርቦ ሲፈቀድ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል

9. ቀሳውስት የንስሐ ልጆቻቸው ልጆች መንፈሳዊውን ትምህርት እንዲከታተሉ ወላጆችም ልጆቻቸው በሰንበት ትምህርት ቤት ተመዝግበው መንፈሳዊውን እውቀት እንዲቀስሙ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታቸው መሆኑን ያሳውቃል

10. የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች መንፈሳዊውን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ የቤተክርስቲያናችንን ሥርዓት እና ባህል በተከተለ ሁኔታ የመለያ ልብስ (ዩኒፎርም) እንዲዘጋጅላቸው ያደርጋል።

11. በሰበካ ጉባኤ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አካል ካልታወቀ እና በጽሑፍ ካልተፈቀደ በቀር በሰንበት ትምህርት ቤት ስም የአዳር መርሐ ግብር እንዳይደረግ በጥብቅ ይቆጣጠራል

12. ከስብከተ ወንጌል እና ከመንፈሳዊ ትምህርት ክፍሎች ጋር በመተባበር መምህራንን እየጋበዘ ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቃት እና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

በማለት የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ምንነት እና ተግባራት ይዘረዝራል።

በመሆኑም የሰንበት ትምህርት ቤቶች ዋነኛ ተግባራቸው በቃለ አዋዲው መሰረት ብቃት እና ጥራት ያለው ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት መስጠት በመሆኑ ያንን ለማድረግ ደግሞ ብቃት እና ጥራት ያለው በእድሜ የተከፋፈለ ሁሉንም ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ያካተተ ሥርዓተ ትምህርት ወሳኝ በመሆኑይህ ማሳያ የሚሆን ሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶዋል።

ሥርዓተ ትምህርት ምንድነው

ታይለር የተባለ ሰው ስለ ሥርተ ትምሀርት ምንነት ሲገልጽ ሥርዓተ ትምህርት

1.የተግባር ዕቅድ ነው

2.የተጻፈ መረጃ ነውብሎ ሲናገር ታባ የተባለ ምሁር ደግሞ ሥርዓተ ትምህርት ማለት

3.ግብ፤ዓላማ፤ይዘት፤ማስተማሪያ ዘዴ እና ምዘና እና ግምገማያለው ጽሑፍ (ነገር) ነው ብሎዋል

4.የተደራጀ መደበኛ ትምህርት ነው (ፕራት1980)

5.ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች የሚያቀርበው የትምህርት መርሐ ግብር ነው (ኢሲነር1975)ሌሎች ደግሞ

6.የታቀደ ይዘት ነው

7.የተወሰነ የትምህርት ውጤት እና ይዘት ነው

8.የማኅበሰቡን ባህል ማንጸባረቂያ መድረክ ነው

9.ልምድን ዓላማን የሚያመለክት ስራ ነው

10.የጎብረተሰቡን ዕሴት ክሂል ለመገንባት የሚጠቅም መሳሪያ ነው

11. ትምህርት ቤት ውስጥ የምንማረው ነገር ነው

12.የሚጠኑ የትምህርት ዓይነቶች ስብስብ ነው

13.ተማሪዎች የሚከተሉት የጥናት መርሐ ግብር ነው

14.የጥናት ስልት እና ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ ቦታ ያለው ማንኛውም ነገር ነው

15.በትምህርት ባለሙያ የሚታቀድ ማንኛውም ነገር ነው

16.የትምህርት ልምድ ነው

የሥርዓተ ትምህርት ሂደት

1. ማቀድ
2. ማደራጀት
3. ማሰራጨት
4. መተግበር
5. መገምገም
6. መከለስ

የሥርዓተ ትምህርት ዓይነቶች

1.የተጻፈ

2.ኢ መደበኛ የሆነ (ቤተሰብ አቻ ቡድን ጓደኛ)

3.መማሪያ መጻሕፍት ተኮር

4.ኤሌክትሮኒክስ በኢሜይል በኢንተርኔት የሚማሩበት

የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ

1. የተገለጸ ግብ ያለው
2. ዓላማ ያለው
3. ምክንያታዊ የሆነ
4. በቀላሉ የሚያግባባ
5. ተጠያቂነት ያለበት
6. የታቀደ
7. ውጤታማ እና ተከታታይ ምዘና ያለው
8. ውጤታማ አመራር ያለው
9. አስተማማኝ
10. ትርጉም ያለው

የሥርዓተ ትምህርት ዕቅድ ዝግጅት

1.የሁኔታ እና ፍላጎት ትንተና መስራት

2. ግብ ዓላማ እና ውጤትን ማስቀመጥ

3.ዋና ዋና የትምህርት ይዘቶችን ማስቀመጥ

4.የመምህሩን እና ተማሪዎችን ተግባራት ለይቶ መስቀመጥ

5.የማስተማሪያ ስልት እና ዘዴን ማስቀመጥ

6.ምዘና እና ግምገማ ዘዴን ማስቀመጥ

የሥርዓተ ትምህርት ስርጭት

1.የትምህርት መርሐ ግብርን ማሳወቅ እና ማደል

2.የትምህርት መሪ ማንዋል ዝግጅት እና ስርጭት

3.የመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት

4. ማስተማሪያ እቅድ ዝግጅት

ምዘናና ግምገማ ዘዴ

የትምህርት ምዘና እና ግምገማ የሚያስፈልገው ለሚከተሉት ምክያቶች ነው

1.ለማሻሻል በትምህርት ሂደት ችግሮች ካሉ እነዛን ለማሻሻል

2.የቦታ ምደባ ለማካሄድ ከ1ኛ ወደሁለተኛ ከፍል አልፈሃል ወድቀሃል ለማለት

3.ለመቆጣጠር ተማሪው በሚገባ እየተማረ ነው አይደለም ብሎ ለማለት

4. ለማበረታታት ጥሩ ውጤት ያመጣውን ለመሻለም ለመለየት

5.ለመደገፍ ዝቅተኛ ውጤት ያመጣውን ተጨማሪ ጊዜ ሰጥቶ ለመከለስ እና ለመርዳት

6.ችግር ለማውጣት ችግሩ ያለው መምህሩ ላይ ነው ትምህርቱ ላይ ነው ሥርዓተ ትምህርቱ ነው ብሎ ለመለየት

7.ለማነጻጸር ከአምና የዘንድሮን ከአንዱ ተማሪ የሌላውን

የምዘና መስፈርቶች

1.ዋጋ ያለው

2.ተከታታይነት ያለው

3.ዓላማ ተኮር የሆነ

4.ታማኝነት ያለው

5.ሁሉን አቀፍ የሆነ መሆን አለበት

የምዘና ዓይነቶች

1.መስፈርታዊ ምዘና (criterion reference) ውሱን መስፈርት በማውጣት

2. ውድድራዊ ምዘና (norm reference) ተማሪን በክፍል ውስጥ እርስ በእርስ በማወዳደር

የመማሪያ ማስተማሪያ ዘዴ

በዓለም ላይ ከ1ሺ በላይ የማስተማሪያ ዘዴዎች አንዳሉ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ ሁሉም የመማሪያ ማስተማሪያ ዘዴዎች ተማሪው ትምህርቱን በሚረዳው መጠን እንዲቀርብለት የሚያግዙ ሲሆኑ መምህሩ እንደሚያስተምረው ትምህርት እና እንደ ርእሰ ጉዳዩ የማስተማሪያ ዘዴውን ጥቅም እና ጉዳት ለይቶ ሊጠቀምበት ይገባል።የመማሪያ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ከእነሱም ውስጥ የተወሰነውን ማጎበረ ቅዱሳን ለግቢ ጉባኤ መምህራን ያዘጋጀው የመማሪያ ማስተማሪያ ዘዴ እና ምዘና እና ግምገማ ስልት ከተባለው መጽሐፍ የተወሰደውን የተወሰነ ክፍል እነሆ ማሳያ እንዲሆን

ሁሉም የማስተማሪያ ዘዴዎች የራሳቸው የሆነ ጥቅም እና ጉዳት አላቸው

1. በገለጻ የማስተማር ዘዴ
2. በውይይት የማስተማር ዘዴ
3. በማሳየት እና በገለጻ የማስተማር ዘዴ
4. በተግባር
5. በውይይት
6. በጥያቄ እና መልስ
7. በፕሮጀክት
8. በመስክ ስራ
9. በጭውውት
10. በሚና ጨዋታ
11. ሌሎች

መማር ማስተማር ዘዴዎችን ስንመርጥ ልናስወውል የሚገቡን ነገሮች

1የትምህርቱን ዓላማ

2የተማሪዎችን እድሜ እና ችሎታ ፍላጎት

3.የመምህሩ አቀራረብ

4. የተማሪዎች ብዛት

5. የትምህርቱ ይዘት

6. ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታ እና ለትምህርቱየተሰጠው ሰዓት

ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል

የመማር ማስተማር መርሖች

1.ትምህርቱን ከማኅበራዊ ወቅታዊ እና ዕለታዊ ህይወት ጋር የማያያዝ መርህ

2.ትምህርቱን በሥርዓተ ትምህርቱ መሰረት የማቅረብ መርህ

3.በተማሪዎች መካከል ልዩነት እንዳለ የመገንዘብ መርህ

4.የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የማቀዳጀት መርህ

5.ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱት አድርጎ የማቅረብ መርህ

6.ተማሪው የተማረውን ትምህርት እንዲናገር ወይም እንዲገልጽ የማድረግ መርህ

7.ትምህርትን ግልጽአድርጎ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ የማቅረብ መርህ

8.የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች በግልጽ የማስቀመጥ መርህ

9.ትምህርቱን ዘላቂነት እንዲኖረው የማድረግ መርህ

10.ጊዜን ገንዘብን ጉልበትን በአግባቡ የመጠቀም መርህ

ትምህርቶች በክፍለ ትምህርቶች ሲከፋፈሉ

ክፍላት	ቅዱሳት መጻሕፍትክፍል	ታሪክ ክፍል	ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ክፍል	ዜማና ቋንቋክፍል	የሃይማኖት ትምህርት ክፍል	ሥነ ጥበባት እና ጠቅላላ ትምህርት ክፍል	ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
1		የቤተ ክርስቲያን በዓላት	ክ.ሥ.ም.	ግእዝ1እና ዜማ			
2	የመ.ቅ.ጥ.የብሉይ ኪዳን ታሪክ	የቤተ ክርስቲያን ታሪክ	ክ.ሥ.ም.	ግእዝ2እና ዜማ	አዕማደ ምስጢር በጥያቄና መልስ		

3	የመ.ቅ.ጥ.የሐዲስ ኪዳን ታሪክ	የቤተ ክርስቲያን ታሪክ	ክ.ሥ.ም.	ግእዝ3እና ዜማ	ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንበ ጥያቄና መልስ		
4	መ.ቅ.ጥናትመግቢያ1	የቤተክርስቲያን ታሪክ	ክ.ሥ.ም.	ግእዝ4እና ዜማ	ትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ		
5	አዋልድ መጻህፍት	የቤ.ክ.ታሪክ መግቢያ	ክ.ሥ.ም.	ግእዝ5እናዜማ	ነገረ ማርያም		
6				ግእዝ6እናዜማ፣	ነገረ ቅዱሳን		ሥርዓተ ቅዳሴቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ፣
7	መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት	የቤ.ክ.ታሪክ በዓለም መግቢያ	ክ.ሥ.ም.	ግእዝ1	ትምህርተ ሃይማኖት		
8	የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ	የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. ታሪክ እና የቤ.ክ.ታ.በዓለ ም		ግእዝ2			ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን
9	የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ1	ትምህርተ አበው	ክርስቲያናዊ ህይወት	ግእዝ3		ፍልስፍና	ኦ.መ.እና ምስጢራዊ ሥርዓቱ
10	የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ2		ሐዋርያዊ ተልእኮ			የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርጥ ናት እና ምርምር ዘዴ፣ክርስት ና እና መገናኛ ብዙሀን	ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
11	ዕብራውያን		ኦ.የጾ.ት.እና	ሰዓታት		ሥነ ልቡና	አንጻራዊ

	መልእክትትርጓሜ		የልጆች አስተዳደግ				ትምህርተ መለኮት
12	የዮሐንስ ራዕይ ትርጓሜ		ኦ.የስብከት ዘዴ	አገባብ እና ቅኔ ሰዓታት2		ባህረ ሀሳብ	ሥርዓተ ቅዳሴ

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቶች ትምህርቶች ከቤተ ክርስቲያናችን የአብነት ትምህርቶች አንጻር</u>

1. ንባብ ቤት የግእዝ ንባብ ከአአትብ ገጽየ ጀምሮ፤ የዮሐንስ ወንጌል የቃል ጥናት ዳዊት
2. ዜማ ቤት ውዳሴ ማርያም ዜማ
3. ቅዳሴ ቤት ሰዓታት ቅዳሴ
4. ቅኔ ቤት የግእዝ ግስ፤ የግእዝ ግስ እርባታ፤
5. ቅኔ አገባብ ሙያ ዜማ ልክ
6. አቋቋም ቤት ዝማሜ መዝሙራት ወረብ
7. ብሉያት ትርጓሜ ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ጥናት
8. ሐዲሳት ትርጓሜ ቤት የማቴዎስ ወንጌል፤የዮሐንስ ወንጌል፤ የዕብራውያን መልእክትየዮሐንስ ራዕይ

8.ሊቃውንትትርጓሜቤትሥርዓተቅዳሴ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም አቡሻህር

9.መነኮሳት ትርጓሜ ቤት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ

10.ቁት ጽህፈት እና ሥነ ሥዕል ትምህርተ ሃይማኖት ቤተክርስቲያንህን እወቅ

11.መዝሙር

12.የዜማ መገልገያ ንዋያተ ቅድሳት

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቶች የትምህርት ዓይነቶች</u>

1. ግእዝ
2. መዝሙር
3. ትምህርተ ሃይማኖት
4. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
5. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

6. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር
7. ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
8. ነገረ ማርያም
9. ነገረ ቅዱሳን
10. ነገረ ድኅነት
11. ሥነ ፍጥረት
12. ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን
13. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
14. ኦርቶዶክሳዊ የጾታ ትምህርት
15. ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ
16. ክርስትና እና መገናኛ ብዙሃን
17. ክርስቲያናዊ ሕይወት
18. የማቴዎስ ወንጌልትርጓሜ
19. የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ
20. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር
21. ሐዋርያዊ ተልእኮ(የአገልግሎት ትምህርት)
22. ሐዲሳት ትርጓሜ
23. ብሉያት ትርጓሜ
24. ግብረ ዲቁና
25. ንባብ
26. ዜማ
27. ቅኔ
28. አቋቋም
29. መጻህፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ
30. መጻህፍተ መነኮሳት ትርጓሜ

31. ባህረ ሃሳብ

32. ጥናትና ምርምር ዘዴ

33. ትምህርተ አበው

34. አንጻራዊ ትምህርተ መለኮት

35. ሥነ ልቡና

36. ፍልስፍና መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

እግዚአብሔር ቢፈቅድ እና ብንኖር ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ያዕ4፤15

የ2009ዓ.ም የትምህርት መርሐ ግብር እቅድ

መስከረም

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
1	2	3	4	5	6	7
8	9	10	11	12	13	14
15	16	17	18	19	20	21
22	23	24	25	26	27	28
29	30					

ጥቅምት

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
	1	2	3	4	5	
6	7	8	9	10	11	12
13	14	15	16	17	18	19
20	21	22	23	24	25	26

27 28 29 30

ህዳር

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
			1	2	3	
4	5	6	7	8	9	10
11	12	13	14	15	16	17
18	19	20	21	22	23	24
25	26	27	28	29	30	

ታህሳስ

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
					1	
2	3	4	5	6	7	8
9	10	11	12	13	14	15
16	17	18	19	20	21	22
23	24	25	26	27	28	29
30						

ጥር

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
	1	2	3	4	5	6
7	8	9	10	11	12	13

14 15 16 17 18 19 20

21 22 23 24 25 26 27

28 29 30

የካቲት

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
			1	2	3	4
5	6	7	8	9	10	11
12	13	14	15	16	17	18
19	20	21	22	23	24	25
26	27	28	29	30		

መጋቢት

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
				1	2	
3	4	5	6	7	8	9
10	11	12	13	14	15	16
17	18	19	20	21	22	23
24	25	26	27	28	29	30

ሚያዝያ

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
1	2	3	4	5	6	7
8	9	10	11	12	13	14
15	16	17	18	19	20	21
22	23	24	25	26	27	28
29	30					

ግንቦት

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
	1	2	3	4	5	
6	7	8	9	10	11	12
13	14	15	16	17	18	19
20	21	22	23	24	25	26
27	28	29	30			

ሰኔ

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
			1	2	3	
4	5	6	7	8	9	10
11	12	13	14	15	16	17
18	19	20	21	22	23	24
25	26	27	28	29	30	

ሐምሌ

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
					1	
2	3	4	5	6	7	8
9	10	11	12	13	14	15
16	17	18	19	20	21	22
23	24	25	26	27	28	29
30						

ነሐሴ

እሑድ	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዐርብ	ቅዳሜ
	1	2	3	4	5	6
7	8	9	10	11	12	13
14	15	16	17	18	19	20
21	22	23	24	25	26	27
28	29	30	1	2	3	4
5						

የበዓላት እና አጽዋማት ማውጫ

1ኛ.ዓመተ ዓለም 5500+2009እኩል ይሆናል 7509

2ኛ. ወንጌላዊ7509/4እኩል ይሆናል1877 ቀሪ1 ዘመኑ ዘመነ ማቴዎስ

3ኛ.እንቁጣጣሽ1877+7509/7 እኩል ይሆናል9386ቀሪ6 ዘመን መለወጫ እለቱ እሑድ

4ኛ.መደብ7500/19 እኩል ይሆናል395 ቀሪ4

5ኛ.ወንበር5500+2009/19እኩል ይሆናል395 ቀሪ4ስለዚህ1ለዘመኑ ስንሰጥ3ይቀራልስለዚህምወንበር3 ነው

6ኛ.አበቅቴ3(ወንበር)×11/30=3×19=57-30=27

7ኛ. የዕለት ተውሳክ2

8ኛ.መባጃ ሐመር ጥር 29

ዐቢይ ጾምየካቲት13ሰኞ

ደብረ ዘይት መጋት 10

ሆሳዕና ሚያዝያ1

ስቅለት ሚያዝያ6

ትንሳኤ ሚያዝያ8

ርክበ ካህናት ግንቦት 2

ጸራቅሊጦስ ግንቦት 27

ጾመ ሐዋርያት ግንቦት 28

ጾመ ድኅነት ግንቦት 30

የሥርዓተ ትምህርት መለኪያ

1.ግልጽ የትምህርት ፍልስፍና እና ተልእኮ ያለው

2.የግል እና የማኅበርን ሀላፊነት እና ተግባራት በግልጽ የሚያመላክት

3.የሥርዓተ ትምህርቱ ተግባራት በተግባሪዎቹ የተረዳ (የሚረዳ መሆን) አለበት

4.የታቀደ መርሀ ግብር ተከታታይነት ያለው ተግባር የጊዜ ገደብ ያለው ምዘናና ግምገማው የትምህርት ግቡን ለመተግበር የሚያስችል።

5.አስተዳደራዊ ድጋፍ የሚሰጠው ሰዓት በጀት ማንኛውም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚሟሉለት

6.በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የትምህርት ቤቱ አወቃቀር ሚያስፈልጉ ግብዓቶች የተመለከተበት

7.ማዕከላዊ የሥርዓተ ትምህርት ኮሚቴዎች ያሉት ኮሚቴዎቹም ባለሙያዎች የሆኑ

እኔ ባይ ተጠሪ እና ተቆጣጣሪ አስተባባሪ ያለው

8.የግል ተነሳሽነትን የሚያበረታታ እያንዳንዱ ሰንበት ትምህርት ቤት እና መምህር በግል ጥረቱ የሚያደርገውን የትምህርት ሥርዓት የሚደግፍ

9.የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ኮሚቴዎች ስራ በሂደት የሚሻሻል እና ሁሉም ተሳታፊዎች የሚስማሙበት የሚረኩበት መሆን

10.ከየትኛውም ትምህርት ቤት የሚመጣው ታሳቢ ረቂቅ ለሥርዓተ ትምህርቱ ግብዓት ማድረግ

11.አባላት የትምህርት ቤቱን ግብ በመቅረጽ ሂደት እንዲሳተፉ ማበረታታት

12.የሥርዓተ ትምህርቱ ግብ ወደ ትምህርት ቤቱ ፖሊሲ መቀየር የሚችል

13.የትምህርት ቤቱ አገልጋዮች (መምህራኑ) ለማርቀቅ፣ ለማሳደግ፣ ለመተግበር ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበት)

14.በሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ ሂደት የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን መምህራን ተሳታፊ የሚሆኑበትን እድል የሚሰጥ

15.ግልጽ የሆነ የቃል እና የጽሑፍ ግንኙነት በሁሉም ያገባኛል ባይ አባላት ዘንድ ያለው

16.የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅቱ የተማሪዎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባ

17ሙከራ እና ተግባራዊ ጥናት በቅንጅት በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ተግባራዊ የሆነበት

18.ምዘና እና ግምገማው የሥርዓተ ትምህርቱን ውጤታማነት የሚለካ መሆኑ

19.ዓላማ እና ግቡ ሁሉንም ባለ ድርሻ አካላት ሊያግባባ የሚችል

20.የተቀናጀ የመሪዎች ስራ ለግብ ማጥሪያነት የሚረዳ

21.አዳዲስ የመማሪያ ነገሮች መጻህፍትን መፍጠር፣ወቅታዊ ስብሰባዎች የትምህርት ቤት ጉብኝት ቁጥጥር የተደረገበት

22.የሥርዓተ ትምህርት መሻሻል የአመለካከት፣የአቀባበል፣የእሴት እና የመረዳት እንዲሁም የክሂሎት ለውጥ ማምጣት የሚችል

23.ዓላማው በሁሉም ደረጃ እና ክፍለ ትምህርቶች የተማሪዎችን ባህርይ ያማከለ ሆኖ የተጻፈ

<u>እነዚህ ከላይ የተቀመጡት መለኪያዎች</u>

1.ማስተዳደር መተንተን የሚያስችሉ መሆን አለባቸው

2.ሁለገብ ሁሉን አቀፍ መሆን አለበት

3.መስፈርቶቹ ወሳኝ፣ጠቃሚ እና የሚታዩ መሆን አለባቸው

4.ጠንከር ያለ ስምምነት በሁሉም ዘንድ ያለው

5.ፍላጎት ዋነኛ መረጋገጫ ነው የሚመራውም ደግሞ በማዕከላዊ መምሪያ ይሆናል

6.የትምህርት ቤቶቻችን መጠን እና መገኛ ቦታዎች እና መዋቅር የሥርዓተ ትምህርቱን ማዕከላዊ መሆኑን

የሚመዝኑ ናቸው

7.ባህርያዊ ዓላማ የወደፊቱን የሥርዓተ ትምህርት መልክ የሚወስን ነው

8.የተማሪዎችን ፍላጎት ለማወቅ የሚደረግ ፍተሸ ትንተና ጥናት ወጪ የሚጠይቁ ነገሮች ናቸው

እነዚህ መስፈርቶች የትምህርት ቤቶቻችንን የትምህርት ሥርዓት የሚወስኑ ናቸው

የልህቀት ማእከላት መምረጫ መለኪያ

መማሪያ ክፍልን በተመለከተ

1.ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከ12 ክፍሎች ቢያንስ 6 የመማሪያ ክፍል ያለው

2.ለማስተማሪያ የሚያስፈልጉ ጥቁር እና ነጭ ሰሌዳ ኮምፒውተር፣ፕሮጀክተር እንዳስፈላጊነቱ ያለው

3.ለመማሪያ የሚያስፈልጉ ወንበር ጠረጴዛ ያሉት

4.ቤተክርስቲያኑ የራሱ የሆነ የአስኳላ ትምህርት ቤት ያለው እሱንም መጠቀም የሚቻል

5.መማሪያ ክፍሎቹ ለመማር ማስተማር ሂደት የሚመች በቂ ብርሃን እና ነፋስ የሚገባበት

6.አንዱ ክፍል በአማካኝ አርባ ተማሪ ማስተማር የሚያስችል

7.በቤተክርስቲያኑ ቅጥረ ግቢ በሚገኝ ገረገራ ለመማር የሚያውክ ነገር የሌለበት

8.የመማሪያ ክፍሉ ከሽታ እና ሽታ ሊያመጡ ከሚችሉ ነገሮች የጸዳ

9.በየጊዜው በቀላሉ ለማጽዳት የሚያስችል ወለል ያለው

10.ለተማሪዎች ለመማር ማስተማር ምቾት ያለው

መምህራኑን በተመለከተ

1.የአብነት ትምህርት ተምረው ማስተማር የሚችሉ መምህራን ያሉት

2.በመንፈሳዊ ኮሌጅ የሚሰጡ ትምህርቶችን ተምረው የተመረቁ መምህራን ያሉት

3. የሰንበት ትምህርት ቤቱን ትምህርት መምህራኑ ከ5ዓመት በላይ በማስተማር የቆዩ

4. የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ትምህርት በሚገባ ተምረው የጨረሱ መምህራን ያሉት

5.ቤተክርስቲያናችን ካልዋት የካህናት ማሰልጠኛዎች ተምረው የጨረሱ ተፈትነው

6.ከ1ኛ ክፍል እስከ 6ኛ ክፍል ላሉት ተማሪዎች ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የካልዓይን ትምህርት የጨረሰ

7.ከ1ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ለማስተማር በቂና ጥሩ ዝግጅት ያላቸው መምህራን ያሉት

8.እውቀትና ህይወቱን ሰንበት ተማሪዎች የመሰከሩለት

9. ሰንበት ትምህርት ቤቱ በቂ መምህራን ከሌሉት ከአቻ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እና መንፈሳዊ ኮሌጆቻችን በማስመጣት እንዲያስተምሩ ማድረግ የሚችል

10. በአስኳላ ትምህርት መምህር የሆነ እና የሚያስተምረውን ትምህርት በሚገባ የሚያውቀው ለተወሰኑ ትምህርቶች ብቻ

<u>የሰንበት ትምህርት ቤቱን አደረጃጀት በተመለከተ</u>

1.የተደራጀ ክፍለ ትምህርት ያሉት

2.በቂ ተማሪዎች ያሉት

3.በቀን በማታ በክረምት በበጋ በርቀት እና በተከታታይ ለማስተማር የሚያስችል አቅም ያለው

4.የተደራጀ መዋቅር ያለው

5.ከቤተክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ እና ስብከተ ወንጌል ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ያለው

6.የሰንበት ትምህርት ቤቱ ስራ አስፈጻሚዎች ሰንበት ትምህርት ቤቱን ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም ያላቸው

7.ቤተክርስቲያኑ ለትራንስፖርት ምቹ የሆነ ማእከላዊ ቦታ

8.የጸጥታ ስጋት የሌለበት በቀን በማታ ትራንስፖርት የሚገኝበት

9.ከሚረብሹ እንደ ጋራጅ፣ ሙዚቃ ቤት ፣ወፍጮ ቤት ከመሳሰሉት ነገሮች የራቀ

10.ጽሕፈት ቤት ከነጽህፈት ቤት ቁሳቁስ የተሟሉለት

11.የትምህርት ማእከል ንዋያተ ቅድሳት ለማስቀመጥ ለመስራት የሚስችል ቦታ እና ዝግጅት ያለው

12.ከሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ጎብረት እና ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ እና መምሪያ ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ያለው።

የሥርዓተ ትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማው

የቤተክርስቲያናችንን መሰረተ እምነት (ዶግማ)

ሥርዓት (ቀኖና) እና የቤተ ክርስቲያናችንን ባህል (ትውፊት) እንዲያውቁ እና እንዲጠብቁ ማድረግ ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማሳካት ደግሞ የሚሰጡትን ትምህርቶች በሙሉ በእነዚህ ሶስት መሰረታዊ ዓላማዎች ማጠር አስፈላጊ ነው ሁሉም ትምህርቶች ከዚህ ዓላማ በምንም መልኩ አይወጣም::

ከዚህም በተያየዘ በእያንዳንዱ ክፍል በሚማሩት ትምህርት የማያውቁትን አዲስ እውቀት ያውቃሉ በተማሩት ትምህርት የግንዛቤ ለውጥ ያመጣሉ የተማሩትን ትምህርት በተግባር ይገልጣሉ ይህ እውቀታዊ አእምሮዓዊ እና ትግበራን ያማከለ እንዲሆን መምህራኑ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በእግዚአብሔር ቸርነት ታግዘው ሊያደርጉ ይገባል።

ተማሪዎች ከእያንዳንዱ ትምህርት በኋላ እንዲያመጡ የሚፈለገው ውጤት

አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንደጨረሱ

1ኛ.ስለቤተክርስቲያናችን በዓላት መጠነኛ ግንዛቤ ኖሮዋቸው ስለበዓላቱ ይገልጻሉ

2ኛ.ቤተክርስቲያን በመምጣት ያስቀድሳሉይቆርባሉ

3ኛ.የግእዝ ፊደላትን እና ቁጥሮችን በሚገባ በመጠናቸው በተማሩት መሰረት ያውቃሉ ያነባሉ

4ኛ.የቤተክርስቲያንን መዝሙራት ወቅቱን ጠብቀው በኦርቶዶክሳዊ ወዝ በአውደ ምሕረት እና በቤታቸው ይዘምራሉ።

በአጠቃላይ ህጻናቱ በሥዕላዊ መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስን እውቀት በመጠኑ የተገነዘቡ የቤተክርስቲያንን ልሳን ግእዝን ንባብን እና የመጀመሪያውን የቃል ትምህርት ይዘው የሚደግሙ በመልካም ሥነ ምግባር የታነጹ ይሆናሉ

ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንደጨረሱ

1. ስለ ሥነ ፍጥረት አምስቱም አእማደ ምስጢር፤ነገረ ማርያም እና ነገረ ቅዱሳን በጥያቄና መልስ ይረዳሉ ሲጠየቁ ይመልሳሉ።
2. ነጠላ ትእምርተ መስቀል ለብሰው ቤተክርስቲያን ይመጣሉ ይቆርባሉ ለቤተሰባቸው ይታዘዛሉ

3. በቃላቸው በግእዝ ቋንቋ አቡነ ዘበሰማያት እና ሰላም ለኪን ያደርሳሉ ይጸልያሉ
4. የግእዝ መዝሙራትን ኦርቶዶክሳዊ ወዛቸውን ጠብቀው ቤተክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ ያቀርባሉ ቤታቸውም ይዘምራሉ።
5. በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፉትን የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ተረድተው ይተርካሉ
6. የቤተክርስቲያንን ዓበይት በዓላት ታሪክ አውቀው ያከብራሉ ለምን እንደምናከብር ሲጠየቁ ይናገራሉ
7. የዮሐንስ መልእክትን በሚገባ ያነባሉ

<u>ሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተምረው እንደጨረሱ</u>

1ኛ.ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን በጥያቄና መልስ በቃላቸው ይይዛሉ

2ኛ.ውዳሴ ማርያምን በግእዝ እስከ ረቡእ ድረስ ይይዛሉ ይጸልያሉ

3ኛ.አጫጭር የግእዝ መዝሙራትን በቃላቸው በማጥናት በአውደ ምሕረት ላይ ይዘምራሉ

4ኛ. የሐዲስ ኪዳንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከጌታችን ጽንሰት እስከ እርገቱ በመማር ሲጠየቁ ይመልሳሉ ያስረዳሉ

5ኛ.የቤተክርስቲያንን ዓበይት በዓላት ታሪክ አውቀው ያከብራሉ ለምን እንደምናከብር ሲጠየቁ ይናገራሉ

6ኛ.የዮሐንስን ወንጌል ሥርዓተ ንባቡን ተከትለው እስከ ደረሱበት ድረስ ያነባሉ

7ኛ.በሁሉም ቦታ በጎ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ያሳያሉ

<u>አራተኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተምረው እንደጨረሱ</u>

1. የዮሐንስን ወንጌል ሥርዓተ ንባቡን ተከትለው ያነባሉ
2. ውዳሴ ማርያምን አንቀጸብርሃንን በቃላቸው ይዘው ያደርሳሉ ይጸልያሉ ይቀበላሉ ያድላሉ
3. አጫጭር የግእዝ መዝሙራትን አጥንተው ይዘምራሉ
4. ስለ ሃይማኖት ምንነት ፣ ስለ መሰረተ እምነት፣ቀኖና እና ትውፊት፣የእግዚአብሔር ባህርያት ተምረው ሲጠየቁ ይናገራሉ
5. ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምንነት የት መጣውን ጸሐፍቱን የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴን አውቀው ያጠናሉ መጽሐፍ ቅዱስን ያነባሉ
6. ስለመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ተምረው በህይወታቸው ያሳያሉ
7. ስለ ቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ያብራራሉ

<u>አምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተምረው እንደጨረሱ</u>

1. ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለሚጠየቁት ጥያቄ ኦርቶዶክሳዊ መልስ ይሰጣሉ
2. ስለአዋልድ መጻህፍት ምንነት ዓይነት ያብራራሉ አዋልድ መጻህፍትን ያነባሉ
3. ቤተክርስቲያን ከዓለመ መላእክት ጀምሮ እኛ ዘንድ እንዴት እንደ ደረሰች ይመሰክራሉ
4. የብጹዓንን ትምህርት ተምረው ብጹእ የሚያሰኛቸውን ስራ ይሰራሉ ቃላተ ወንጌልን በስራ ይገልጣሉ
5. ውዳሴ ማርያምን ከሰኞ እስከ ረቡእ ድረስ በዜማ ያደርሳሉ
6. መልክዓ ማርያምን በቃላቸው ይዘው ያደርሳሉ ያድላሉ ይቀበላሉ
7. ዮሐንስ ወንጌልን ያነባሉ ስለ ግእዝ ሰዋስው መጠነኛ ግንዛቤ ይይዛሉ

ስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንደጨረሱ

1.ነገረ ቅዱሳንን በሚገባ ተረድተው በቅዱሳን መንገድ ይኖራሉ

2.ኦርቶዶክሳዊ የጾታ ትምህርት ተምረው ራሳቸውን በንጽህና በድንግልና ጠብቀው ይኖራሉ

3.ቅዳሴ ተሰጥኦ ተምረው ቤተክርስቲያን በመገኘት ተሰጥኦ ይመልሳሉ

4.የቤተክርስቲያንን ንዋያተ ቅድሳት በክብር ይጠብቃሉ በቅዳሴ ወቅት ዲያቆናትን ጠበል በመቅዳት በማስተናበር ይራዳሉ

5.ውዳሴ ማርያምን እና መሐረነ አብን በዜማ ተምረው ሰርክ ላይ በሰንበት ትምህርት ቤታቸው ያደርሳሉ

6.መልክአ ኢየሱስን በቃላቸው ይዘው ያደርሳሉ ያድላሉ ይቀበላሉ

7.ዮሐንስ ወንጌልን መዝሙረ ዳዊትን ያነባሉ ስለ ግእዝ ሰዋስው መጠነኛ ግንዛቤ ይይዛሉ

ሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተምረው እንደጨረሱ

1.የቤተክርስቲያንን መሰረተ እምነት አውቀው ለሚጠየቁት ሁሉ ኦርቶዶክሳዊ መልስ ይሰጣሉ ራሳቸውን ከምንፍቅና እና ከክህደት ትምህርት ይጠብቃሉ

2.የመጽሐፍ ቅዱስን ምንነት የት መጣውን መቼቱን ባህሉን እና አዋልድ መጻሕፍትን 81ን መጻሕፍት አውቀው ከእነሱ በሚገኝ እውቀት እና ሕይወት ራሳቸውን ያንጻሉ

3.የቤተክርስቲያንን ታሪክ ከዓለመ መላእክት ጀምሮ እኛ ዘንድ እንዴት ልትደርስ እንደቻለች ያስረዳሉ

4፣የሥነ ምግባር ህግጋት እና መመሪያዎችን በመረዳት ራሳቸውን በበጎ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ያንጻሉ ንስሐ በመግባት በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ይኖራሉ

5.ስለ ግእዝ ምንነት የትመጣውን ጥቅሙን በማወቅ የግእዝ መጻህፍትን ለማንበብ ይሞክራሉ

ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1. ቤተክርስቲያናችን ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ እኛ ዘንድ እንዴት እንደ ደረሰች ተረድተው ቤተክርስቲያን በዘመናት

ሁሉ የሚገጥማት ፈተናን እንዴት በኃይለ እግዚአብሔር እንዳለፈችው በመረዳት ለቤተክርስቲያናችን ችግሮች እና ፈተና የመፍትሄ አካል ይሆናሉ

2. የቤተክርስቲያናችንን የትርጓሜ ስልት አውቀው የትርጓሜ መጻህፍትን በማንበብ ማስተማር ይችላሉ

3. ሰባቱን ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በመረዳት የምስጢራተ ቤተክርስቲያን ተሳታፊ ይሆናሉ ንስሐ ገብተው ይቆርባሉ ሥርዓተ ጋብቻቸውን በቤተክርስቲያን ሥርዓት መሰረት ይፈጽማሉ ካህናትን ያከብራሉ ወደ ክህነት ማዕረግ ተምረው ይመጣሉ

4. የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ/በዘመናት ሁሉ የገጠማትን ችግሮች በመረዳት ራሳቸውን እና ቤተክርስቲያናቸውን ከሚመጣባቸው ፈተና ሁሉ ይጠብቃሉይከላከላሉ

5. መሰረታዊ የግእዝ ቋንቋን በማወቅ በግእዝ ሰላምታ ይሰጣሉ የግእዝ መጽሐፍ በአቅማቸው ያነባሉ

<u>ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተምረው እንደጨረሱ</u>

1. የግእዝን ሰዋስው በማወቅ የግእዝ ግስን ማርባት ግስን መዘርዘር ይችላሉ
2. ስለቀደምት የቤተክርስቲያናችን አበው በማወቅ እምነት ትምህርታቸውን ተከትለው ያስተምራሉ
3. ስለእውነተኛ መንፈሳዊነት ተረድተው በኑሮዋቸው ሁሉ እውነተኛ ክርስትናን ያሳያሉ
4. ኦርቶዶክሳዊ መዝሙራትን ኦርቶዶክሳዊ ወዝ ከራቃቸው ለይተው ይዘምራሉ ገዛሉ
5. ስለሃይማት እና ፍልስፍና ጠንቅቀው አውቀው ከስጋዊ ፍልስፍና ተጠብቀው በሃይማኖት ራሳቸውን ያንጻሉ
6. በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተገለጡትን የትርጓሜ ትምህርቶች ያብራራሉ

<u>አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተምረው እንደጨረሱ</u>

1.ቤተክርስቲያንን አውቀዋት በቤተክርስቲያን መዋቅር ውስጥ በመግባት ከዲቁና እስከ መምህርነት ደርሰው ቤተክርስቲያንን ያገለግላሉ

2. የተለያዩ የትርጓሜ ሥልቶችን በመረዳት የትርጓሜ መጻሕፍትን ያነባሉ

3. ግእዝ ግስን አጥንተው ያረባሉ፣ ዐረፍተ ነገር ይሰራሉ፣ ይተረጉማሉ

4.ጥናትና ምርምር ዘዴን ተምረው በቤተክርስቲያን ዙሪያ ጥናት ያጠናሉ

5.ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ተምረው አውቀው ጠብቀው ያስጠብቃሉ ያስተምራሉ

6. መገናኛ ብዙኃን በክርስትናችን ላይ ያለውን በጎም ክፉ ተጽእኖ አውቀው ከክፉ ተጽእኖ ይርቃሉ

<u>አስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ</u>

1.በቤተክርስቲያን ማንኛውም አገልግሎት ላይ ይሳተፋሉ

2.በዕብራውያን መልእክት ላይ ያሉ ጥያቄዎችን በትርጓሜ ይመልሳሉ

3.የምናምነውን እምነት ትክክለኛነት ከሌሎች ቤተ እምነቶች አንጻር መዝነው ይረዳሉ ያስረዳሉ

4.ራሳቸውን ካላስፈላጊ የጾታ ግንኙነት ይጠብቃሉ በድንግልና በመኖር የህይወት አቅጣጫቸውን ይወስናሉ ልጆቻቸውን በኦርቶዶክሳዊ አስተዳደግ ያሳድጋሉ

5. ሰዓታት ተምረው በቤተክርስቲያን ይቆማሉ. ጠዋት ጠዋት ተፈሲሒታን እና መልክአ ሥዕልን ያደርሳሉ

6.የሰዎችን ሥነልቡና በተለይ በመንፈሳዊ መንገድ በመረዳት ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ይኖራሉ

አስራ ሁለተኛ ክፍልተማሪዎች ትምህርታቸውን እንደጨረሱ

1.ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ ተምረው ቅዳሴ በማስቀደስ ተሰጥኦ በመመለስ በማስተናበር በማስተማር ያገለግላሉ

2.የዮሐንስ ራዕይን ትርጓሜ አጥንተው ይተረጉማሉ

3. የግእዝን ሰዋስው በማጥናት ቅኔ ይቀኛሉ ይተረጉማሉ

4.ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴን ተምረው ይሰብካሉ

5. ሰዓታትን በማጠናቀቅ በቤተክርስቲያን ያደርሳሉ።

የክፍላት እና የትምህርቶቹ ስርጭት

1ኛ ክፍል (ህጻናት አንድ)

እድሜያቸው ከ6-8ዓመት የሆናቸው በክፍል ደረጃ ከመዋዕለ ህጻናት እስከ አራተኛ ክፍል

በሳምንት ለ3 ሰዓት በቀን1፤30ሰዓት ይማራሉ እያንዳንዱን ትምህርት ለ40 ደቂቃ ያህል ይማራሉ በሳምንት ሁለት ቀን ብቻ ይማራሉ በአጠቃላይ አራት የትምህርት ዓይነቶችን ሲማሩ ሁሉም ዓመቱን ሙሉ የሚዘልቁ ይሆናሉ።

የትምህርት ዓይነቶቹም

1.ዜማ (መዝሙር) አጫጭር የግእዝ መዝሙራት

2.ግእዝ (ንባብ አአትብ ገጽየ እስከ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም)

3.ሥነ ምግባር (ተግባራዊ ክርስትና ነጠላ መልበስ...)

4.የቤተ ክርስቲያን ታሪክ (የቤተ ክርስቲያናችን ዓበይት በዓላት)

ሁሉም ትምህርቶች ዓመቱን ሙሉየሚማሩት ሲሆን እያንዳንዱ ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ይሆናል አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማ ዝርዝር ይዘት የሚወስደው ደቂቃ ማስማሪያ ዘዴ መርጃ መሳሪያ ምዘና እና ግምገማ ስልት በዝርዝር ይሰራል።

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ህጻናት አንድ(አንደኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

በዚህ ክፍል የሚማሩ ህጻናት ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1.ስለቤተክርስቲያናቸው ክብር ቅድስና ያውቃሉ

2. ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መግባት እንዳለባቸው ይገነዘባሉ

3. ቤተክርስቲያን ሲመጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዴት በውስጥዋ መስገድ እንዳለባቸው አውቀው ይሰግዳሉ

4.ወደቤተክርስቲያን እየመጡ ይቆርባሉ ቅዳሴ ያስቀድሳሉ ቤታቸው ጸሎት ይጸልያሉ።

5. ለችግረኞች ምጽዋት ይሰጣሉ በዓላትን ከባልንጀሮቻቸው ጋር ያከብራሉ

6.ምግብ ሲበሉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በማወቅ አማትበው እና ጸልየው ይመገባሉ።

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ለህጻናት አንድ (አንደኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት

መስከረም1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለ ትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ነጠላ ትእምርተ መስቀል አጣፍቶ ስለመልበስ ስናማትብ እና ቤተክርስቲያን ስንገባ ስለምንለው ነገር ያዕቆብ ኤፍሬምና ምናሴንአመሳቅሎ እንደባረከ መተረክ

4ኛ ቤተ ክርስቲያን ስለ መምጣት ስግደት በቤተ ክርስቲያን ቅዱስጴጥሮስና ዮሐንስ የሐዋ3

ጥቅምት1ኛ ሳምንት በቤተክርስቲያን ምን መደረግ እንዳለበት ሳሙኤል

2ኛ ሳምንት በቤተክርስቲያን መደረግ የሌለበት መልአኩ ቅዱስ ቀውስጦስ ከቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ

3ኛ ሳምንት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉቅዱሳት ሥዕላትን መሳለም ሰሎሞን ነገ7

4ኛ ሳምንት በቤተክርስቲያን የካህናትን መስቀል መሳለም ባስልዮስ ዘቂሳርያ እና ኤፍሬም ሶርያዊ

ህዳር 1ኛ ሳምንት ስለቤተክርስቲያን አገልጋይ ካህናት የአሮን ክህነት በደብተራ ኦሪት

2ኛ ሳምንት ለሰው ሁሉ ስለመታዘዝ ይስሐቅ

3ኛ ሳምንት በመታዘዝ የሚገኝ በረከት ሙሴ ጸሊም

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ1ኛ ሳምንት በመታዘዛቸው በጎ ዋጋ ያገኙ ቅዱሳን ታሪክ አባ ህርያቆስ

2ኛ ሳምንት ስለ ትህትና እመቤታችን የትህትና አብነቶች

3ኛ ሳምንት ቤተሰብን ስለማገልገል ያዕቆብ

4ኛ ሳምንት ቤት ውስጥ ለወላጆቻችን እንዴት መታዘዝ እንዳለብን

ጥር1ኛ ሳምንት የታዛዥነት ዋጋ ኖኅ

2ኛ ሳምንት ጥሩ ልጅ ስለመሆን ቅዱስ አግናጥዮስ የልጅነት ታሪኩን ብቻ

3ኛ ሳምንት ስለ ጥሩ ጓደኝነት እና መጥፎ ጓደኝነት ዳዊትና ዮናታን የሮብአም ጓደኞች

4ኛ በትምህርት ውጤታማ ስለመሆን ቅዱሳት መጻህፍትን ስለማንበብ አባ አርሳንዮስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስለማንበቡ

የካቲት1ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

2ኛ ሳምንት ወላጆችን በስራ ስለመርዳት ጌታችን ለእመቤታችን እንደታዘዘ

3ኛ ሳምንት የጥሩ ልጅ ምሳሌዎች ሠለስቱ ደቂቅ በሃይማኖት ስለመጽናታቸው (ዮሴፍ)

4ኛ ሳምንትየመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ እና ፈተና

መጋቢት 1ኛ ሳምንት ስለ ትምህርት ሰዓት አጠቃቀም ዳንኤል የፀሎት ሰዓቱን ጠብቆ ጸሎት ስለማድረሱ

2ኛ ሳምንት ስለ ጸሎት ሰዓት ዳንኤል ነቢይ

3ኛ ሳምንት ቅዳሴ ስለማስቀደስ አባ ጳዊሊ ርእሰ መነኮሳት አቡነ ተክለሃይማኖት

4ኛ ሳምንት ከቅዳሴ ስለሚገኘው በረከት ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ በቅዳሴ ሰዓት ነአኩቶ ለአብ

ሚያዝያ1ኛ ሳምንት ስለ ቅዱስ ቁርባን አቡነ አሮን መንክራዊ ይምርሃነ ክርስቶስ

2ኛ ሳምንት እንዴት መቁረብ እንዳለብን

3ኛ ሳምንት ከቆረብን በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብን

4ኛ ሳምንት ክለሳ ስለ ቁርባን

ግንቦት1ኛሳምንት እንዴት መጸለይ እንደሚገባን ስለ ቀራጩ እና ፈሪሳዊው ጸሎት ሉቃ18

2ኛ ሳምንት ስለ ምን እንደምንጸልይማቴ6 አባታችን ሆይ ሉቃ1 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ

3ኛ ሳምንት ለምን እንደምንጸልይ የት እንደምንጸልይ የሳሙኤል እናት ሐና 1ሳሙ1

4ኛ ሳምንት የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና

ሰኔ1ኛ ሳምንት በዓላት ሃይማኖታዊ በዓላት ጥምቀት እና ደብረ ታቦር

2ኛ ሳምንት በዓላትን እንዴት እናክብራቸው

3ኛ ሳምንት በዓላትን ከቤተሰብ ከችግረኞች ጋር ስለማክበርሉቃ14

4ኛ ሳምንት በዓላት አከባበር በቤተክርስቲያን ልደተ እግዚእ እና ትንሳኤ

ሐምሌ1ኛ ሳምንት መዝሙር ስለመዘመር እንዴት እንደ ምንዘምር የመላእክት ዝማሬ በቤተ ልሄም እና በሰማይ ሉቃ2 እና ራእ4

2ኛ ሳምንት የመዝሙር ጥቅምጳውሎስ እና ሲላስ የሐዋ16

3ኛ ሳምንት የእምነት ጥቅም ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት ቬሮኒካ ማቴ9

4ኛ ሳምንት ስለ ተስፋ ስምኦን አረጋዊ

ነሐሴ 1ኛ ሳምንት ስለፍቅር ሰውን ሁሉ ስለመውደድ ዳዊት ጠላቱን ሳኦልን እንደወደደ

2ኛ ሳምንት የፍቅርን ትልቅነት አብነት በሚሆኑን ቅዱሳን ህይወት ቅድስት አርሴማ

3ኛ ሳምንት ክለሳ

4ኛ ሳምንት ማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

በገለጻ ማለት መምህሩ ስለትምህርቱ ለተማሪዎች በሚገባቸው መጠን ያስረዳቸዋል ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እና ለምን እንደምንመጣ መጥተን ስለምናደርገው ነገር ስንገባ ምን ብለን እንደ ምንሳለም በመጻፍ እና የተጻፈውን መላልሶ እንዲሉት በማድረግ

ሚና ጫወታ በመውሰድ ማለት አንድ ተማሪ እናት ሌላው አባት አንዱ ልጅ ሆነው በቤት ውስጥ ጸሎት እንዴት እንደሚመራ እና እንደሚጸለይ ወደ ቤተክርስቲያን እንዴት መምጣት እንደሚገባ በድራማ በማሳየት ወይም ከተማሪዎች ሁለቱን አውጥቶ ነጠላ እንዴት እንደሚለበስ እና እንዴት እንደሚሰገድ ምን እያልን እንደምንሰግድ በማሳየት ማስተማር።ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አኒሜሽን አዘጋጅቶ ወይም የተዘጋጀ አኒሜሽን ፊልም አምጥቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍቅዱስ

2. ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተዘጋጀ ማስተማሪያ መጽሐፍ

3.ከፍትሐ ነገስት

4.የቤተ ክርስቲያን ጸሎት

5.መርሐ ህይወት

6.ዓበይትሥነምግባራት

7.ክርስቲያናዊ ህይወት

8.ፍኖተ ቅዱሳን

9.ገድለ ቅድስት አርሴማ

10.ተዓምረ ኢየሱስ

11.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት ላይ ያገኘዋል

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ ተማሪዎች ሚለማመዱበት በመጠናቸው የተዘጋጀ ነጠላ

6.ስለ ዐበይት ሥነ ምግባር የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

7. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተማሩትን እንዲያሳዩ በማድረግ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት

6.ቤተክርስቲያን እየተገኙ መምጣት አለመምጣታቸውን ማስቀደስ አለማስቀደሳቸውን በማየት መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ30 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይ በዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናት ሳይቆጠሩ 40 ክፍለ ጊዜ ቢኖር 40ሲባዛ በ30 እኩል

ይሆናላ16 ሰዓት ይወስዳል።

ትምህርተ ግእዝ ለህጻናት አንድ(አንደኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው እንደጨረሱ

1.በቃላቸው ከአአትብ ገጽየ ጀምረው እስከ ሰላም ለኪ ድረስ በየቀኑ ያደርሳሉ

2.መርሐ ግብራቸውን በግእዝ ጸሎት ይከፍታሉ ይዘጋሉ

3.የግእዝ ቁጥሮችን ጠንቅቀው አውቀው በተጠየቁ ጊዜ ይመልሳሉ መጽሐፍ ቅዱስን ያለምንም የቁጥር ስህተት ማንበብ ይችላሉ።

4.ምግብ በልተው ስብሐት በግእዝ ያደርሳሉ

ትምህርተ ግእዝ ለህጻናት አንድ(አንደኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት

ዘወርኃ መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት አአትብ ገጽየ እና ነአኩተከ የግእዝ ፊደል ቀዳማውያን አበገደ

4ኛ ሳምንት ነአኩተከ የግእዝ ፊደላት ቀዳማውያን

ዘወርኃ ጥቅምት 1ኛ ሳምንት አቡነ ዘበሰማያት የግእዝ አኃዝ ከ1-20

2ኛ ሳምንተ አቡነ ዘበሰማያት የግእዝ አኃዝ ከ21-50

3ኛ ሳምንት አቡነ ዘበሰማያትየግእዝ አኃዝ ከ51-100

4ኛ ሳምንት አቡነ ዘበሰማያት የግእዝ አኃዝ ከ100-150

ዘወርኃ ህዳር 1ኛ ሳምንት በሰላመ ቅዱስገብርኤልመልአክ የግእዝ አኃዝ ከ150-200

2ኛ ሳምንት በሰላመ ቅዱስ ገብርኤልመልአክየግእዝ አኃዝ 200-250

3ኛ ሳምንት በሰላመ ቅዱስገብርኤልመልአክየግእዝ አኃዝ 250-300

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ዘታህሳስ1ኛ ሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት እስከ ወረደ እምሰማያት ድረስየግእዝ አኃዝ 300-350

2ኛሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት እስከ ወረደ እምሰማያት ድረስየግእዝ አኃዝ 350-400

3ኛ ሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት እስከ ወረደ እምሰማያት ድረስየግእዝ አኃዝ ከ400-450

4ኛ ሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት እስከ ወረደ እምሰማያት ድረስ የግእዝ አኃዝ ከ450-500

ዘጥር1ኛ ሳምንት ከተሰብአ ወተሰገወ እስከ ለዓለመ ዓለም ድረስየግእዝ አኃዝ ከ500-550

2ኛ ሳምንት ከ ተሰብአ ወተሰገወ እስከ ለዓለመ ዓለም ድረስየግእዝ አኃዝ ከ1-20550-600

3ኛ ሳምንት ከተሰብአ ወተሰገወ እስከ ለዓለመ ዓለም ድረስ የግእዝ አኃዝ ከ600-650

4ኛ ሳምንት ከተሰብአ ወተሰገወ እስከ ለዓለመ ዓለም ድረስየግእዝ አኃዝ ከ650-700

ዘወርኃ የካቲት 1ኛ ሳምንት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ

2ኛ.ሳምንት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

ዘወርሃ መጋቢት1ኛ ሳምንት እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

2ኛ ሳምንት እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

3ኛ ሳምንት እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

4ኛ ሳምንት እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ዘወርሃ ሚያዝያ1ኛ ሳምንት ክለሳ

2ኛ ሳምንት ስብሐት

3ኛ ሳምንት ስብሐት

4ኛ ሳምንት ስብሐት

ዘወርሃ ግንቦት 1ኛ ሳምንት ሰላም ለኪ

2ኛ ሳምንት ሰላም ለኪ

3ኛ ሳምንት ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም

4ኛ ሳምንት የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና

ዘወርኃሰኔ 1ኛ ሳምንት ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም

2ኛ ሳምንት ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም

3ኛ ሳምንት አአትብ ገጽየ ክለሳ

4ኛ ሳምንት ነአኩተከ ክለሳ

ሀምሌ1ኛ ሳምንት አቡነ ዘበሰማያት ክለሳ

2ኛ ሳምንት አቡነ ዘበሰማያት ክለሳ

3ኛ ሳምንት በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ክለሳ

4ኛ ሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት ክለሳ

ነሀሴ 1ኛ ሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት ክለሳ

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ቅዱስ ክለሳ

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ቅዱስ ክለሳ

4ኛ ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

ትምህርቱን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ስለ ትምህርት አሰጣጡ መምህሩ ለተማሪዎች በመግለጽ ከእኔ በኋላ በሉ በማለት ከእርሱ ቀጥለው ቃል በቃል በማስጠናት እንዲሁም እሱ ካለ በኋላ እንዲመልሱ በማድረግ፤ይሔንን በመደጋገም እስኪያሠርፁት በመመላለስ ተማሪዎች በቀኝ በግራ ወንድ እና ሴት እንዲመላልሱት በማድረግ፤ ከተማሪዎች መካከል ሁለት ሰው ወስዶ እንዲሉት በማድረግ ትምህርቱ መያዙን እስኪያረጋግጥ ድረስ መምህሩ መላልሶ መንገር ተማሪዎችም መላልሰው እንዲሉት በማድረግ ማስተማር ፤ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1.ከመዝገበ ጸሎት መጽሐፍ

2.ውዳሴ ማርያም በግእዝ

3.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት ላይ ያገኘዋል

4.ጥንታዊ ግእዝ በዘመናዊ አቀራረብ

<u>ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)</u>

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ(ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.የግእዝ ቁጥሮች የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

7. እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዥ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4. ከተማሪዎች አንዱን ድንገት ይኼንን በለው በማለት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይበዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናትሳይቆጠሩ 40 ክፍለጊዜ ቢኖር 40ሲባዛ በ40 እኩል ይሆናል16 ሰዓት ይወስዳል።

መዝሙር ለህጻናት አንድ (አንደኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

በዚህ ክፍል የዓመቱን ትምህርት ተምረው የሚጨርሱ ሰንበት ተማሪዎች በዓመቱ መጨረሻ

1ኛ.ከ48 ያላነሱ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ ኦርቶዶክሳዊ ወዛቸውን ያልለቀቁ መዝሙራትን አጥንተው ማቅረብ መዘመር ይችላሉ።

2ኛ.ትክክለኛውን መዝሙር ከዚህ እድሜያቸው ጀምረው ይመርጣሉ ይዘምራሉ

3ኛ. ሌላ መልክ ያለውን መዝሙር ይርቃሉም ያርቃሉም።

4ኛ.እዚህ ላይ ከቀረቡት መዝሙራት ውጪ እንደ አጥቢያቸው በደብራቸው ያለውን ታቦት መዝሙር ከሁለት ስንኝ ያልበለጠ አጥንተው ይዘምራሉ

<u>መዝሙር ለህጻናት አንድ (አንደኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት(መዝሙራት)</u>

ዘወርኃ መስከረም1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ዮም በዓለ መስቀሉ በሰማያት በላዕሉ

4ኛ ሳምንት በመስቀልከ ርድአነ

ዘወርኃ ጥቅምት 1ኛ ሳምንት እስከ ማእዜኑ እግዝእትየ

2ኛ ሳምንት ጴና አልባሲሁ

3ኛ ሳምንት ፊልጶስ ሐዋርያ

4ኛ ሳምንት እስመ አልብነ ረዳኢ

ዘወርኃ ህዳር 1ኛ ሳምንት ወመኑ መሐሪ ዘከማከ

2ኛ ሳምንት ባህራንኒ

3ኛ ሳምንት ንጽህተ ንጹሃን ከዊና፤

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና

ዘወርኃ ታህሳስ1ኛ ሳምንት ገብርኤም ምልአኒ

2ኛ ሳምንት ለዘተወልደ እምቅድስት

3ኛሳምንት ዮም ፍስሐ ኮነ

4ኛ ሳምንትመድኃኒነ ተወልደ ነዋ

ዘወርኃ ጥር1ኛ ሳምንት ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ

2ኛ ሳምንት በወንጌሉ ያመናችሁ 3ኛ.ሳምንት አስተርዮቱ

4ኛ ሳምንት ነአምን ክርስቶስሃ

ዘወርኃ የካቲት1ኛ ሳምንት መጽአ መርአዊ

2ኛ ሳምንት ካህናት ተንስኡ

3ኛ ሳምንት ማርያም ተዓቢ

4ኛ.ሳምንት የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና

ዘወርኃ መጋቢት 1ኛ ሳምንት ንጹም ጾመ

2ኛ ሳምንት ሆሳእና እምርት

3ኛ ሳምንት እም አፈ ደቂቅ

4ኛ ሳምንት ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ዘወርኃ ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት ትንሳኤከ

2ኛ ሳምንት አንትሙሰ ንበሩ

3ኛ ሳምንት ገድልከ ግሩም

4ኛ ሳምንት ያሬድ ፈልፈለ ማኅሌት

ዘወርኃ ግንቦት 1ኛ ሳምንት ኢያቄም ወሀና

2ኛ ሳምንት በመኑ በአምሳለ መኑ

3ኛ ሳምንት ኩሉ ዘፈቀደ

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት አጋማሽፈተና

ዘወርኃ ሰኔ 1ኛ ሳምንት ተዋህዶ ንጽህት

2ኛ ሳምንት ዘሰማየ ገብረ

3ኛ ሳምንት መድኃኔ ዓለም ወሀቤ ሰላም

4ኛ ሳምንት ተናገሩ ድንቅ ስራውን

ዘወርኃ ሐምሌ 1ኛ ሳምንት ሰአሉ ለነ ቅዱሳን

2ኛ ሳምንት ስብሐት ለአብ

3ኛሳምንት ኦ አንትሙ

4ኛ ሳምንት ጊዮርጊስ ኃያል

ዘወርኃ ነህሴ 1ኛ ሳምንት ሰላም ለኪ ማርያም

2ኛ ሳምንት በስመ ዚአከ ይትፌስሑ ዮም

3ኛ ሳምንት እምሄሶ ለሔሮድስ

4ኛ ሳምንት ማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

መዝሙራቱን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ በሽት አዘጋጅቶ በመስጠት ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ስለ መዝሙሩ አጠናን መምህሩ ለተማሪዎች በመግለጽ ከእኔ በኋላ በሉ በማለት ከእርሱ ቀጥለው ቃል በቃል እንዲሉ በማድረግ እና በማስጠናት እንዲሁም እንዲቀባበሉ በማድረግ፤ይሔንን በመደጋገም እስኪያሰርጹት በመመላለስ ተማሪዎች በቀኝ በግራ ወንድ እና ሴት እንዲሉት በማድረግ፤ ከተማሪዎች መካከል አንድ ሰው ወስዶ እንዲዘምረው በማድረግ ማስተማር ፤ወይም እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም መዝሙራቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1.መዝሙረ ማኅሌት (የሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ የመዝሙር መጽሐፍ)

2.የጽርሐ ጽዮን ኦርቶዶክሳዊ መዝሙር መጽሐፍ ቁጥር1 እና 2

3.የማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ሰንበት ትምህርት ቤት የመዝሙር መጽሐፍ

4.የደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ሰንበት ትምህርት ቤት የመዝሙር መጽሐፍ

5.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.ከበሮ ጸናጽል መቋሚያ

7.ተማሪዎች የሚያደርጉት ነጠላ (የሰንበት ተማሪዎች ልብስ)

8.እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር

ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እያዩ እንዲዘምሩ በማድረግ

2. የተጻፈውን በማጥፋት መዝሙሩን በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት መዝሙሩን በቃላቸው እንዲይዙት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን መዝሙራቱ እንዳይረሱ

5 በየወቅቱ ስላጠኑት መዝሙር ያለፈውን እንዲዘምሩ በማዘዝ መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ30 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይ በዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናትሳይቆጠሩ 40 ክፍለጊዜ ቢኖር 30ሲባዛ በ30 እኩል ይሆናላ12 ሰዓት ይወስዳል።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለህጻናት አንድ

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1. በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በዓመት ስለሚውሉ ዐበይት በዓላት ያውቃሉ።

2.በዓመት ውስጥ ያሉትን በዓላት ታሪክ ሲጠየቁ ይናገራሉ

3.በዓላቶቻችንን እና ትውፊታችንን ይጠብቃሉ ቅዱሳኑን ያከብራሉ

4.ክዱሳኑን በግብር ለመምሰል ይሞክራሉ የቅዱሳኑን የተጋድሎ ህይወት በሚገባ ይረዳሉ

<u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለህጻናት አንድዝርዝር ይዘት</u>

መስከረም 1ኛ ሳምንትየተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ስለ እንቁጣጣጭ ታሪካዊ አመጣጥ እንዲሁም ስለ ዮሐንስ መጥምቅ

4ኛ ሳምንት ስለ መስቀል እና ንግሥት እሌኒ

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ስለ አብርሃ እና አጽብሐ

2ኛ ሳምንት እመቤታችን በግብጽ ስደትዋ

3ኛ ሳምንት ስለ ቅዱስ ፊልጶስ እና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ባኮስ

4ኛ ሳምንት ስለ ቅዱስ ዮሐንስ ሐጺር

ህዳር 1ኛ ሳምንት ስለ እመቤታችን በደብረ ቁስቋም

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እድገት

3ኛ ሳምንት ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ባህራንን እንዳዳነው

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ1ኛ ሳምንት ኤልያስ እና ናቡቴ

2ኛሳምንት እመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ መግባትዋ

3ኛ ሳምንት ሠለስቱ ደቂቅ እና ቅዱስ ገብርኤል

4ኛ ሳምንት የጌታችን ልደት

ጥር 1ኛ ሳምንት የቅዱስ እስጢፋኖስ የዲቁና ህይወቱ

2ኛ ሳምንት በዓለ ጥምቀት

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት የልጅነት ህይወቱ

4ኛ ሳምንት የዶኪማስ ሰርግ

የካቲት 1ኛ ሳምንት ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ የልጅነት ህይወቱ

2ኛ ሳምንት እመቤታችን በጎለጎታ እና ቃል ኪዳንዋ

3ኛ ሳምንት ስምኦን አረጋዊ (ሙሴ)

4ኛየመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና

መጋቢት 1ኛ ሳምንት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕረፍታቸው

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ቄርሎስ የልጅነት ህይወቱ

3 ሳምንት ጌታችን የሐዋርያትን እግር ማጠቡ

4ኛ ሳምንት ብስራተ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ

ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር መፍታቱ

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ዘሲማስ በብሔረ ብጹአን

3ኛ ሳምንት ጌታችን ስቅለት እና የታዩ ተዓምራት

4ኛ ሳምንት የጌታችን ትንሳኤ

ግንቦት 1ኛ ሳምንት ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ከስምን ጫማ ሰፊው ጋር በግብጽ

2ኛሳምንት ልደታ ለእግዝእትነ ማርያም

3ኛ ሳምንት ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በልጅነቱ ከቅዱስ እለ እስክንድሮስ ጋር

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት አጋማሽፈተና

ሰኔ 1ኛ ሳምንት አቡነ ተክለ ሃይማኖት የልጅነት ታሪካቸው እና ዲቁና እንዴት እንደተቀበሉ

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያዊ እና አጼ ገብረ መስቀል

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ላሊበላ እና የሰራው ውቅር አብያተ ክርስቲያን

4ኛ ሳምንት ህንጻ ቤተ ክርስቲያን መሰራት

ሐምሌ1ኛ ሳምንት አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ የጸሎት ህይወት

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ጳውሎስ ያደረጉት ተዓምር ህመምተኛ ማዳናቸው

3ኛ ሳምንት ህጻኑ ቂርቆስ እና እናቱ ኢየሉጣ

4ኛሳምንት ቅድትስ እንባ መሪና

ነሐሴ 1ኛ ሳምንት በዓለ ደብረ ታቦር

2ኛ ሳምንት የእመቤታችን እርገት

3ኛ ቅድስት ቅድስት መስቀለ ክብራ

4ኛ ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

ትምህርቱን የሚገልጽ ከቅዱሳት ሥዕላት ቀድሞ አዘጋጅቶ መርጦ በሰንበት ትምህርት ቤቱ በበጀት አጸድቆ ወይም በጎ ሊያደርጉ ሚችሉ ምዕመናንን በማሳሰብ በመንገር ሥዕላቱን በዲጂታል ህትመት በማሳተም ሁሉም ተማሪ እንዲያየው በማድረግ ስለ ሥዕሉ ባለቤት ቢገልጹላቸው ትምህርቱ በቀላሉ ይረዳቸዋል ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ሥዕሉን በላፕቶፕ ማብራራት እንዲሁም ሥለ ሥዕሉ ባለቤት ከ6 መስመር ባልበለጠ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ሥዕሉን በመለጠፍ በ በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በኮምፒውተር ጽፎ አባዝቶ በመስጠት ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቢማሩ ትምህርቱ ማይረሳ ይሆናል እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ በማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍ ቅዱስ

2.ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ ያሉ የትርጓሜ መጻህፍት

3.ከውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ መጽሐፍ

4.ክብረ ነገሥት

5.ገድለ ዮሐንስ መጥምቅ

6. ድርሳነ መስቀል

7. ወንጌል ትርጓሜ

8.ነገረ ማርያም

9. የሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተማሪያ ያዘጋጀው መጽሐፍ

10.መርሐ ህይወት

11. ገድለ ጊዮርጊስ

12 ገድለ ማርያም ግብጻዊት እና ቅዱስ ዘሲማስ

13. ገድለ ተክለ ሃይማኖት

14.አራቱ ቅዱሳን ነገሥታት

15.ስንክሳር

16.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.ቅዱሳት ሥዕላት በሲዲ በፍላሽ በዲጅታል ህትመት

7.የታተመ ቅዱሳት ሥዕላት 2 በ2 የሆነ በውስጡ ከ5ያልበለጡ ከ5ያላነሱ ቅዱሳት ሥዕላት ያሉበት ባነር

8.ከቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ ፎቶ የተነሱ ቅዱሳንን ሚያሳዩ ቅዱሳት ሥዕላት

9ስለ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

10. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዥ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5. በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

6.በእለቱ የተማሩት ቅዱስ ማን እንደሚባል የስማቸው ትርጉም ምን እንደሆነ ታሪካቸውን እና ከታሪካቸው ምን እንደምንማር በቃል እና በጽሑፍ መጠየቅ

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይበዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናትሳይቆጠሩ 40 ክፍለጊዜ ቢኖር 40ሲባዛ በ40 እኩል ይሆናላ16 ሰዓት ይወስዳል።

ህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል)

እድሜያቸው ከ7-9ዓመት የሆናቸው በክፍል ደረጃ ከአንደኛ ክፍል እስከ አራተኛ ክፍል የሆኑ

በሳምንት ለ4 ሰዓት በቀን ለሁለት ሰዓት ይማራሉ

በአጠቃላይ ስድስት የትምህርት ዓይነቶችን ሲማሩ ሶስቱ ትምህርቶች ዓመቱን ሙሉ የሚዘልቁ ሲሆኑ ሶስቱ ግን በወሰነ ትምህርት የሚቀየሩ ይሆናሉ።

<u>የትምህርት ዓይነቶቹም</u>

1.ዜማ (መዝሙር) አጫጭር የግእዝ መዝሙራት

2.ግእዝ (ንባብ አአትብ ገጽየ እስከ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም)

3.ትምህርተ ሃይማኖት አዕማደ ምስጢራትን በጥያቄ እና መልስ

4.የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (ከሥነ ፍጥረት እስከ ነቢያት መነሳት ድረስ)

5.ሥነ ምግባር (ተግባራዊ ክርስትና ነጠላ መልበስ...

6.የቤተ ክርስቲያን ታሪክ (የቤተ ክርስቲያናችን ዓበይት በዓላት)

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዜማ እና ግእዝ ዓመቱን ሙሉ የሚሰጡ ሲሆኑ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በወሰነ ትምህርትየሚቀያየሩ ይሆናል

የትምህርቶቹ አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማ ዝርዝር ይዘት የሚወስደው ደቂቃ ማስማሪያ ዘዴ መርጃ መሳሪያ ምዘና እና ግምገማ ስልት በዝርዝር ይሰራል።

<u>ትምህርተ ሃይማኖት ለህጻናት ሁለት(ሁለተኛ ክፍል)</u>

<u>የትምህርቱ ዓላማ፤</u>

በዚህ ክፍል የሚማሩ ህጻናት ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1.እግዚአብሔር ፈጣሬ ዓለማት መሆኑን የፈጠራቸውን ፍጥረታት ያውቃሉ።

2.የእግዚአብሔርን አንድነት እና ልዩ ሶስትነት ሲጠየቁ ያብራራሉ፤

3.አዕማደ ምስጢራትን ከነጥቅማቸው መግለጽይችላሉ

4.ሰው በጥምቀት ሚያገኘውን ጥቅም ከቁርባንም እንዲሁ ይገልጻሉ

5.እንዴት መቁረብ እንዳለብን ይገልጻሉ

6.ሰው ሞቶ ፈርሶ በስብሶ እንደማይቀር እንደሚነሳ ያምናሉ ይናገራሉ፡

7.ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስና ምልጃ መግለጽ ይችላሉ ይገልጻሉ

8. ቅዱሳን እነማን እንደሆኑ እና ለምን ቅዱስ እንደተባሉ ያብራራሉ

<u>ትምህርተ ሃይማኖት ለህጻናት ሁለት(ሁለተኛ ክፍል) ዝርዝር ይዘት</u>

ዘወርኃመስከረም1ኛ ሳምንትየተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ሥነ ፍጥረት በጥያቄና መልስ

4ኛ ሳምንት ምስጢረ ሥላሴ በጥያቄና መልስ

ዘወርኃ ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ምስጢረ ሥላሴ ታሪክ አብርሃም ሥላሴን በእንግድነት መቀበሉ

2ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ሥላሴ ጥቅስ ጥናት

3ኛ ሳምንት ምሥጢረ ሥጋዌ በጥያቄና መልስ

4ኛ. ሳምንት ስለ ምስጢረ ሥጋዌ ታሪክ የክርስቶስ ልደት ታሪክ

ዘኅዳር1ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ስጋዌ ጥቅስ ጥናት

2ኛ ሳምንት ምስጢረ ጥምቀት በጥያቄና መልስ

3ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ጥምቀትታሪክ የጌታችን ጥምቀት ታሪክ በዮርዲያኖስ መጠመቁ

4ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ጥምቀት ጥቅስ ጥናት

ታህሳስ1ኛ ሳምንት ምስጢረ ቁርባን በጥያቄና መልስ

2ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ቁርባን ታሪክ የጸሎተ ሐሙስ የቁርባን ሥርዓት

3ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ቁርባን ጥቅስ ጥናት

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ጥር1ኛ ሳምንት ምስጢረ ትንሳኤ ሙታን በጥያቄና መልስ

2ኛ ሳምንት ስለምስጢረ ትንሳኤ ሙታን የአልአዛር ታሪክ

3ኛ ሳምንት ስለምስጢረ ትንሳኤ ሙታን ጥቅስ ጥናት

4ኛ ሳምንት ነገረ ማርያም በጥያቄና መልስ

የካቲት 1ኛ.ሳምንት ነገረ ማርያም የእመቤታችን የዘር ሀረግ እና ልደት ልደት

2ኛ ሳምንት ነገረ ማርያም እመቤታችን ቤተ መቅደስ መግባትዋ ጥቅስ ጥናት ጨምሮ

3ኛሳምንት ነገረ ቅዱሳን በጥያቄ እና መልስ

4ኛ ሳምንት ነገረ ቅዱሳን ቅዱስ ስለመባል እና ቅድስና

መጋት 1ኛ ሳምንት የቅድስት አርሴማ ዘአርመንያ ታሪክ

2ኛሳምንት ማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

ትምህርቱን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ስለ ትምህርት አሰጣጡ መምህሩ ለተማሪዎች በመግለጽ ከእኔ በኋላ በሉ በማለት ከእርሱ ቀጥለው ቃል በቃል በማስጠናት እንዲሁም ጥያቄውን እሱ እየጠየቀ እነርሱ መልሱን እያነበቡ እንዲመልሱ በማድረግ፤ይሔንን በመደጋገም እስኪያሰርጹት በመመላለስ ተማሪዎች በቀኝ በግራ ወንድ እና ሴት እንዲጠያየቁ በማድረግ፤ ከተማሪዎች መካከል ሁለት ሰው ወስዶ እንዲጠያየቁ በማድረግ ማስተማር ፤ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

የተለጠፈውን ጥቅስ ወይም የተጻፈውን እያነበቡ ደጋግመው ጥቅሱን እንዲናገሩት በማድረግ እና እሱን አንስቶ ወይም አጥፍቶ በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በማረጋገጥ ማስተማር ይቻላል

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1.ከመዝገበ ጸሎት መጽሐፍ

2.ከዓምደ ሃይማኖት መጽሐፍ

3.ከውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ መጽሐፍ

4.ከሃይማኖተ አበው እና

5.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት ላይ ያገኘዋል

6. ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

7. ነገረ ማርያም

8 ተዓምረ ማርያም

9 ገድለ ቅድስት አርሴማ

10.ስንክሳር

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.ስለ አዕማደ ምስጢራት የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

7. እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዥ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይበዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናትሳይቆጠሩ 40 ክፍለጊዜ ቢኖር 40ሲባዛ በ40 እኩል ይሆናላ16 ሰዓት ይወስዳል።

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ህጻናት ሁለት(ሁለተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

በዚህ ክፍል የሚማሩ ህጻናት ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1.ስለቤተክርስቲያናቸው ክብር ቅድስና ያውቃሉ

2. ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መግባት እንዳለባቸው ይገነዘባሉ።

3.ቤተክርስቲያን ሲመጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዴት በውስጥዋ መስገድ እንዳለባቸው አውቀው ይሰግዳሉ

4.ወደቤተክርስቲያን እየመጡ ይቆርባሉ ቅዳሴ ያስቀድሳሉ

5. ቤታቸው ጸሎት ይጸልያሉ።

6.ለችግረኞች ምጽዋት ይሰጣሉ

7. በዓላትን ከባልንጀሮቻቸው ጋር ያከብራሉ

8. ምግብ ሲበሉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በማወቅ አማትበው እና ጸልየው ይመገባሉ።

9. ምን ዓይነት ልብስ መቼ እና እንዴት መልበስ እናዳለባቸው አውቀው ይለብሳሉ

<u>ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ለህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት</u>

መጋቢት 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለ ትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ቤተ ክርስቲያን ስለ መምጣት ነጠላ ትእምርተ መስቀል አጣፍቶ ስለመልበስ ቆስጠንጢኖስ በመስቀል ድል እንዳደረገ ታሪክ

4ኛሳምንት ስናማትብ እና ቤተ ክርስቲያን ስንገባ ስለምንለው ነገር ስግደት በቤተ ክርስቲያን ሙሴ በሲና በቁጥቋጦ መጠራቱ

ሚያዝያ1ኛ ሳምንት ጸሎት ስለማድረስ የቤት ውስጥ ጸሎት ስምኦን ጫማ ሰፊው ለአባ አብርሃም እንደጸለየ

2ኛ ሳምንት ክርስቲያናዊ አለባበስ እና አመጋገብስለ አቡነ ሐቢብ የቅዱስ ጴጥሮስ አለባበስ በቀያፋ ግቢ ማቴ27፤

3ኛ ሳምንት ምጽዋት ስለመመጽወት እንጢላርዮስ

4ኛ ሳምንት ችግረኞችን ስለመርዳት ቅዱስ ቶማስ ሐዋርያ

ግንቦት 1ኛ ሳምንት በዓላትን ከሌሎች ጋር ስለማክበር ሉቃ14 ታሪክ

2ኛ ሳምንት ለሰው ሁሉ ስለመታዘዝ ሙሴ ጸሊም ዮሴፍ ወልደ ያዕቆብ

3ኛ ሳምንት ስለቁርባን ቅዳሴ ስለማስቀደስ የአባ እንጦንስ መጠራት

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ሰኔ1ኛ ሳምንት ስለ ትህትና ቅዱስ ዳዊት ከጎልያድ ጋር

2ኛ ሳምንት ስለ ታዛዥነት ቅዱስ ሉቃስ ሐዋርያትን እንደታዘዘ

3ኛ ሳምንት ቤተሰብን ስለማገልገል የጦቢያ አባቱን ጦቢትን እንዳገለገለው

4ኛ ሳምንት ቤት ውስጥ መዝሙር ስለማድመጥ

ሐምሌ1ኛ ሳምንት ሰውን ሁሉ ስለመውደድ

2ኛ ሳምንት ጥሩ ልጅ ስለመሆን ቅዱስ ጊዮርጊስ በገንዘብ በስልጣን ሃይማኖቱን እንዳልተወ

3ኛ ሳምንት ስለ ጥሩ ጓደኝነት እና መጥፎ ጓደኝነት ጥጦስ እና ዳርክስ በበረሀ ጌታችንን እንዳገኙት

4ኛ በትምህርት ውጤታማ ስለመሆን ቅዱስ ያሬድ

ነሐሴ1ኛ ሳምንት ቅዱሳት መጻህፍትን ስለማንበብ ቅዱስ ጢሞቴዎስ

2ኛ ሳምንት ወላጆችን በስራ ስለመርዳት ያዕቆብ ለላባ እንደታዘዘ

3ኛ ሳምንት የጥሩ ልጅ ምሳሌዎች ሠለስቱ ደቂቅ በሃይማኖት መጽናታቸው

4ኛ ሳምንት ማጠቃለያ እና ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

በገለጻ ማለት መምህሩ ስለትምህርቱ ለተማሪዎች በሚገባቸው መጠን ያስረዳቸዋል ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እና ለምን እንደምንመጣ መጥተን ስለምናደርገው ነገር ስንገባ ምን ብለን እንደምንሳለም በመጻፍ እና የተጻፈውን መላልሶ እንዲሉት በማድረግ

ሚና ጫወታ በመውሰድ ማለት አንድ ተማሪ እናት ሌላው አባት አንዱ ልጅ ሆነው በቤት ውጥ ጸሎት እንዴት እንደሚመራ እና እንደሚጸለይ ወደቤተክርስቲያን እንዴት መምጣት እንደሚገባ በድራማ በማሳየትወይም ከተማሪዎች ሁለቱን አውጥቶ ነጠላ እንዴት እንደሚለበስ እና እንዴት እንደሚሰገድ ምን እያልን እንደምንሰግድ በማሳየት ማስተማር

ወይም እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አኒሜሽን አዘጋጅቶ ወይም የተዘጋጀ አኒሜሽን ፊልም አምጥቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍቅዱስ

2. መጽሐፍ ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተዘጋጀ ማስተማሪያ መጽሐፍ

3.ከፍትሐ ነገስት

4.የቤተ ክርስቲያን ጸሎት

5.መርሐ ህይወት

6.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት ላይ ያገኘዋል

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ ተማሪዎች ሚለማመዱበት በመጠናቸው የተዘጋጀ ነጠላ

6.ስለ ዐበይት ሥነ ምግባር የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

7. እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተማሩትን እንዲያሳዩ በማድረግ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት

6.ቤተክርስቲያን እየተገኙ መምጣት አለመምጣታቸውን ማስቀደስ አለማስቀደሳቸውን በማየት መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ30 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይበዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናትሳይቆጠሩ 40 ክፍለጊዜ ቢኖር 40ሲባዛ በ30 እኩል ይሆናላ12 ሰዓት ይወስዳል።

ትምህርተ ግእዝ ለህጻናት ሁለት(ሁለተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው እንደጨረሱ

1. በቃላቸው ከአአትብ ገጽየ ጀምረው እስከ ሰላም ለኪ ድረስ በየቀኑ ያደርሳሉ
2. መርሐ ግብራቸውን በግእዝ ጸሎት ይከፍታሉ ይዘጋሉ
3. የግእዝ ቁጥሮችን ጠንቅቀው አውቀው በተጠየቁ ጊዜ ይመልሳሉ
4. መጽሐፍ ቅዱስን ያለምንም የቁጥር ስህተት ማንበብ ይችላሉ።
5. ምግብ በልተው ስብሐት በግእዝ ያደርሳሉ

ትምህርተ ግእዝ ለህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል) ዝርዝር ይዘት

ዘወርኃ መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪ ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለ ትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት አአትብ ገጽየ ነአኩተ

4ኛ ሳምንት አአትብ ገጽየ ነአኩተከ

ዘወርኃ ጥቅምት 1ኛ ሳምንት አቡነ ዘበሰማያት

2ኛ ሳምንተ አቡነ ዘበሰማያት

3ኛ ሳምንተ በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ

4ኛ ሳምንት በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ

ዘወርኃ ህዳር 1ኛ ሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት እስከ ወረደ እምሰማያት ድረስ

2ኛሳምንት ጸሎተ ሃይማኖት እስከ ወረደ እምሰማያት ድረስ

3ኛ ሳምንት ከ ተሰብአ ወተሰገወ እስከ ለዓለመ ዓለም ድረስ

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ዘወርኃ ታህሳስ 1ኛ ሳምንት ከተሰብአ ወተሰገወ እስከ ለዓለመ ዓለም ድረስ

2ኛ.ሳምንት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ

3ኛ ሳምንት እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

4ኛ ሳምንት እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ዘወርኃ ጥር 1ኛ ሳምንት ስብሐት

2ኛ ሳምንት ስብሐት

3ኛ ሳምንት ስብሐት

4ኛ ሳምንት ክለሳ

ዘወርኃ የካቲት 1ኛ ሳምንት ሰላም ለኪ

2ኛ ሳምንት ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም

3ኛ ሳምንት ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

ዘወርኃ መጋቢት1ኛ ሳምንት የግእዝ አኃዝ (ቁጥሮች) ከ1-20

2ኛ ሳምንት የግእዝ አኃዝ ከ21-50

3ኛ ሳምንት የግእዝ አኃዝ ከ51-70

4ኛ ሳምንት የግእዝ አኃዝ ከ71-100

ዘወርኃ ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት የግእዝ አኃዝ ከ100-130

2ኛ ሳምንት የግእዝ አኃዝ ከ130-160

3ኛ ሳምንት የግእዝ አኃዝ ከ160-200

4ኛ ሳምንት የግእዝ ቁጥሮች ከ201-240

ዘወርኃ ግንቦት 1ኛ ሳምንት የግእዝ ቁጥሮች ከ241-280

2ኛሳምንት የግእዝ ቁጥሮች ከ280-320

3ኛ ሳምንት የግእዝ ቁጥሮች ከ340-400

4ኛ ሳምንት የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት አጋማሽፈተና

ዘወርኃ ሰኔ 1ኛ ሳምንትየግእዝ ፊደላት ከሀ-ፐ

2ኛሳምንት የግእዝ ፊደላት ከ ሀ-ፐ

3ኛ ሳምንት ባለ ድርብ ድምጽ ፊደላት

4ኛሳምንት ክለሳ

ዘወርኃ ሀምሌ 1ኛ ሳምንት የግእዝ ቁጥሮች ከ400-500

2ኛ ሳምንት የግእዝ ቁጥሮች ከ500-600

3ኛ ሳምንት የግእዝ ቁጥሮች ከ600-700

4ኘ የግእዝ ቁጥሮች ከ700-1000 ድረስ

ዘወርኃ ነሀሴ 1ኛ ሳምንት ክለሳ

2ኛ ሳምንት ክለሳ

3ኛ ሳምንት ክለሳ

4ኛ ሳምንት ማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

ትምህርቱን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ስለ ትምህርት አሰጣጡ መምህሩ ለተማሪዎች በመግለጽ ከእኔ በኋላ በሉ በማለት ከእርሱ ቀጥለው ቃል በቃል በማስጠናት እንዲሁም እሱ ካለ በኋላ እንዲመልሱ በማድረግ፤ይሔንን በመደጋገም እስኪያሠርፁት በመመላለስ ተማሪዎች በቀኝ በግራ ወንድ እና ሴት እንዲመላልሱት በማድረግ፤ ከተማሪዎች መካከል ሁለት ሰው ወስዶ እንዲሉት በማድረግ ትምህርቱ መያዙን እስኪያረጋግጥ ድረስ መምህሩ መላልሶ መንገር ተማሪዎችም መላልሰው እንዲሉት በማድረግ ማስተማር ፤ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ በማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1.ከመዝገበ ጸሎት መጽሐፍ

2.ውዳሴ ማርያም በግእዝ

3.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት ላይ ያገኘዋል

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.የግእዝ ቁጥሮች የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

7. እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደ ሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘና እና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዥ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4. ከተማሪዎች አንዱን ድንገት ይኼንን በለው በማለት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይበዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናትሳይቆጠሩ 40 ክፍለጊዜ ቢኖር 40ሲባዛ በ40 እኩል ይሆናላ16 ሰዓት ይወስዳል።

መዝሙር ለህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

በዚህ ክፍል የዓመቱን ትምህርት ተምረው የሚጨርሱ ሰንበት ተማሪዎች

1.በዓመቱ መጨረሻ ከ48 ያላነሱ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ ኦርቶዶክሳዊ ወዛቸውን ያልለቀቁ መዝሙራትን አጥንተው ማቅረብ መዘመር ይችላሉ።

2. ትክክለኛውን መዝሙር ከዚህ እድሜያቸው ጀምረው ይመርጣሉ ይዘምራሉ

3.ሌላ መልክ ያለውን መዝሙር ይርቃሉም ያርቃሉም

<u>መዝሙር ለህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል) ዝርዝር ይዘት (መዝሙራት)</u>

መስከረም1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ለተማሪዎች አጠቃላይ ስለትምህርቱ ገለጻ

3ኛ ሳምንት እምሄሶ ለሄሮድስ (ጎበሩ ቃለ ነቢያት)

4ኛ ሳምንት ርዕዩ እበዩ ለእጸ መስቀል (ዕሌኒ ንግስት ሀሰሰት መስቀሉ)

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ረሀበ ወጽምዓ (በጽሐ ሠናየ)

2ኛ ሳምንት መሰረተ ህይወት (አክሊለ ጽጌ)

3ኛ ሳምንት ሀበነ እግዚኦ (እናመስግን አማኑኤልን)

4ኛ ሳምንት እስመ አልብነ ረዳኢ (እግዚአብሔር ብርሃኔ እና)

ህዳር 1ኛ ሳምንት ዘየአምር እምቅድመ ህሊና (ያከብርዋ)

2ኛ ሳምንት ባህራንኒ (ምስለ ሚካኤል)

3ኛ ሳምንት ሐነጽዋ ለቤተ ክርስቲያን (ኖላዊ ትጉህ)

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና ታህሳስ1ኛ ሳምንት ገብርኤም ምልአኒ (ገብርኤል አማልደን)

2ኛ ሳምንት ለዘተወልደ እምቅድስት (አንፈርአጹ)

3ኛሳምንት ዮም ፍስሐ ኮነ (ውስተ ማኅጸነ ድንግል ሀደረ)

4ኛ ሳምንትመድኃኒነ ተወልደ ነዋ (ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት)

ጥር1ኛ ሳምንት ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ (ሖረ ኢየሱስ)

2ኛ ሳምንት በወንጌሉ ያመናችሁ (ሐዲኅተስአ)

3ኛ.ሳምንት አስተርእዮቱ (ወረደ ወልድ)

4ኛ ሳምንት ነአምን ክርስቶስሃ (ጥምቀተ ባህር ዮርዲያኖስ ንያ)

የካቲት1ኛ ሳምንት መጽአ መርአዊ (በቃና ዘገሊላ)

2ኛ ሳምንት ካህናት ተንስኡ (ሶበሰ ኪዳንኪ)

3ኛ ሳምንት ማርያም ተዓቢ

4ኛ.ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

መጋቢት 1ኛ ሳምንት ንጹም ጾመ (መድኃኔ ዓለም አዳነን)

2ኛ ሳምንት ሆሳእና እምርት (ሆሳዕና ለወልደ ዳዊት)

3ኛ ሳምንት እም አፈ ደቂቅ (ፍቅር ሰሐቦ)

4ኛ ሳምንት ጼና አልባሲሁ (ገብረ መንፈስ ቅዱስ)

ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት ትንሳኤከ (አማን በአማን)

2ኛ ሳምንት አንትሙሰ ንበሩ (መንፈስ ቅዱስ ወረደ ላዕለ ሐዋርያት)

3ኛ ሳምንት ገድልከ ግሩም (ኮከብ ብሩህ)

4ኛ ሳምንት ያሬድ ፈልፈለ ማኅሌት (ተወልዳለችእና)

ግንቦት 1ኛ ሳምንት ኢያቄም ወሀና (ቀዋምያን ለነፍሳት)

2ኛ ሳምንት በመኑ በአምሳለ መኑ (ልቤን አነሳስቶ)

3ኛ ሳምንት አድኅነነ እግዚኦ ኩሉ ዘፈቀደ

4ኛ ሳምንት የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ሰኔ 1ኛ ሳምንት ተዋህዶ ንጽህት (እምኩሉ ይሄይስ)

2ኛ ሳምንት ዘሰማየ ገብረ (ማርያም ኩኒ)

3ኛ ሳምንት መድኃኔ ዓለም ወሀቤ ሰላም (እመቤቴ ጥላ ከለላዬ)

4ኛ ሳምንት ተናገሩ ድንቅ ስራውን (ከክርስቶስ ፍቅር)

ሐምሌ 1ኛ ሳምንት ሰአሉ ለነ ቅዱሳን (ጳውሎስ ሐዋርያ)

2ኛ ሳምንት ስብሐት ለአብ (ቂርቆስ ቀዊሞ)

3ኛሳምንት ኦ አንትሙ (እም ርሁቅሰ)

4ኛ ሳምንት ጊዮርጊስ ኃያል (ሰላም ዘአብ)

ነሀሴ 1ኛ ሳምንት ሰላም እለኪ ማርያም (ማርያም ማርያም ድንግል)

2ኛ ሳምንት በስመ ዚአከ ይትፌስሑ ዮም (አሐደ ለከ)

3ኛ ሳምንት በመንፈስ የሐውር (ማርያም አረገች)

4ኛ ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

መዝሙራቱን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ በሽት አዘጋጅቶ በመስጠት ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ስለ መዝሙሩ አጠናን መምህሩ ለተማሪዎች በመግለጽ ከእኔ በኋላ በሉ በማለት ከእርሱ ቀጥለው ቃል በቃል እንዲሉ በማድረግ እና በማስጠናት እንዲሁም እንዲቀባበሉ በማድረግ፤ይሔንን በመደጋገም እስኪ ያሰርጹት በመመላለስ ተማሪዎች በቀኝ በግራ ወንድ እና ሴት እንዲሉት በማድረግ፤ ከተማሪዎች መካከል አንድ ሰው ወስዶ እንዲዘምረው በማድረግ ማስተማር ፤ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም መዝሙራቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1.የሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ የመዝሙር መጽሐፍ

2.የጽርሐ ጽዮን ኦርቶዶክሳዊ መዝሙር መጽሐፍ ቁጥር1 እና 2

3.የማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ሰንበት ትምህርት ቤት የመዝሙር መጽሐፍ

4.የደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ሰንበት ትምህርት ቤት የመዝሙር መጽሐፍ

5.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6. ከበሮ ጸናጽል መቋሚያ

7፣ ተማሪዎች የሚያደርጉት ነጠላ (የሰንበት ተማሪዎች ልብስ)

8.እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘና እና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እያዩ እንዲ ዘምሩ በማድረግ

2. የተጻፈውን በማጥፋት መዝሙሩን በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት መዝሙሩን በቃላቸው እንዲይዙት በማድረግ

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን መዝሙራቱ እንዳይረሱ

5 በየወቅቱ ስላጠኑት መዝሙርያ ለፈውን እንዲዘምሩ በማዘዝ መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በአጠቃላይ በዓመት በዓላት ዝግ የሚሆኑበት ቀናት ሳይቆጠሩ 40 ክፍለ ጊዜ ቢኖር 40 ሲባዛ በ40 እኩል ይሆናላ16 ሰዓት ይወስዳል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ፤

በዚህ ክፍል ትምህርታቸውን ሚማሩ ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1. በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የተጻፉትን ታሪኮች አውቀው ሲጠየቁ ያብራራሉ።

2.በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት አበው ህይወት ተምረው በጎ ሥነ ምግባር ይይዛሉ

3.የእግዚአብሔርን ሀልዎት ጥበቃ መግቦት ተረድተው ተስፋቸውን በእርሱ ላይ ያደርጋሉ

4.በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ስለነበሩ አበው ይናገራሉ።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት</u>

መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለ ትምህርቱ ጠቅላላ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ስለ ቅዱሳት ሥዕላት የሥነ ፍጥረት ታሪክ ዘፍጥ1፤

4ኛ ሳምንት አዳም በኤዶም ገነት ዘፍጥ2፤

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ኖኅ እና የጥፋት ውሃ ዘፍጥ6-10፤

2ኛ ሳምንት አባታችን አብርሃም እና ካህኑ መልከጼዴቅ ዘፍጥ12-18

3ኛ ሳምንት የሰዶም መጥፋት የሎጥ መዳን ዘፍ19

4ኛ ሳምንት የይስሐቅ ልደት እና እድገት ዘፍ21-26

ህዳር1ኛ ሳምንት የያዕቆብ ዕድገት ታሪክ ዘፍ25

2ኛ ሳምንትያዕቆብ እና ኤሳው ዘፍ27

3ኛ ሳምንት የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ ዘፍ37፤የዮሴፍ መሸጥ እና የግብጽ ኑሮ ዘፍ39

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ 1ኛ ሳምንት ዮሴፍ በግብጽህልም እንደፈታ ዘፍ42

2ኛ ሳምንት ያዕቆብ ከነ ቤተሰቡ ግብጽ እንደገባ ዘፍ46

3ኛ ሳምንት የሙሴ መወለድ እና እድገት ዘጸ2

4ኛ ሳምንት እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ተዓምራት

ጥር1ኛ ሳምንት እስራኤል ከግብጽ መውጣታቸው

2ኛ ሳምንት በዓለ ፋሲካ እና የእስራኤል ጉዞ

3ኛ ሳምንት የአስሩ ትእዛዛት መሰጠት

4ኛ ሳምንት የአሮን ለክህነት መለየት እና የክህነት ስራው

የካቲት 1ኛ ሳምንት እስራኤል መና መብላታቸው እና ውሃ ከዓለት መጠጣታቸው ዘኁል 16-

2ኛ ሳምንትበለዓም እና ባላቅ ዘኁ22-24

3ኛ ሳምንት አስራ ሁለቱ ሰላዮች ዘኁ13

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

መጋቢት1ኛ ሳምንትሁለቱ ሰላዮች እና ረዓብ (ራኬብ) ኢያ2

2ኛ ሳምንት የኢያሪኮ ቅጥር መውደቅኢያሱ 6

3ኛ ሳምንት የጌድዮን መነሳት መሳፍንት6

4ኛ ሳምንት ዬፍታሄ ስዕለት መሳፍንት11

ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት የሶምሶን ልደቱን ታሪክ መሳ13

2ኛ ሳምንት ሩት ቦኤዝ እና ኑኃሚን ሩት1-4

3ኛ. ሳምንት ሄኖክ ስለ ጻድቃን እና ኃጥአን ያየው ራዕይ መ. ሄኖክ

4ኛ ሳምንት ካህኑ ኤሊ እና ታቦተ ጽዮን1ሳሙ1-6

ግንቦት 1ኛ ሳምንት የነብዩ ሳሙኤል እናት እና የሳሙኤል መጠራት1ሳሙ2-3

2ኛ ሳምንት የታቦተ ጽዮን መማረክ እና በድል መመለስ1ሳሙ4-6

3ኛ ሳምንት የሳኦል ንግስና 1ሳሙ9 እረኛው ዳዊት እና መቀባቱ

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና

ሰኔ 1ኛ ሳምንት የዮናታን እና የዳዊት ጓደኝነት 1ሳሙ20

2ኛ ሳምንት የዳዊት በጎነት ለሳኦል1ሳሙ24

3ኛ ሳምንት የዳዊት ንግስና 2ኛሳሙ2

4ኛ ሳምንት የዳዊት እና አቢግያ2ሳሙ25

ሐምሌ 1ኛ ሳምንት ሰሎሞንን ንግሥተ ሳባ በእንቆቅልሽ እንደፈተነችው1ነገ9

2ኛ ሳምንት የሰሎሞን ጥበብ እውነተኛ ፍርድን ለሁለቱ ሴቶች እንደፈረደ1ነገ3

3ኛ ሳምንት ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን እንደ ሰራ1ነገ6

4ኛ ሳምንት ነቢዩ ዳንኤል እና ሠለስቱ ደቂቅ

ነሀሴ 1ኛ ሳምንት የሮብዓም ንግስና 2ነገ12

2ኛ ሳምንት ነቢዩ ኤልያስ እና ሱነማይቴ ሴት

3ኛ ሳምንት ነቢዩ ኤልሳዕ ንዕማን ሶርያዊ

4ኛ ሳምንት ማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

ትምህርቱን የሚገልጽ ከቅዱሳት ሥዕላት ቀድሞ አዘጋጅቶ መርጦ በሰንበት ትምህርት ቤቱ በበጀት አጸድቆ ወይም በጎ ሊያደርጉ የሚችሉ ምዕመናንን በማሳሰብ በመንገር ሥዕላቱን በዲጂታል ህትመት በማሳተም ሁሉም ተማሪ እንዲያየው በማድረግ ሥዕሉን እያሳዩ ስለ ሥዕሉ ባለቤት ቢገልጹላቸው ትምህርቱ በቀላሉ ይረዳቸዋል ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ሥዕሉ በላፕቶፕ ማብራራት በማሳየት ሥለ ሥዕሉ ባለቤት ከ6 መስመር ባልበለጠ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ሥዕሉን በመለጠፍ በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ቢማሩ ትምህርቱ ማይረሳ ይሆናል እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ በማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍ ቅዱስ

2.ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ ያሉ የትርጓሜ መጻህፍት

3.ከውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ መጽሐፍ

4.መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት

5.የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተማሪያ ያዘጋጀው መጽሐፍ

6.መርሐ ህይወት መጽሐፍ እና ሌሎች መጻህፍት

7.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.ቅዱሳት ሥዕላት በሲዲ በፍላሽ በዲጅታል ህትመት

7.የታተመ ስለ ቅዱሳት ሥዕላት 2በ2 የሆነ በውስጡ ከ5 ያልበለጡ ከ5 ያላነሱ ቅዱሳት ሥዕላት ያሉበት ባነር

8.ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ እስከ ነቢያት ድረስ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ቅዱሳንን ሚያሳዩ ቅዱሳት ሥዕላት

9.ስለ ቅዱሳን አበው ነቢያት መሳፍንት የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

10. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘና እና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

6.ስለ አዳም ከተማሩ ሚስቱ ማን እንደሆነች የስማቸው ትርጉም ምን እንደሆነ ታሪካቸውን እና ከታሪካቸው ምን እንደ ምንማር በቃል እና በጽሑፍ መጠየቅ

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40 ቀን ይሆናል 40 ሲባዛ በ40 16 ሰዓት ይመጣል ስለዚህ በአጠቃላይ በዓመት16 ሰዓት ይወስዳል።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለህጻናት ሁለት(ሁለተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1.በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በዓመት ስለሚውሉ ዐበይት በዓላት ያውቃሉ።

2.በዓመት ውስጥ ያሉትን በዓላት ታሪክ ሲጠየቁ ይናገራሉ

3.በዓላቶቻችንን እና ትውፊታችንን ይጠብቃሉ ቅዱሳኑን ያከብራሉ

4.ክዱሳኑን በግብር ለመምሰል ይሞክራሉ የቅዱሳኑን የተጋድሎ ህይወት በሚገባ ይረዳሉ

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለህጻናት ሁለት ዝርዝር ይዘት

መስከረም 1ኛ ሳምንት ተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ስለ እንቁጣጣጭ ታሪካዊ አመጣጥ እና ስለዮሐንስመጥምቅየበረሃኑሮ እና ስብከቱ

4ኛ ሳምንት ስለ መስቀል ስለ ንግሥት እሌኒ

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ስለ አብርሃ እና አጽብሐአብያተ ክርስቲያናትን እንዳነጹ

2ኛ ሳምንት እመቤታችን በኢትዮጵያ

3ኛ ሳምንትስለ ገብረ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ

4ኛ ሳምንት ስለ ቅዱስ ዮሐንስ ሐጺር

ህዳር 1ኛ ሳምንት ስለቅዱስ ባስልዮስ እና እህቱ ቅድስት ማክሪና

2ኛ ሳምንት እመቤታችን ከስደት ስለመመለሷ

3ኛ ሳምንት ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤልቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽፈተና

ታህሳስ1ኛ ሳምንት ኤልያስ እና ናቡቴ

2ኛሳምንት እመቤታችን በቤተ መቅደስ እድገትዋ

3ኛ ሳምንት ሠለስቱ ደቂቅ እና ቅዱስ ገብርኤል

4ኛ ሳምንት የጌታችን ልደት ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ እንዳቀረቡለት

ጥር 1ኛ ሳምንት ቅዱስ እስጢፋኖስ እና አይሁዳውያን ያደረጉት ውይይት

2ኛ ሳምንት በዓለ ጥምቀት

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት በመበለትዋ ቤት ያደረገው ተዓምር

4ኛ ሳምንት አስሩ ደናግል አምስቱ ልባሞች ማቴ25

የካቲት 1ኛ ሳምንት ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እና እመቤታችን

2ኛ ሳምንት ነቢይት ሐና በሐዲስ ኪዳን ሉቃ2

3ኛ ሳምንት የሙሴ እረፍት

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

መጋቢት 1ኛ ሳምንት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዝቋላ

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ቄርሎስ መናፍቃንን መርታቱ

3 ሳምንት ጌታችን በማርያም እና በማርታ ቤት

4ኛ ሳምንት እመቤታችን ለተጠማ ውሻ ውሃ ማጠጣትዋ

ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት ቅዱስ ያሬድ ዜማን ከመላእክት እንደተማረ

2ኛ ሳምንት ተፋጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ እና ደቀመዛሙርቱ

3ኛ ሳምንት ስቅለተ እግዚእነ

4ኛ ሳምንት የጌታችን ትንሳኤ

ግንቦት 1ኛ ሳምንት የቅዱስ ድሜጥሮስ ሹመት

2ኛሳምንት ልደታ ለእግዝእትነ ማርያም

3ኛ ሳምንት የኢዮብ ደግነት

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ጋማሸፈተና

ሰኔ 1ኛ ሳምንት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ተዓምር

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ሚካኤል እና ቅድስት አፎምያ

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ላሊበላ እና የሰራቸው አብያተ ክርስቲያናት

4ኛ ሳምንት የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ጽንሰት

ሐምሌ1ኛ ሳምንት ታዴዎስ እና ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያት እለቱን ዘርተው ማብቀላቸው ታሪክ

2ኛ ሳምንት ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ጳውሎስ ተዓምራት

3ኛ ሳምንት ህጻኑ ቂርቆስ እና እናቱ ኢየሉጣ

4ኛሳምንት አቡነ ሰላማ ቅዱስ ፍሬምናጦስ በአክሱም ቤተ መንግስት

ነሐሴ 1ኛ.ሳምንት በዓለ ደብረ ታቦር

2ኛ.ሳምንት የእመቤታችን እርገት

3ኛ.ሳምንት ቅድስት አትናስያ

4ኛ ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

ትምህርቱን የሚገልጽ ከቅዱሳት ሥዕላት ቀድሞ አዘጋጅቶ መርጦ በሰንበት ትምህርት ቤቱ በበጀት አጸድቆ ወይም በጎ ሊያደርጉ ሚችሉ ምዕመናንን በማሳሰብ በመንገር ሥዕላቱን በዲጂታል ህትመት በማሳተም ሁሉም ተማሪ እንዲያየው በማድረግ ስለ ሥዕሉ ባለቤት ቢገልጹላቸው ትምህርቱ በቀላሉ ይረዳቸዋል ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ሥዕሉን በላፕቶፕ ማብራራት እንዲሁም ሥለ ሥዕሉ ባለቤት ከ6 መስመር ባልበለጠ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ሥዕሉን በመለጠፍ በ በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በኮምፒውተር ጽፎ አባዝቶ በመስጠት ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ቢማሩ ትምህርቱ ማይረሳ ይሆናል እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ በማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍ ቅዱስ

2.ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ ያሉ የትርጓሜ መጻህፍት

3.ከውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ መጽሐፍ

4.ክብረ ነገሥት

5.ገድለ ዮሐንስ መጥምቅ

6. ድርሳነ መስቀል

7. ወንጌል ትርጓሜ

8.ነገረ ማርያም

9. የሰ/ት/ቤቶች/ማ/መ/ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተማሪያ ያዘጋጀው መጽሐፍ

10.መርሐ ህይወት

11. ገድለ ጊዮርጊስ

12 ገድለ ማርያም ግብጻዊት እና ቅዱስ ዘሲማስ

13. ገድለ ተክለ ሃይማኖት

14.አራቱ ቅዱሳን ነገሥታት

15.ስንክሳር

16.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

<u>ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)</u>

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.ቅዱሳት ሥዕላት በሲዲ በፍላሽ በዲጅታል ህትመት

7.የታተመ ስለ ቅዱሳት ሥዕላት 2በ2 የሆነ በውስጡ ከ5 ያልበለጡ ከ5 ያላነሱ ቅዱሳት ሥዕላት ያሉበት ባነር

8.ከቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ ፎቶ የተነሱ ቅዱሳንን ሚያሳዩ ቅዱሳት ሥዕላት

9.ስለ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

10. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

2.በእለቱ የተማሩት ቅዱስ ማን እንደሚባል የስማቸው ትርጉም ምን እንደሆነ ታሪካቸውን እና ከታሪካቸው ምን እንደምንማር በቃል እና በጽሑፍ መጠየቅ

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40ቀን ይሆናል 40 ሲባዛ በ40 16 ሰዓት ይመጣል ስለዚህ በአጠቃላይ በዓመት16ሰዓት ይወስዳል።

3ኛ ክፍል (ህጻናት ሶስት)

እድሜያቸው ከ8-11ዓመት የክፍል ደረጃቸው ከ2-6ኛ ክፍል ወይም የህጻናት አንድ ትምህርትን የጨረሱ በሳምንት ለሁለት ቀናት ለ4ሰዓት ያህል በሳምንት ለሁለት ሰዓት ይማራሉ።

በአጠቃላይ ስድስት የትምህርት ዓይነቶችን ሲማሩ ሶስቱ ትምህርቶች ዓመቱን ሙሉ የሚዘልቁ ሲሆኑ ሶስቱ ግን በወሰነ ትምህርት የሚቀየሩ ይሆናሉ።

የትምህርት ዓይነቶቹም

1.ዜማ (መዝሙር) አጫጭር የግእዝ መዝሙራት

2.ግእዝ (የቃል ትምህርት ከጸሎተ እግዝእትነ ማርያም እስከ ዐርብ ውዳሴ ማርያም)

3.ትምህርተ ሃይማኖት በጥያቄ እና መልስ ሰባቱን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን

4.የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (ከልደተ ክርስቶስ እስከ ሐዋርያት መነሳት ድረስ)

5.ሥነ ምግባር (ዘጠኙን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በአጭሩ...

6.የቤተ ክርስቲያን ታሪክ (የቤተ ክርስቲያናችን ዓበይት በዓላት)

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዜማ እና ግእዝ ዓመቱን ሙሉ ሚሰጡ ሲሆኑ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ትምህርተ ሃይማኖት እና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በወሰነ ትምህርት የሚቀያየሩ ይሆናል የሁሉም ትምህርት አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማ ዝርዝር ይዘት የሚወስደው ደቂቃ ማስማሪያ ዘዴ መርጃ መሳሪያ ምዘና እና ግምገማ ስልት በዝርዝር ይሰራል።

ለህጻናት 3 (ሶስተኛ ክፍል)ትምህርተ ሃይማኖት

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች የዚህን ክፍል ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ

1.ስለ ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ያውቃሉ

2.ምስጢራቱን ማን እንደ ሚፈጽማቸው ይረዳሉ

3.የምስጢራቶቹ ተካፋዮች ይሆናሉ

4. በቤተክርስቲያን በመገኘት ምስጢራቱን ይከታተላሉ ከምስጢራቶቹ ተሳታፊ ይሆናሉ

5.ስለ እመቤታችን ቅድስና እና ክብር ይናገራሉ ስለቅዱሳን እና ክብራቸው ይገልጻሉ

የትምህርተ ሃይማኖት የህጻናት ሶስት ዝርዝር ይዘት

መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለ ትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን መግቢያ በጥያቄና መልስ

4ኛ ሳምንት ምሥጢረ ጥምቀት በጥያቄ እና መልስ

ጥቅምት1ኛ ሳምንት ምስጢረ ሜሮን በጥያቄ እና መልስ

2ኛ ሳምንት ምስጢረ ሜሮን በጥያቄ እና መልስ

3ኛ ሳምንት ምስጢረ ቁርባን በጥያቄ እና መልስ

4ኛ ሳምንት ምስጢረ ቁርባን በጥያቄ እና መልስ

ህዳር 1ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ክህነት በጥያቄ እና መልስ

2ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ክህነት በጥያቄ እና መልስ

3ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ክህነት በጥያቄ እና መልስ

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ 1ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ንስሐ በጥያቄ እና መልስ

2ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ንስሐ በጥያቄ እና መልስ

3ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ቀንዲል በጥያቄ እና መልስ

4ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ቀንዲል በጥያቄ እና መልስ

ጥር1ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ተክሊል በጥያቄ እና መልስ

2ኛሳምንት ስለ ምስጢረ ተክሊል በጥያቄ እና መልስ

3ኛ ሳምንት ስለ ምስጢረ ተክሊል በጥያቄ እና መልስ

4ኛ ሳምንት ነገረ ማርያም በጥያቄ እና መልስ

የካቲት 1ኛ ሳምንት ስለ ነገረ ማርያም በጥያቄ እና መልስ

2ኛ ሳምንት ስለ ነገረ ማርያም በጥያቄ እና መልስ

3ኛ ሳምንት ነገረ ቅዱሳን በጥያቄ እና መልስ

4ኛ የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

ይህ ትምህርት ከሌሎቹ ትንሽ ለየት ያለ የማስተማሪያ ዘዴ የሚፈልግ ሲሆን ተግባራዊ የሚደረግ የሚታይ በመሆኑ ትምህርቱን ምስጢራቱ በሚፈጸሙበት ቦታ በቤተ ክርስቲያን በአካል በመገኘት ቢማሩ ትምህርቱ ማይረሳ ይሆናል ምሳሌ ስለ ምስጢረ ጥምቀት ለማስተማር መጠመቂያ ክርስትና ቤት ወስዶ ሲጠመቁ የሚፈጸመውን ምስጢር በማሳየት ወይም በፊልም ቀድቶ በፕሮጀክተር ወይም በቲቪ ወይም በኮምፒውተር ማሳየት ቅዳሴ አስቀድሰው እንዲቆርቡ በማድረግ የተክሊል ሥርዓትን የተቀረጸ ፈልጎ በማሳየት ማስተማር ይቻላል።

ስለ ትምህርቱ ከ5-6 መስመር ባለበለጠ ጥቁር ወይም ነጭ ሰሌዳ ላይ መጻፍ እና ያንን በመግለጽ

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍ ቅዱስ

2.ምስጢራተ ቤተክርስቲያን

3.ፍትሐ ነገሥት

4.ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

5.የሰ/ት/ቤ/ማ/መ/ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተማሪያ ያዘጋጀው መጽሐፍ

6.መርሐ ህይወት መጽሐፍ እና ሌሎች መጻህፍት

7.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

<u>ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)</u>

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

4.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

5.ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ሚያሳዩቪሲዲ በፍላሽ በዲጅታል ህትመት

6.ቲቪ ከነ ዲቪዲ ማጫወቻው

7. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

<u>ምዘናእና ግምገማ</u>

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘና እና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5. ከተመለከቱ በኋላ በሳምንቱ ሳምንት ምን እንደ ተመለከቱ እንዲናገሩ በማድረግ

6.በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

<u>ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ</u>

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆንበዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40ቀን ይሆናል 40 ሲባዛ በ40 16 ሰዓት ይመጣል ስለዚህ በአጠቃላይ በዓመት 16 ሰዓት ይወስዳል።

<u>ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ለህጻናት ሶስት(ሶስተኛ ክፍል)</u>

<u>የትምህርቱ ዓላማ</u>

ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1.የአንድ በጎ ክርስቲያን ተግባርን በህይወታቸው ያሳያሉ

2.ቤተክርስቲያን ሲገቡ እና ሲወጡ ተሳልመው እና ሰግደው ይገባሉ ይወጣሉ

3.ቅዳሴ በማስቀደስ ይቆርባሉ ከመቁረባቸው በፊት እና በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ

4.በጎ ክርስቲያናዊ አኗኗርን ይለምዳሉ

5.ለሰው ሁሉ ሚራሩ ሰውን ሁሉ ሚወዱ እና ለሰው ሁሉ ፍቅር የሚያሳዩ ይሆናሉ።

<u>ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ለህጻናት ሁለት (ሁለተኛ ክፍል) ዝርዝር ይዘት</u>

መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንትሳምንት ስለ ማማተብ በቤተ ክርስቲያን እንዴት መስገድ እንዳለብን

4ኛ ሳምንት በቤተ ክርስቲያን ማድረግ ስለ ሚገባን እና ስለ ማይገባን

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ስለ ማማተብ ክለሳ እና ቤተ ክርስቲያን ስለ መግባት ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ

2ኛ ሳምንት በቅዳሴ ወቅት ማድረግ ስለ ሚገባን እና ስለ ማይገባን

3ኛ ሳምንት ቅዳሴ ስለ ማስቀደስ

4ኛ ሳምንት እንዴት ማስቀደስ እንደሚገባ

ህዳር1ኛ ሳምንት ስለ ቅዱስ ቁርባን

2ኛ ሳምንት ቁርባን ለመቁረብ ምን ማድረግ እንዳለብን

3ኛ ሳምንት ከመቁረባችን በፊት ምን ማድረግ እንዳለብን ከቆረብን በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብን

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ1ኛ ሳምንት ነጠላ ስለመልበስ

2ኛ ሳምንት ተግባራዊ ስራ መሳለም ነጠላ አለባበስ

3ኛ ሳምንት ጉብኝት ወደ ገዳም ስለ ክርስቲያናዊ አለባበስ

4ኛ ሳምንት ስለ ስግደት

ጥር 1ኛ ሳምንት ስለ ትህትና

2ኛ ሳምንት ስለ መታዘዝ

3ኛ ሳምንት ስለ ምጽዋት

4ኛ ሳምንት ስለ መዝሙራት

የካቲት 1ኛ ሳምንት መዝሙር እንዴት መዘመር እንዳለብን

2ኛ ሳምንት ሰውን ሁሉ ስለ መውደድ

3ኛ ሳምንት የጥሩ ልጅ አብነት ስለመሆን

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

በገለጻ ማለት መምህሩ ስለትምህርቱ ለተማሪዎች በሚገባቸው መጠን ያስረዳቸዋል ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እና ለምን እንደምንመጣ መጥተን ስለምናደርገው ነገር ስንገባ ምን ብለን እንደ ምንሳለም በመጻፍ እና የተጻፈውን መላልሶ እንዲሉት በማድረግ

ሚና ጫወታ በመውሰድ ማለት አንድ ተማሪ እናት ሌላው አባት አንዱ ልጅ ሆነው በቤት ውጥ ጸሎት እንዴት እንደሚመራ እና እንደ ሚጸለይ ወደ ቤተክርስቲያን እንዴት መምጣት እንደሚገባ ነጠላ እንዴት እንደ ሚለበስ ስለ ክርስቲያናዊ ሰላምታ በድራማ በማሳየት ወይም ከተማሪዎች ሁለቱን አውጥቶ ነጠላ እንዴት እንደ ሚለበስ እና እንዴት እንደሚሰገድ ምን እያልን እንደ ምንሰግድ በማሳየት ማስተማር

ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አኒሜሽን አዘጋጅቶ ወይም የተዘጋጀ አኒሜሽን ፊልም አምጥቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍቅዱስ

2. መጽሐፍ ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተዘጋጀ ማስተማሪያ መጽሐፍ

3.ከፍትሐ ነገስት

4.የቤተ ክርስቲያን ጸሎት

5.መርሐ ህይወት

6.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት ላይ ያገኘዋል

<u>ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)</u>

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ ተማሪዎች ሚለማመዱበት በመጠናቸው የተዘጋጀ ነጠላ

6. የጉዞ መኪና በመከራየት በዓመት 2 ቀናት ወደተለያዩ ቅርብ እና ውሎ ገብ ወደሆኑ ገዳማት ወስዶ መመለስ

7. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

<u>ምዘናእና ግምገማ</u>

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘና እና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተማሩትን እንዲያሳዩ በማድረግ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት

6.የወላጆቻቸውን ስልክ በመቀበል ስልክ በመደወል እና ስለመንፈሳዊ ህይወታቸው ወላጆችን በመጠየቅ

7.ቤተክርስቲያን እየተገኙ መምጣት አለመምጣታቸውን ማስቀደስ አለማስቀደሳቸውን በማየት መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ30 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆንበዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40ቀን ይሆናል 40 ሲባዛ በ30 12ሰዓት ይመጣልስለዚህ በአጠቃላይበዓመት16ሰዓት ይወስዳል።

መዝሙር ለህጻናት ሶስት(ሶስተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

በዚህ ክፍል የዓመቱን ትምህርት ተምረው የሚጨርሱ ሰንበት ተማሪዎች

1.በዓመቱ መጨረሻ ከ48 ያላነሱ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ ኦርቶዶክሳዊ ወዛቸውን ያልለቀቁ መዝሙራትን አጥንተው ማቅረብ መዘመር ይችላሉ።

2.ትክክለኛውን መዝሙር ከዚህ እድሜያቸው ጀምረው መርጠው ይዘምራሉ

3.ሌላ መልክ ያለውን መዝሙር ይርቃሉም ያርቃሉም

4.የቤተክርስቲያናችንን የመዝሙር ወዝ ይለምዳሉ።

5.በቤተክርስቲያናችን አውደምሕረት ኦርቶዶክሳዊ ወዙ ያልራቀውን መዝሙር ያቀርባሉ

መዝሙር ለህጻናት ሁለት(ሁለተኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት

መስከረም1ኛ ሳምንት ተማሪ ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት በመስቀልከ ርድአነ

4ኛ ሳምንት ወሪዶ እመስቀሉ

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ረሀበ ወጽምዓ

2ኛ ሳምንት መሰረተ ህይወት

3ኛ ሳምንት ሀበነ እግዚኦ

4ኛ ሳምንት እስመ አልብነ ረዳኢ

ህዳር 1ኛ ሳምንት ዘየአምር እምቅድመ ህሊና

2ኛ ሳምንት ባህራንኒ

3ኛ ሳምንት ሐነጽዋ ለቤተ ክርስቲያን

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ1ኛ ሳምንት ገብርኤም ምልአኒ

2ኛ ሳምንት ለዘተወልደ እምቅድስት

3ኛሳምንት ዮም ፍስሐ ኮነ

4ኛ ሳምንት መድኃኒነ ተወልደ ነዋ

ጥር1ኛ ሳምንት ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ

2ኛ ሳምንት በወንጌሉ ያመናችሁ

3ኛ ሳምንት አስተርዮቱ

4ኛ ሳምንት ነአምን ክርስቶስሃ

የካቲት1ኛ ሳምንት መጽአ መርአዊ

2ኛ ሳምንት ካህናት ተንስኡ

3ኛ ሳምንት ማርያም ተዓቢ

4ኛ.ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

መጋቢት 1ኛ ሳምንት ንጹም ጾመ

2ኛሳምንት ሆሳእና እምርት፤ሆሳዕና ለወልደ ዳዊት

3ኛ ሳምንት እም አፈ ደቂቅ፤እም እቶነ እሳት

4ኛ ሳምንት ጴና አልባሲሁ አባ አቡነ

ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት ትንሳኤከ

2ኛ ሳምንት አንትሙሰ ንበሩ፤ጊዮርጊስ ኃያል

3ኛ ሳምንት ገድልከ ግሩም ፤ማርቆስ አስተማረ

4ኛ ሳምንት ያሬድ ፈልፈለ ማኅሌት፤ምስራቀ ምስራቃት

ግንቦት 1ኛ ሳምንት ኢያቄም ወሀና፤ ኩሉ ከንቱ ከንቱ ንብረቱ

2ኛ ሳምንት በመኑ በአምሳለ መኑ ፤ኦ አባ ቅዱስ እቀቦሙ

3ኛ ሳምንት አድኅነነ እግዚኦ ፤ከመ ትባርከነ

4ኛ ሳምንት የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ሰኔ 1ኛ ሳምንት ተዋህዶ ንጽህት ፤እንዘ ይብሉ ይዜምሩ

2ኛ ሳምንት ዘሰማየ ገብረ ፤ንጽሕተ ንጹሐን ከዊና

3ኛ ሳምንት መድኃኔ ዓለም ወሀቤ ሰላም፤በምድራዊ ህይወት

4ኛ ሳምንት ተናገሩ ድንቅ ስራውን

ሐምሌ 1ኛ ሳምንት ሰአሉ ለነ ቅዱሳን ፤ጴጥሮስ አስተማረ ቃለ ክርስቶስ

2ኛ ሳምንት ስብሐት ለአብ ፤ያልጠፋነው

3ኛሳምንት ኦ አንትሙ ፤ ገብርኤል ምልዓኒ

4ኛ ሳምንት ጊዮርጊስ ኃያል፤ቂርቆስ ቀዊሞ

ነሀሴ 1ኛ ሳምንት ሰላም እለኪ ማርያም

2ኛ ሳምንት በስመ ዚአከ ይትፌስሑ ዮም

3ኛ ሳምንት በመንፈስ የሐውር

4ኛ ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

መዝሙራቱን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ በሽት አዘጋጅቶ በመስጠት ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ስለ መዝሙሩ አጠናን መምህሩ ለተማሪዎች በመግለጽ ከእኔ በኋላ በሉ በማለት ከእርሱ ቀጥለው ቃል በቃል እንዲሉ በማድረግ እና በማስጠናት እንዲሁም እንዲቀባበሉ በማድረግ፤ይሔንን በመደጋገም እስኪያሰርጹት በመመላለስ ተማሪዎች በቀኝ በግራ ወንድ እና ሴት እንዲሉት በማድረግ፤ ከተማሪዎች መካከል አንድ ሰው ወስዶ እንዲዘምረው በማድረግ ማስተማር መዝሙሩን ቆመው እያሸበሸቡ እያጨበጨቡ እንዲሉት በማድረግ ፤ወይም እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም መዝሙራቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1.የሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ የመዝሙር መጽሐፍ

2.የጽርሐ ጽዮን ኦርቶዶክሳዊ መዝሙር መጽሐፍ ቁጥር1 እና 2

3.የማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ሰንበት ትምህርት ቤት የመዝሙር መጽሐፍ

4.የደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ሰንበት ትምህርት ቤት የመዝሙር መጽሐፍ

5.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

<u>ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)</u>

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6. ከበሮ ጸናጽል መቋሚያ

7.ተማሪዎች የሚያደርጉት ነጠላ (የሰንበት ተማሪዎች ልብስ)

8.እንደሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

<u>ምዘናእና ግምገማ</u>

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘና እና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እያዩ እንዲዘምሩ በማድረግ

2. የተጻፈውን በማየጥፋት መዝሙሩን በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት መዝሙሩን በቃላቸው እንዲይዙት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን መዝሙራቱ እንዳይረሱ

5 በየወቅቱ ስላጠኑት መዝሙርያለፈውን እንዲዘዘምሩ በማዘዝ መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆንበዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40ቀን ይሆናል 40 ሲባዛ በ40 16 ሰዓት ይመጣል ስለዚህ በአጠቃላይ በዓመት 16 ሰዓት ይወስዳል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለህጻናት ሶስት(ሶስተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

በዚህ ክፍል የሚማሩ ህጻናት ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1. ስለቅዱስ የሐንስ እና ቤተሰቡ ያውቃሉ።

2.የጌታችንን እና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ጉዞ ከጽንሰት ጀምሮ እስከ እርገቱ ይገነዘባሉ፤

3.ጌታችንን ያስተማረውን ትምህርቶች የሰራውን ተዓምራት ይናገራሉ

4.በሐዲስ ኪዳን በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተገለጹት ቅዱሳን እና ቅዱሳት መግለጽ ይችላሉ

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለህጻናት 3 (ሶስተኛ ክፍል) ዝርዝር ይዘት

መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ካህኑ ዘካርያስ እና ቅድስት ኤልሳቤጥ ሉቃ1የቅዱስ ዮሐንስ ልደት ሉቃ1

4ኛሳምንት የቅድስት ኤልሳቤጥ እና የእ/ቅ/ድ/ማርያም መገናኘት ሉቃ1

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት የጌታችን ብስራት 1-2

2ኛ ሳምንት የጌታችን ልደት እና ስደት ሉቃ2 የሰብአ ሰገል መምጣት ማቴ2

3ኛ ሳምንት የጌታችን ጥምቀት ማቴ3

4ኛ ሳንት የጌታችን መፈተን ማቴ4

ህዳር 1ኛ ሳምንት የሐዋርያት መጠራት ማቴ4

2ኛ ሳምንት የጌታችን ትምህርቶች አንቀጸ ብጹአን ማቴ5

3ኛ ሳምንት ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ማቴ5 ስለ ምጽዋት ምስለ ጸሎት እና ስለጾም ማቴ6

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ 1ኛ ሳምንት ማንም ላይ መፍረድ እንደማይገባ ማቴ7

2ኛ ሳምንት የዘሪው ምሳሌ ማቴ13

3ኛ ሳምንት ደጉ ሳምራዊ ሉቃ10

4ኛ ሳምንት የጠፋው ልጅ ታሪክ ሉቃ15

ጥር1ኛሳምንት ቀራጩ ዘኬዎስ ሉቃ18

2ኛ ሳምንት ጌታችን እና ኒቆዲሞስዮሐ3

3ኛ ሳምንት ጌታችን እና ሳምራዊቷሴት ዮሐ4

4ኛ ሳምንት በአመንዝራነት የተያዘችው ሴት ዮሐ8

የካቲት 1ኛ ሳምንት የጌታችን ተዓምራቶች ጌታችን የመስፍኑን ልጅ ማዳኑማቴ8

2ኛ ሳምንት የጴጥሮስን አማት ከንዳድ ማዳኑ ማቴ8ማዕበሉን መገሰጹ

3ኛሳምንት ደም ይፈሳት የነበረችውን ሴት ማዳኑ ማቴ9 ሁለቱ ዓይነ ስውራን ህብስት አበርክቶ እንዳበላ

4ኛ የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

መጋቢት 1ኛ ሳምንት የዶኪማስ ሰርግ ዮሐ2

2ኛ ሳምንት የመጻጉዕ መዳን ዮሐ5

3ኛ ሳምንት ስለ ህይወት ምግብ ዮሐ6

4ኛ ሳምንት ዕውር ሆኖ የተወለደውን ማዳኑዮሐ9

ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት የዓልዓዛር ከሞት መነሳት ዮሐ11

2ኛ ሳምንት ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ

3ኛ ሳምንት ሳምንት የሐዋርያት ሹመት ዮሐ21

4ኛ ሳምንት ቶማስ ሐዋርያዮሐ20

ግንቦት1ኛ ደብረ ታቦር ማቴ17

2ኛ ሳምንት ከነናዊትዋ ሴት ማቴ15

2ኛ ሳምንት የመንግስተ ሰማይ ምሳሌ

3ኛ ሳምንት ስለ ትህትና ማቴ18 ስለ ዓለም ፍጻሜ ምልክት ማቴ 24

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት አጋማሽፈተና

ሰኔ 1ኛ ሳምንት የበጎች እና የፍየሎች ምሳሌ ማቴ25

2ኛ ሳምንት ሆሳዕና ማቴ21

3ኛ ሳምንት ምስጢረ ቁርባን እና ጸሎት በጌቴ ሴማኒ ማቴ26

4ኛ ሳምንት ጌታችን በጲላጦስ ፊት ማቴ27

ሐምሌ 1ኛ ሳምንት የጌታችን ስቅለትማቴ27

2ኛ ሳምንት ሰባ ሁለቱ አርድዕት ሉቃ10

3ኛ ሳምንት ፈያታዊ ዘየማን እና ዘጸጋም ጥጦስ እና ዳርክስሉቃ23

4ኛ ሳምንት የጌታችን ትንሳኤማቴ28

ነሐሴ 1ኛ የጌታችን እርገት ሉቃ24

2ኛ ሳምንትየጌታችን በቢታንያ ማረግሉቃ24

3ኛ ሳምንት በሐዋርያት ላይ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ መውረዱ የሐዋ2

4ኛ ሳምንት ማጠቃለያ እና ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

ትምህርቱን የሚገልጽ ከቅዱሳት ሥዕላት ቀድሞ አዘጋጅቶ መርጦ በሰንበት ትምህርት ቤቱ በበጀት አጸድቆ ወይም በጎ ሊያደርጉ ሚችሉ ምዕመናንን በማሳሰብ በመንገር ሥዕላቱን በዲጂታል ህትመት በማሳተም ሁሉም ተማሪ እንዲያየው በማድረግ ሥዕሉን እያሳዩ ስለ ሥዕሉ ባለቤት ቢገልጹላቸው ትምህርቱ በቀላሉ ይረዳቸዋል ወይም እንደሰንበት ትምህርትቤቱ እና መምህሩ አቅም ሥዕሉ በላፕቶፕ ላይ በማሳየት ሥለ ሥዕሉ ባለቤት ከ6 መስመር ባልበለጠ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ሥዕሉን በመለጠፍ በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቢማሩ ትምህርቱ ማይረሳ ይሆናል እንደ ሰንበት ትምህርትቤቱ እና መምህሩ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ በማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍ ቅዱስ

2.ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ ያሉ የትርጓሜ መጻህፍት

3.ከውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ መጽሐፍ

4.ተዓምረ ኢየሱስ እና ተዓምረ ማርያም

5. የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተማሪያ ያዘጋጀው መጽሐፍ

6.መርሐ ህይወት

7.ስንክሳር

8.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

<u>ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)</u>

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.ቅዱሳት ሥዕላት በሲዲ በፍላሽ በዲጅታል ህትመት

7. የታተመ ስለ ቅዱሳት ሥዕላት 2 በ2 የሆነ በውስጡ ከ5ያልበለጡ ከ5 ያላነሱ ቅዱሳት ሥዕላት ያሉበት ባነር

8.ከክርስቶስ ጽንሰት ጀምሮ እስከ እርገቱ ድረስ በሐዲስ ኪዳን የነበሩ ቅዱሳንን ሚያሳዩ ቅዱሳት ሥዕላት

9ስለ ጌታችንን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ተዓምራት እናትሩፋት የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

10. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

6.ጌታችን ያስተማረባቸው ከተሞች መንደሮች ማን እንደሆኑስማቸውን እና የስማቸው ትርጉም ምን እንደሆነ ታሪካቸውን እና ከታሪካቸው ምን እንደምንማር በቃል እና በጽሑፍ መጠየቅ

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆንበዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40ቀን ይሆናል 40ሲባዛ በ40 በዓመት16 ሰዓትይመጣል ስለዚህ በአጠቃላይ በዓመት16 ሰዓት ይወስዳል።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለህጻናት ሶስት (ሶስተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው እንደጨረሱ

1. በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በዓመት ስለሚውሉ ዐበይት በዓላት ያውቃሉ።

2.በዓመት ውስጥ ያሉትን በዓላት ታሪክ ሲጠየቁ ይናገራሉ

3.በዓላቶቻችንን እና ትውፊታችንን ይጠብቃሉ ቅዱሳኑን ያከብራሉ

4.ቅዱሳኑን በግብር ለመምሰል ይሞክራሉ የቅዱሳኑን የተጋድሎ ህይወት በሚገባ ይረዳሉ

<u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለህጻናት ሶስት (ሶስተኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት</u>

መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ስለ ቅዱስ ራጉኤል መልአክ ስለ ዮሐንስ መጥምቅ

4ኛ ሳምንትቅድስት እሌኒ እና ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ስለ መስቀል

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት እመቤታችን በምድረ ግብጽ

2ኛ ሳምንት እመቤታችን በኢትዮጵያ

3ኛ ሳምንት ሐዋርያው ቶማስ

4ኛ ሳምንት ቅድስት ጲላግያ

ህዳር1ኛ ሳምንት ቅድስት አንስጣስያ

2ኛ ሳምንት እመቤታችን ደብረ ቁስቋም ስለመግባትዋ

3ኛ ሳምንት የእመቤታችን እናት እና አባት ሐናእና ኢያቄም ቅዱስ ሚናስ

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ 1ኛ ሳምንት ካህናተ ሰማይ

2ኛ ሳምንት እመቤታችን ወደ ቤተመቅደስ መግባትዋ

3ኛ ሳምንት ሠለስቱ ደቂቅ እና ቅዱስ ገብርኤል

4ኛ ሳምንት የጌታችን ልደት

ጥር1ኛ ሳምንት የጌታችን ግዝረት

2ኛ ሳምንት የጌታችን ጥምቀት

3ኛ ሳምንት ጌታችን በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት

4ኛ ሳምንት የእመቤታችን እረፍት

የካቲት 1ኛ ሳምንት ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ

2ኛ ሳምንት ማርያም እንተ እፍረት

3ኛ ሳምንት ኪዳነ ምሕረት ቴዎድሮስ ሮማዊ

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ፈተና

መጋቢት 1ኛ ሳምንት ቅዱስ ጎርጎርዮስ

2ኛ ሳምንት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

3ኛ ሳምንት ስለ ሊቃነ ጳጳሳት

4ኛ ሳምንት ስለ አባ መቃርስን

ሚያዝያ 1ኛ ሳምንት ስለ ስምኦን ሰፋዔ አዕሳን

2ኛ ሳምንት ሕዝቅኤል ነቢይ

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ኤስድሮስ

4ኛ ሳምንት ቅዱስ ያዕቆብ ሐዋርያ

ግንቦት 1ኛ ሳምንት ኢዮብ ጻድቅ

2ኛ ሳምንት አቡነ ተክለ ሃይማኖት

3ኛ ሳምንት ናትናኤል ሐዋርያ ቅዱስ ኤስድሮስ

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ሰኔ 1ኛ ሳምንት ቅድስት አፎምያ

2ኛ ሳምንት የቤተክርስቲያን መታነጽ

3ኛ ሳምንት ገብረ ክርስቶስ መርዓዊ

4ኛሳምንት ሙሴ ጸሊም

ሐምሌ1ኛ ሳምንት ቅዱስ ቄርሎስ ዓምደ ሃይማኖት

2ኛ ሳምንት ነቢዩ ዕዝራ

3ኛ ሳምንት ቅዱስ ጴጥሮስ እና ጳውሎስ

4ኛ ሳምንት ቅድስት እንባ መሪና

ነሐሴ 1ኛ ሳምንት ቅዱስ አቦሊ

2ኛ ሳምንት ስምዖን ዘአምድ

3ኛ ሳምንት የእመቤታችን እርገት

4ኛ ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና

የማስተማሪያ ዘዴ

ትምህርቱን የሚገልጽ ከቅዱሳት ሥዕላት ቀድሞ አዘጋጅቶ መርጦ በሰንበት ትምህርት ቤቱ በበጀት አጸድቆ ወይም በጎ ሊያደርጉ ሚችሉ ምዕመናንን በማሳሰብ በመንገር ሥዕላቱን በዲጂታል ህትመት በማሳተም ሁሉም ተማሪ እንዲያየው በማድረግ ስለ ሥዕሉ ባለቤት ቢገልጹላቸው ትምህርቱ በቀላሉ ይረዳቸዋል ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ሥዕሉን በላፕቶፕ ማብራራት እንዲሁም ሥለ ሥዕሉ ባለቤት ከ6 መስመር ባልበለጠ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ሥዕሉን በመለጠፍ በ በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በኮምፒውተር ጽፎ አባዝቶ በመስጠት ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ቀድሞ ቢማሩ ትምህርቱ ማይረሳ ይሆናል እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እና መምህሩ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ በማቅረብ ማስተማር ይቻላል።

መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1. መጽሐፍ ቅዱስ

2.ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ ያሉ የትርጓሜ መጻህፍት

3.ከውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ መጽሐፍ

4.ክብረ ነገሥት

5.ገድለ ዮሐንስ መጥምቅ

6. ድርሳነ መስቀል

7. ወንጌል ትርጓሜ

8.ነገረ ማርያም

9. ገድለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

10 ስንክሳር

11. የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተማሪያ ያዘጋጀው መጽሐፍ

12.መርሐ ህይወት

13.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

5.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

6.ቅዱሳት ሥዕላት በሲዲ በፍላሽ በዲጅታል ህትመት

7.የታተመ ስለ ቅዱሳት ሥዕላት 2በ 2 የሆነ በውስጡ ከ5ያልበለጡ ከ5 ያላነሱ ቅዱሳት ሥዕላት ያሉበት ባነር

8.ከቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ ፎቶ የተነሱ ቅዱሳንን ሚያሳዩ ቅዱሳት ሥዕላት

9ስለ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

10. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘናእና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዥ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

2.በእለቱ የተማሩት ቅዱስ ማን እንደሚባል የስማቸው ትርጉም ምን እንደሆነ ታሪካቸውን እና ከታሪካቸው ምን እንደምንማር በቃል እና በጽሑፍ መጠየቅ

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆንበዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40ቀን ይሆናል 40 ሲባዛ በ40 እኩል ሆናል 16 ሰዓት ይመጣል ስለዚህ በአጠቃላይ በዓመት 16ሰዓት ይወስዳል።

ግእዝ ለህጻናት ሶስት (ሶስተኛ ክፍል)

የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው እንደጨረሱ

1. በቃላቸው ከአአትብ ገጽየ ጀምረው እስከ ዓርብ ውዳሴ ማርያም ድረስ በየቀኑ ያደርሳሉ
2. መርሐግብራቸውን በግእዝ ጸሎት ይከፍታሉ ይዘጋሉ
3. የግእዝ ቁጥሮችን ጠንቅቀው አውቀው በተጠየቁ ጊዜ ይመልሳሉ
4. መጽሐፍ ቅዱስን ያለምንም የቁጥር ስህተት ማንበብ ይችላሉ።
5. ምግብ በልተው ስብሐት በግእዝ ያደርሳሉ

5. ከቤታቸው ሲወጡ እና ሲተኙ ውዳሴ ማርያም ያደርሳሉ

6.የዜማ ምልክቶችን የተወሰኑትን ይለያሉ

ግእዝ ለህጻናት ሶስት (ሶስተኛ ክፍል)ዝርዝር ይዘት

መስከረም 1ኛ ሳምንት የተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ሰላም ለኪ ክለሳ ውዳሴ ማርያም ዘሰኑይ ፈቀደ እግዚእ የዜማምልክቶች

4ኛ ሳምንት ሠረቀ በስጋ ለሔዋን የዜማ የዜማ ምልክቶች ጥናት

ጥቅምት1ኛ ሳምንት ኢየሱስ ክርስቶስቃል የዜማ ምልክቶች ጥናት

2ኛ ሳምንት ርዕየ ኢሳይያስ ነቢይ የዜማ ምልክቶች ጥናት

3ኛ ተፈሳህ ወተሐሰይ ኩሉ የዜማ ምልክቶች ጥናት

4ኛ ዘሀሎ ወይሔሉ

ህዳር 1ኛ ሳምንት ተፈስሒ ኦ ቤተልሔም

2ኛ ሳምንት ትትፌሳህ ወትትሐሰይ

3ኛ ሳምንት ብርሃን ዘበአማን

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አማሽ ፈተና

ታህሳስ1ኛ ሳምንት ዘሰሉስ አክሊለ ምክህነ

2ኛ ሳምንትእስመ በፈቃዱ ዐቢይ ውእቱ

3ኛ ሳምንት አንቲ ውእቱ ዘርዕየ ሙሴ

4ኛ ሳምንት አንቲ ውእቱ ገራህት

ጥር 1ኛ ሳምንት ተፈስሒ ኦ ወላዲተ እግዚእ

2ኛ ሳምንት ተፈስሒ እስመ ድልወ ተሰመይኪ

3ኛ ሳምንት ኦድንግል ኦ ቅድስት

4ኛ ሳምንት ቃለ አብ ህያው

የካቲት 1ኛ ሳምንት ውእቱኬ ዘወረደ

2ኛ ሳምንት ዕበያ ለድንግል ኢይትከሃል

3ኛ ሳምንት ዘውእቱ እብን ዘርእየዳንኤል ኮንኪ አጽቀ ንጹሐ

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

መጋቢት1ኛ ሳምንት አንቲ እሙ ለብርሃን

2ኛ ሳምንት አይ ልሳን ዘይክል ነቢበ

3ኛ ሳምንት ተፈስሒ ኦ ማርያምእም ወአመት

4ኛ ሳምንት ክለሳ እና ፈተና

ሚያዝያ1ኛ ሳምንት ውዳሴ ዘረቡዕ ኩሉ ሰራዊተ ሰማያት

2ኛ ሳምንት ኩሉ ትውልድ ተነበዩ ላዕሌኪ ዐቢያተ

3ኛ ሳምንት አንቲ ዘበአማን ደመና

4ኛ ሳምንት ረከብኪ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሀደረ ላዕሌኪ

ግንቦት 1ኛ ሳምንት ግብረ ድንግል ይሴብሕ ልሳንነ - ተፈስሒ ኦጸዋሪቱ ለዋሕድ

2ኛ ሳምንት ግብረ ድንግልከተፈስሒ ኦ ጸዋሪቱ-ዘሎቱ ክብር ወስብሐት

3ኛ ሳምንት የዐቢ ክብራ ለማርያም

4ኛ ሳምንት የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ሰኔ1ኛ ሳምንት ሕዝቅኤል ነቢይ

2ኛ ሳምንት ኖህትሰ ድንግል ይእቲ

3ኛ ሳምንት ውዳሴ ዘሐሙስ እፀእንተ ርዕየ

4ኛ ሳምንት ናዐብየኪ ኩልነ ትምክህተ ኩልነ

ሐምሌ 1ኛ ሳምንት ትምክህተ ኩልነ መከለስ

2ኛ ሳምንት ኦዝ መንክር ወእጹብ- ኦ ዝ መንክር ልደተ

3ኛ ሳምንት ከኦዝ መንክር ልደተ- መጨረሻው

4ኛ ሳምንት ኦዝ መንክር ነስአ አሐደ

ነሐሴ 1ኛ ሳምንት መሐለ እግዚአብሔር ለዳዊት

2ኛ ሳምንት ዳዊት ዘነግሠ ለእስራኤል

3ኛ ሳምንት አሐዱ ዘእምቅድስት ሥላሴ

4ኛ ሳምንት የማጠቃለያ ፈተና

<u>የማስተማሪያ ዘዴ</u>

ትምህርቱን የዜማ ምልክቶችን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ጽፎ ወይም በዲጅታል ጽሑፍ ጽፎ ፕሪንት በማድረግ እና ለሁሉም በሚታይ መልኩ በመለጠፍ ወይም ሁሉም ውዳሴ ማርያም በግእዝ የተጻፈ ገዝተው እንዲመጡ በማድረግ ቀድሞ ስለ ትምህርት አሰጣጡ መምህሩ ለተማሪዎች በመግለጽ ከእኔ በኋላ በሉ በማለት ከእርሱ ቀጥለው ቃል በቃል በማስጠናት እንዲሁም እሱ ካለ በኋላ እንዲመልሱ በማድረግ፤ይሔንን በመደጋገም እስኪያሠርፁት በመመላለስ ተማሪዎች በቀኝ በግራ ወንድ እና ሴት እንዲመላልሱት በማድረግ፤ ከተማሪዎች መካከል ሁለት ሰው ወስዶ እንዲሉት ትምህርቱ መያዙን እስኪያረጋግጥ ድረስ መምህሩ መላልሶ መንገር ተማሪዎችም መላልሰው እንዲሉት በማድረግ ማስተማር ፤ወይም እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ማቅረብ ማስተማር ይቻላል። በየዕለቱ የተወሰኑ የዜማ ምልክቶችን እንዲይዙ በማድረግ ማስተማር ዜማ ምልክቱን ካጠኑት በዛው መሰረት ሌላውን ስለሚያዜሙት

<u>መርጃ መሳሪያ እና ማመሳከሪያ</u>

ይህንን ትምህርት መምህሩ

1.ከመዝገበ ጸሎት መጽሐፍ

2.ውዳሴ ማርያም በግእዝ

3.የዚህ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ ከሆነው ሽት ላይ ያገኘዋል

ለማስተማር ሚገለገልባቸው ነገሮች(ቁሳቁሶች)

1.ነጭ እና ጥቁር ሰሌዳ

2.ጠመኔ (ቾክ)

3.ማርከር

4.ማጥፊያ ጨርቅ (ዳስተር)

4.መምህሩ ሚለብሰው ነጠላ

5.የግእዝ ቁጥሮች የተጻፈበት ሁለት በሁለት የሆነ ባነር ወይም

6. ውዳሴ ማርያም በግእዝ

7. እንደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ አቅም ትምህርቱን በፓወር ፖይንት አዘጋጅቶ በስላይድ ለማቅረብ ፕሮጀክተር እና ኮምፒውተር ተጠቅሞ ማስተማር ይቻላል።

ምዘናእና ግምገማ

ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ

ትምህርቱም ሥርዓተ ትምህርቱም እንደሚፈለገው እየሄደ መሆኑን ለማወቅ

የመምህሩን የማስተማር ስልት እና ብቃት እና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል እና አረዳድ ለማወቅ

ትምህርቱ ዓላማውን ከግብ ማድረስ አለማድረሱን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የምዘና እና ግምገማ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላሉ

1.የተጻፈውን እየጠየቁ የተጻፈውን እያዩ እንዲመልሱ በማድረግ

2. የተጻፈውን ወይም የተለጠፈውን በማንሳት በቃል መያዝ አለመያዛቸውን በመጠየቅ

3 በየወቅቱ የቤት ስራ በመስጠት

4. ከተማሪዎች አንዱን ድንገት ይኼንን በለው በማለት

4.በየወቅቱ ፈተና በመፈተን

5. የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ያለፈውን ትምህርት መጠየቅ

5 በየወቅቱ ስለተማሩት ትምህርት የክፍል ስራ በመስጠት መመዘን ይቻላል

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ትምህርት የህጻናትን ትምህርት የመቀበል የአእምሮ ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በሳምንት 1ቀን ለ40 ደቂቃ የሚሰጥ ሲሆን በዓመት ውስጥ በዓላትን እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት ሲነሱ 40ቀን ይሆናል 40 ሲባዛ በ40 16 ሰዓት ይመጣል ስለዚህ በአጠቃላይ በዓመት 16ሰዓት ይወስዳል።

4ኛ ክፍል(አዳጊ አንድ)

እድሜያቸው ከ11-14ዓመት የክፍል ደረጃቸው ከ5-8ኛ ክፍል ወይም የህጻናት ሁለትን ትምህርት የጨረሱ በሳምንት ለሁለት ቀናት ለ4ሰዓት ያህል በሳምንት ለሁለት ሰዓት ይማራሉ።

በአጠቃላይ ስድስት የትምህርት ዓይነቶችን ሲማሩ ሁሉም ትምህርቶች በወሰነ ትምህርት የሚቀየሩ ይሆናሉ።

የትምህርት ዓይነቶቹም

1.ዜማ (መዝሙር) አጫጭር የግእዝ መዝሙራት

2.ግእዝ (የቃል ጥናት ከ ዐርብ ውዳሴ ማርያም እስከ አንቀጸ ብርሃን ድረስ

3.ትምህርተ ሃይማኖት መግቢያውን እና ሥነ ፍጥረት

4.የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያውን

5.ሥነ ምግባር ዐበይት ሥነ ምግባራት

6.የቤተ ክርስቲያን ታሪክ (የቤተ ክርስቲያናን ምሳሌዎች)

የትምህርቶቹ አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማ ዝርዝር ይዘት የሚወስደው ደቂቃ ማስማሪያ ዘዴ መርጃ መሳሪያ ምዘና እና ግምገማ ስልት በዝርዝር ይሰራል።

አራተኛ ክፍል አዳጊ አንድ ዜማ (መዝሙር)

የትምህርቱ ዓላማ

በዚህ ክፍል የዓመቱን ትምህርት ተምረው ሚጨርሱ ሰንበት ተማሪዎች

1.በዓመቱ መጨረሻ ከ48 ያላነሱ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ ኦርቶዶክሳዊ ወዛቸውን ያልለቀቁ መዝሙራትን አጥንተው ማቅረብ መዘመር ይችላሉ።

2.ትክክለኛውን መዝሙር ከዚህ እድሜያቸው ጀምረው መርጠው ይዘምራሉ

3.ሌላ መልክ ያለውን መዝሙር ይርቃሉም ያርቃሉም

4.የቤተክርስቲያናችንን የመዝሙር ወዝ ይለምዳሉ።

5.በቤተክርስቲያናችን አውደ ምሕረት ኦርቶዶክሳዊ ወዙ ያልራቀውን መዝሙር ያቀርባሉ

አራተኛ ክፍል አዳጊ አንድ ዜማ (መዝሙር) ዝርዝር ይዘት

መስከረም 1ኛ ሳምንት ተማሪዎች ምዝገባ እና ቅበላ

2ኛ ሳምንት ስለትምህርቱ አጠቃላይ ገለጻ

3ኛ ሳምንት ወአንተኒ ህጻነ፡ (ዐውደ ዓመት) መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ (ጎብሩ ቃለ)

4ኛሳምንት በመንፈስ የሐውር (መጽአት ወለታ) ዮም በዓለ መስቀሉ (መስቀል አብርሀ)

ጥቅምት 1ኛ ሳምንት ርሃበ ወጽማ (እስከ ማዕዜኑ)

2ኛ ሳምንት አክሊለ ጽጌ (እንዘ ተሀቅፊዮ)

3ኛ ሳምንት ከመጽጌ ሮማን (አዘክሪ ድንግል)

4ኛ ሳምንት እንዘ ተሀቅፊዮ (ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል)

ህዳር1ኛ ሳምንት አማኑኤል ጌታዬ ሆይ (ዘሰማየ ገብረ)

2ኛ ሳምንት ለጌታዬ ለእግዚአብሔር (ዝንቱ ኩሉ ኮነ)

3ኛ ሳምንት እሳተ ጽርሁ (ኩሉ ዘፈቀደ) እንዘ የአምር (የሀያላንኃያል)

4ኛ ሳምንት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አጋማሽ ፈተና

ታህሳስ1ኛ ሳምንት ውእቱ ሊቆሙ (ሚካኤል ስዩም)

2ኛ ሳምንት ከመ ትባርከነ (ባህራንኒ)

3ኛ ሳምንት ቀዋምያን ለነፍሳት (ገብርኤል ምልአኒ)

4ኛ ሳምንት በኮከብ መጽኡ (በጎል ሰከበ)

ጥር 1ኛ ሳምንት ወወለደት (ውስተ ማኅጸነ ድንግል)

2ኛ ሳምንት እንዘ ህጻን ልህቀ (ሀዲጎ ተስአ)

3ኛ ሳምንት ክርስቶስ ተወልደ ወተጠምቀ (ኢየሱስ ሖረሀገረ እሴይ)

4ኛ ሳምንትሶበ ሰማዕነ ዜናከ መጻእነ (ተፈስሒ ቤተ ክርስቲያን)

የካቲት 1ኛ ሳምንት የቤታችን እራስ ልጅሽነው (አማህኩኪ)

2ኛ ሳምንት የማኑ ተሀቅፈኒ (ትዌድሶ መርአት ወትብሎ)

